ታት ብቻ አገር ሆና የቆመችው ኡጋንዳ መቃብሯን ቆፈረች ፣ ከሺህ
ዓመት በላይ አለኝ የምትለው ካምቦዲያ በባሰ ሁኔታ ራሷን እንጦሮ
ጦስ አወረደች ። የኡጋንዳ ውድቀት ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለመ
ላው የሰው ልጅ ትምህርት የሚሆን ነው ።

ለእርሻ ምቹ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት ስላላት ኡጋንዳ በውጭ
ርዳታ ሊያንሰራራ የሚችል የኤኮኖሚ መሠረት አላት ። ይህ ብቻ
እንኳን በአንድና ሁለት ትውልድ ኡጋንዳ እንደምንም ትርጉም
ያለው ሀገር ሆና ልትቆም እንደምትችል ተስፋ ያሳድራል ። ይህ ተሃ
ድሶ ሊመጣ የሚችለው ግን አስከፊ መሪዎች ተወግደው ሕዝቡ የወ
ደፊት ዕድሉ ወሳኝ መሆን ሲችል ነው ።

በዚህ አቅጣጫ የመጀመሪያው ርምጃ የሰላም መከበር ነው ።
ትክክለኛና ነፃ ሕዝባዊ ምርጫ ማካሄድ መቻል ነው ። ሕዝቡ ትጥቅ
ፈትቶ የጎሳዎችን ሚዛን የጠበቀ ጦር ማደራጀት ሲቻል ነው ።በእ
ኩልነትና በነፃነት ሁሉም አሥራ ሶስት ጎሣዎች በሀገሪቱ የኢኮኖሚና
የፖለቲካ ሕይወት ተገቢ ቦታ እስካላገኙ ድረስ ኡጋንዳ የምትባል
የእውነት ሀገር አትኖርም ። ኡጋንዳ ይህ ዕድል በአንድ ወቅት አጋጥ
ሟት ባትጠቀምበትም ሁለተኛው አጋጣሚ ብቅ ሲል ስለሚችል
ምርጫው የራስዋ ነው ።

የኡጋንዳ መሪዎች በሥልጣን መባለግና እምባገነን መሆን ሲጀ
ምሩ የምዕራብ ኃያላን ቃል የገቡትን የገንዘብ ርዳታ አቋረጡ ።
ይህም ትክክለኛ አሠራር ነበር ።ከአስቸኳይ ጊዜ ምግብና መድሃኒት
ሌላ በኡጋንዳ ገንዘብ ማፍሰስ ማበላሸት ነበር ።ያ ፣ ጊዜ በኡጋንዳ
ግድብ የሚሰራበትና መንገድ የሚጠገንበት አልነበረም ።የኡጋንዳ
ችግር በገንዘብ ይፈታል ብሎ ማሰብ መጠጥ የለመደ ጠጭ ከዚያ
መጥፎ ልማዱ እንዲወገድ ጠርሙስ ውስኪ እንደመለገስ ያህል የቂል
ሥራ ይሆን ነበር ። ኡጋንዳ ተቀርቋሪ ያጣች ሀገር ስለሆነች ከራሳ
ቸው ከኡጋንዳውያን በስተቀር መልሶ ሊያቋቁማት የሚችል ማንም
የለም ። በጠመንጃ ማምለክና ጭካኔ ፣ ስግብግብነትና ለሰው ሕይወት
ክብር አለመስጠት ማክተም አለበት ።



## ምዕራፍ አምስት

# አንድነትን ፍለጋ

"ስብሰባዎች በከንቱ ጊዜ ማባከኛዎች ናቸው ። በአፍሪካ
አንድነት ድርጅት ዓመታዊ ስብሰባዎች ሁሉም እየተነሳ
መናገር ብቻ ነው ። እዚያ ተቀምጠው የሁሉንም ንግግር
መስማት በንዴት የሚያስጮኸኝ ይመስለኛል ።"

ኤል ሀጂ ኦማር ቦንጎ
የጋቦን ፕሬዚዳንት

በየዓመቱ ክረምት መግቢያ ላይ በዓለም ላይ ከፍተኛ ሥጋት
የተደቀነባቸውን የፖለቲካ ሥራዎች የያዙት ሃምሳ ሰዎች በአንድ
የአፍሪካ ከተማ ይሰበሰቡና የአህጉራቱን ጉዳዮች ይወያያሉ ። ይህ
የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዓመታዊ የመሪዎች ስብሰባ ለመሪዎቹ
እፎይታ የሚሰጥ መድረክ ነው ። ብዙውን ጊዜ ከአገራቸው ግዙፍ
ችግሮች ሸሽቶ ለመሰንበት ዕድል ይፈጥርላቸዋል ። የአፍሪካን
ልማት ከሚያጓትቱ እያሌ ችግሮች ማለትም ከሙስና ፣ ከድርቅ ፣
ከረሀብ ፣ ከኃያላን ጣልቃገብነት ፣ ከድንበር ግጭቶች ፣ ከኢኮኖሚ ውድ
ቀቶች ፣ ብቃት ከጐደለው አመራር ፣ ከርዕዮተዓለም ልዩነቶች ፣ ከሰብ
ዓዊ መብት ረገጣዎች ፣ ከፖለቲካ አለመረጋጋት ፣ ከወሊድ ቁጥር
መናር ሸሽተው የሚሰነብቱበት ሰሞን ነው ። ስብሰባው የሚጀም
ረው በወንድማዊ መተቃቀፎችና ስለአንድነት በመማል ነው ።
ከሶስት ቀን በኋላ ሲጠናቀቅ ፕሬዚዳንቶችና ጀኔራሎች በመጣደፍ
ወደ የሀገሮቻቸው ይመለሳሉ ። በስብሰባው ያከናወኑት ነገር ቢኖር

የደቡብ አፍሪካን የዘር መድልኦ ማውገዝና ላለመስማማት መስማማት ነው ።

“እነዚህን ሰዎች በአንድም ጉዳይ ላይ እንዲስማሙ ለማድረግ መሞከር በጊታር ላይ ሽንትን እየሸኑ የሙዚቃ ድምፅ ለማውጣት እንደመሞከር ነው” ሲሉ የሞሪሽየስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሀሮልድ ዋልተር ከአንድ ዓመታዊ ስብሰባ ሲወጡ ተችተዋል ።

በ1963 አአድ የተመሠረተው በተባበሩት መንግሥታት አመሠራረት መሠረት ነው ። ከደቡብ አፍሪካ በቀር ሁሉም የአፍሪካ አገሮች የድርጅቱ አባሎች ናቸው ። ለነገሩ አአድ ለጥቁር አፍሪካውያንና ለአረቦች በአንድ ድምፅ ለመናገር ጥሩ ዕድል ፈጥሮላቸዋል ። የአፍሪካን ችግሮች ለማጥናትና መፍትሔ ለማስገኘት መድረኩን አመቻችቷል ። በቻርተሩ ከተጠቀሱት መርሆዎች መካከል ፤ የአፍሪካ ሕዝቦች በኤኮኖሚና በፖለቲካ እድገት መጨበጥ ፣ ቅኝ አገዛዝን በማንኛውም መልኩ ከአህጉሪቱ ማስወገድና የአፍሪካን አንድነት ማጠናከር የሚሉ ይገኙበታል ። ሀሳብ ለመለዋወጥ ትልቁ መድረክ ነው ። እስካሁን ብዙ ጉልህ ጉዳዮች ባያከናውንም አአድ ሕልውናውን ጠብቆ መቆየቱ በራሱ አንድ ታላቅ ውጤት ነው ። መላዋ አፍሪካ አንድ ቀን በጋራ ስምምነት የፍትሕ መጓደሎችንና የእኩልነት አለመጠበቅን የምታስተካክልበት መድረክ እንደሚሆን በተስፋ ትጠብቀዋለች ።

አአድ እንደተባበሩት መንግሥታት የፀጥታ ምክር ቤት የለውም። ውሳኔዎቹን ለማስፈጸም ኃይል የሚጠቀምበት አንቀጽም የለውም። በመግባባት እንጂ በመቅጣት የሚያስጽመው ነገር የለም ። በመተባበርና በመላ መግባባት እንጅ በማውገዝ የሚያከናውነው ጉዳይ የለም ። ይህም ሥልጣኑ ሽባ የሆነው በቻርተሩ ውስጥ በተጠቀሰው ና አባል አገሮች በሌላው አባል አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አይገቡም በሚለው አረፍተነገር ነው ። የአባባሉ መሠረተ ሃሳብ ጥሩ ነው ። ነገር ግን የአፍሪካ መሪዎች ይህን ሐረግ ቃል በቃል በመተርጎም አአድ የእርስ በርስ ጦርነቶችን ለማስማማት ፣ በአጥፊው ላይ ማዕቀብ ለማድረግ ፣ በአረመኔ መሪዎች ላይ ተጽዕኖ ለማድረግና አንድነትን ለማበረታታት የሚችልበትን የአሠራር ሥልት ነፍገውታል ።



ኢዲ አሚን 300,000 ኡጋንዳውያንን ሲያርዱ ፣ አፍሪካ በእርስ በርስ ግጭት ስትተራመስ ፣ ኢትዮጵያ ወህኒ ቤቶችዋን በ30,000 የፖለቲካ እሥረኞች ስታጨናንቅ የአአድ ምላሽ ዝምታ ነበር ። ምነው ቢባል በግልም ሆነ በጋራ ስለነዚህ ፀረ—ሕዝብ ተግባራት መናገር በእነሱ ቤት ጣልቃ መግባት ነው ። የአፍሪካ መሪዎችን የወንድማማችነት ያልተፃፈ ደንብ መጣስ ነው ። አገሬን እንዳሻኝ እንድመራው ፣ እናንተም ሕዝባችሁን እንዳሻችሁ ብትጨፈጭፉት ቃል አልተነፍስም ፤ በዚህ መልኩ ሁላችንም የሥልጣን እድሜያችንን እናራዝማለን ነው ።

ይህም በ1979 ታንዛንያ ኡጋንዳን ስትወር ተፈትኗል ። ናይጀርያና ሱዳን በአአድ ዓመታዊ ስብሰባ ላይ አድራጎቱን ተቃወሙ ። ይህን ያደረጉት ለኢዲ አሚን በማዘን ሳይሆን የታንዛንያው ኒሬሬ ለአፍሪካ አደገኛ አቅጣጫ በመቀየሳቸው ነው ። በጎረቤት ሀገር መሪ መሆን ያለበትን ሰው የሚወስኑ እሳቸው ከሆኑ ሌሎች ፕሬዚዳንቶች ተመሳሳይ ውሳኔዎችን ከማድረግ ምን ያግዳቸዋል? ወረራውን በማውገዝ ሁለት ጠንካራ ተቃውሞዎች ተሰነዘሩ ። ከዚያም ስብሰባው ወደ ሌሎች አጀንዳዎች አመራ ። የሚገርመው ሊቢያ አሚንን ለመርዳት ጦር በመላክ ጣልቃ መግባቷን በመጥቀስ ሙአመር ጋዳፊን የነቀፈ ሰው አለመኖሩ ነው ። በዚህ ክስተት የተገኘው ትምህርት ግልፅ ነበር ። አንድን ፕሬዚዳንት (የፈለገውን ያህል አረመኔ ቢሆንም) በሥልጣን ለማቆየት ጣልቃ መግባት ተቀባይነት አለው ፤ ለመገልበጥ ማገዝ ግን ተቀባይነት የለውም ።

የአፍሪካ መሪዎች በምርጫ ሳይሆን በመፈንቅለ መንግሥት ብዙ ሳይቆዩ ከሥልጣን ይወገዳሉ ። ለምሳሌ በ1963 የአአድን ቻርተር በአዲስ አበባ ከፈረሙት ሰላሳ መሪዎች ውስጥ በ1980 በሥልጣን ላይ የቆዩት ሰባት ብቻ ነበሩ ። ከሌሉት መካከል ሁለቱ በወታደሮቻቸው ተገደሉ ፤ ሁለቱ ሞቱ ፤ አሥራ ሰባቱ በወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ከሥልጣን ተባረዋል ።

የአፍሪካ መሪዎች ለአአድ ስብሰባ ሲገናኙ በናፍቆት መልክ የሚተቃቀፉበት አንዱ ምክንያት በሕይወትና በሥልጣን ቆይቶ ለዓመት መገናኘት ራሱ ትልቅ ፀጋና ሊተነበይ የማይቻል በመሆኑም ነው ። ዘንድሮ የመጣው ከርሞ ለመኖሩ ምንም መተማመኛ የለም። በ1979 የላይቤሪያው ፕሬዚዳንት ዊሊያም ቶልበርት በአገራቸው ላይ የአአድን ዓመታዊ የመሪዎች ጉባኤ ባስተናገዱበት ወቅት አስገራሚ ሁኔታ ታየ ። ከአውሮፕላን ማረፊያው እስከ ጉባኤው አዳራሽ የመሪዎች ፎቶግራፎች በትልልቁ ተደርድረዋል ። ስድስት የፎቶ ፍሬሞች ላይ ግን የሀገሮች ስም ብቻ ተጽፎበታል ። ምክንያቱም ፈጣን የሆነ የመሪዎች መለዋወጥና መፈነቃቀል ስለነበረ ማን የሚባል መሪ እንደሚመጣ አዘጋጅዋን አገር ግራ አጋብቶ ነበር ። ካለፈው ዓመት ስብሰባ ወዲህ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ብቻ በኡጋንዳ ሶስት ፕሬዚዳንቶች ተለዋውጠውባታል ። ጋና ሶስት የቀድሞ መሪዎችን በደፋ ረሽናለች ። ኮንጎ መሪዋን በቁም እሥር አውላለች። የተከሰሱበትም አንድ ሚሊዮን ዶላር ሰርቀው የወርቅ አልጋ አሠርተዋል በሚል ነው ። የቻድ ፕሬዚዳንት ከግልበጣ አምልጠው ተሰደዋል ። የሞሪታንያ ጠቅላይ ሚኒስትር በአውሮፕላን አደጋ ሞተዋል። የኢኳቶሪያል ጊኒ የእድሜ ልክ ፕሬዚዳንት ከሥልጣን ተወግደው ተገደሉ ። የኬንያው ጆሞ ኬንያታና የአልጀርያው ፕሬዚዳንት ሁወሪ ቡሚዲያን በሞት ተለይተዋል ።

ከዓመት በፊት በካርቱም በተደረገው ተመሳሳይ የመሪዎች ስብሰባ ሰሞን ፕሬዚዳንት ቶልበርት በሒልተን ሆቴል ግቢ ነጭ ቁታ ለብሰው የሰውነት እንቅስቃሴ ልምምድ ሶምሶማ ሩጫ ሲያደርጉ የተመለከቱ ሌሎች መሪዎች ይሳለቁባቸዋል ። በአፍሪካ ባህል ያልተለመደ ስለሆነ ነው ። ከዚያም ቶልበርት ስብሰባ ሲገቡ ከኋላና ከፊት ጠርብ በሚያካክሉ ጠባቂዎች ታጅበው ብቅ አሉ ። አጃቢዎች የያዙዋቸው የሬዲዮ መገናኛዎች ያንቃጭላሉ ። ለደህንነታቸው ሥጋት ላይ እንደነበሩ ያስታውቃል ። እንደፈሩትም አልቀረላቸውም ። ከሃያ ወራት በኋላ በወታደሮቻቸው ተገደሉ ። በዚያን ጊዜ የአአድ የዓመቱ ሊቀመንበር ነበሩ ።



የአአድ የመሪዎች ስብሰባ በየዓመቱ በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች ይካሄዳል ። አስተናጋጁ አገር ብዙ ወጭ አለበት ። በሌለ አቅም ተበድረው የሚያዘጋጁም አሉ ። ጋቦን በ1977 አንድ ቢሊዮን ዶላር ፣ ሴራሊዮን በ1980 ሁለት መቶ ሚሊዮን ዶላር በማውጣት የጉባዔ አዳራሽ አሰርተው ነበር ። ለሆቴሎችና መንገዶች ማሰሪያ ፣ ለእንግዶች ማመላለሻ መኪናዎች ፣ ለጋዜጠኞች ማጓጓዣ አውቶቡሶች ፣ ለአጃቢ ትራፊክ ፖሊሶች ሞተር ቢስክሌቶች መግዣ ወዘተ. . . ብዙ ገንዘብ ያወጣሉ ። ስብሰባው ከሶስት ቀን በኋላ ሲጠናቀቅ ጉባዔ አዳራሹም ያለሥራ አፉን ከፍቶ ይቀራል ፣ ሆቴሎችም የሚያስተናግዱት ስለማይኖር እየከሰሩ በመንግሥት ድጐማ ይቀጥላሉ ። ለዝናና ለመሪዎች ጉራ ሲሉ እንጅ ብዙዎቹ ወጭው ይጐዳቸዋል ።

የጋቦኑ ፕሬዚዳንት አል ሀጅ ኦማር ቦንጎ አገራቸው ስብሰባውን ባስተናገደችበት በ1977 ያወጡት ገንዘብና ያሰሯቸው ሁሉ ከአገሪቱ አቅም ጋር ሲተያይ የሚያስገርም ነው ። በነገራችን ላይ ኦማር ቦንጎ በዚያን ወቅት ፕሬዚዳንት ብቻ ሳይሆኑ የፕላንና መርሃ ብሔር ፣ የትምህርት ፣ የማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትርነቱን ደርበው ይዘዋል ። የተለያዩ የፓርቲ አካላትና የሴቶች እድገት ጉዳይ ኃላፊም ናቸው ። የስብሰባው ጊዜ ሲቃረብ በ800,000,000 ዶላር ያሳነፁትን ቤተመንግሥት አጠናቀቁ ። በአዳራሹ የስብሳቢው ቦታ በእብነበረድ አምሯል ። ቦንጎ ቁመታቸው አጭር ቢሆንም በኮታቸው ላይ የደረደሯቸው የበቅሎ ጌጥ የመሰሉ አንፀባራቂ ቁልፎች የኤሌክትሪክ አምፑሎችን ብርሃን ያስንቃሉ ። ጋቦን እብነበረድ አምራች ብትሆንም አዳራሹን ከስብሰባው በፊት ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገውን ሁሉ በፍጥነት ለማቅረብ ስላልቻለች ምርጥ እብነበረድ ከጣሊያን ሀገር ማስመጣት ተገደደች ። ይህም አዳራሽ ብቻ 23,000,000 ዶላር ፈጀ ።

የቦንጎ ቤተመንግሥት የዳንስ ክበብ ፣ የመዋኛ ቦታ የሚያካክሉ የባኞ ገንዳዎች ፣ ሁለት ትያትር ቤቶች አሉት ። ትያትር ቤቶቹ እማካይ መመልከቻ ክፍል ስላላቸው ቦንጎ በሚፈልጉበት ጊዜ አንዲት በእጅ የምትገፋ ነገር በመጫን ያሽከረከሩትና የመረጡትን የመድረክ ዝግጅት ይመለከታሉ ።

ይህ ሁሉ የተዘጋጀው በብድር ገንዘብ ቢሆንም ለጊዜው አጀይብ ተባለለት ። በሊቨርቢል ከተማ የአፍሪካ መሪዎች በማርቸዲስና በካዲላክ በሞተር ቢስክሌተኞች ታጅበው ጥሩምባ እያንባረቁ ተሽከረከሩበት ። ሁሉም በክብር ዘቦች ተከበው ይዘዋወራሉ ። የራሳቸው የቦንጎ ክብር ዘቦች እንደ ሞቡቱ ሴሴሴኮ ሁሉ የሞሮኮ ወታደሮች ናቸው ። የአገራቸውን ወታደር አላመኑም ። የኢዲ አሚን ጠባቂዎች ደግሞ ፍልስጥኤማውያን ናቸው ። የጋቦን የክብር ዘብ በጉባዔው አዳራሽ መግቢያ ተሰልፎ በወርቅ ሻምላዎች ሰላምታ በማቅረብ ይቀበላል ። የጋቦን ወታደሮች በየኮሪደሩ እየተዘዋወሩ የጋዜጠኞችን ድምፅ መቅጃዎች ሳይቀር በመፈተሽ (መልእክት ማስተላለፊያ ያለመሆኑን) በሙሉ የጦር ሜዳ አለባበስ ቅኝት ያደርጋሉ ።

የሊቨርቢል ከተማ ሴቶች ፕሬዚዳንቶችን እየጨፈሩ እንዲቀበሉ በመታዘዛቸው ከአውሮፕላን ማቢያው እስከሆቴሎችና እስከ ጉባዔው አዳራሽ ተደርድረው ይጨፍራሉ ። ሴተኛ አዳሪ የሚባሉ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸውና ግማሾቹም ታፍሰው ተወስደው አንድ አይታይም ። የተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ "በስብሰባው ሰሞን አካላችሁን ሳይሆን ልባችሁን ክፈቱ" የሚል ነበር ። ቦንጎ ለዚያው ሰሞን ወደ ጆሀንስበርግ (ደቡብ አፍሪካ) የሚደረገው መደበኛ የአውሮፕላን በረራ እንዲቋረጥ አደረጉ ። ከሮዴሽያ እያስመጡ በየሆቴሉ የሚያድሉትን ሥጋም ከቦትስዋና እንደሚመጣ አስመስለው ለማስወራት ሞከሩ ።

አንድ ጋዜጠኛ አውሮፕላን ማረፊያ እንደደረሰ ከሳልስበሪ መምጣቱን ሲገልጥላቸው ወዲያው ወደመጣበት መለሱት ። ከሁለት ቀን በኋላ ጉዳዩ ሲጣራ ግን ጋዜጠኛው የመጣው ነፃ ካልወጣችው ከሮዴሽያ ዋና ከተማ ሶልስበሪ ሳይሆን እንግሊዝ አገር ካለችው ሶልስበሪ መሆኑ ታወቀ ። በዚያው ቀን ከባንግላዴሽ የመጡ ሁለት ዲፕሎማቶች የታዛቢነት ወንበር እንዲፈቀድላቸው ጠየቁ ። አዘጋጅው ኮሚቴ ባንግላዴሽ የሚለው ስም አዲስ የተቋቋመ የአፍሪካ የነፃነት ንቅናቄ መስሎት ለሁለቱ ሰዎች የተወካይነት ወንበር ፈቀደላቸው ። በሌላ በኩል ከሳኦ ቶሜና ፕሪንቺፔ የመጡ ተወካዮች ከአፍሪካ ውጭ



የመጡ ስለመሰላቸው የተወካይነት ካርድ ለመስጠት ብዙ አቅማሙ ። በኋላም "በእርግጥ ሳኦቶሜ አፍሪካ ውስጥ ናት?" በማለት አንድ የኮሚቴው አባል ጠየቀ ። ለዚያውም ለጉባዔው ተሳታፊዎች በተዘጋጀው መጽሔት ላይ የፕሬዚዳንቱ ፎቶግራፍ በሚሆንበት ቦታ በተቀናቃኝነት ከአገር የተሰደደውን የቀድሞው የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ፎቶ አድርገው ስለነበር ፣ ያከፋፈሉትን መጽሔት እንደገና በመሰብሰብ የፕሬዚዳንቱን የማኑኤል ዳኪስታ ፎቶ በቦታው ላይ ደርበው እየለጠፉ ሰጡን ።

በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዓመታዊ ስብሰባ ላይ ከሚገኙት ሰባ የሚሆኑ ጋዜጠኞች መካከል የአፍሪካውያን ጋዜጠኞች ብዛት ከስድስት አይበልጥም ። የተቀሩት በሙሉ ምዕራባውያን ናቸው ። የሶስት ቀኑ ስብሰባም ትዕግሥት የሚያስጨርስና ተስፋ የሚያስቆርጥ ዓይነት ነው ። ከመክፈቻውና ከመዝጊያው ሥነሥርዓት በስተቀር የተቀረው የስብሰባው ጊዜ በዝግና በምስጢር የሚካሄድ ነው ። ሆቴል የማያገኙ ጋዜጠኞች ስለሚኖሩ አንድ ጊዜ ላይቤሪያ አንድ የጥንት መርከብ እንደሆቴል በመጠቀም ለጋዜጠኞች መሰንበቻ እንዲሆን አድርጋ ነበር ። ለዚያውም ለጋዜጠኞች መግለጫ መስጠት ያልተለመደ ስለሆነ ያለሪፖርት ሲጉላሉ መሰንበት የተለመደ ነው ።

አሜሪካ ፣ እንግሊዝ ፣ አውስትራሊያ ወጣትና ስለድርጅቱ ስብሰባዎች ልዩ ጥናት ያደረጉ ዲፕሎማቶችን በተመልካችነት ስለሚልኩ ምሥጢሮች ያገኛሉ ። እነዚህ ዲፕሎማቶች በገንዘብ የያዙዋቸው የአፍሪካ ልዑካን ስላሉ ማታ ማታ በሆቴላቸው እየተገናኙ በምሥጢር ስለተያዘው አጀንዳና ውይይት ይነጋገራሉ ። እነዚህ እርዕስተ ጉዳዮችም ብዙውን ጊዜ ስለነፃነት ንቅናቄዎች ፣ ስለ እርስ በርስ ጦርነቶችና ስለሰብዓዊ መብት ፖሊሲ ስለሆኑ በጉባዔው ውሣኔ አያገኙም ። ነገር ግን የአፍሪካን አስተሳሰብ ስለሚያንፀባርቁ የተባለውን ሁሉ ምሥጢር በማዘክዘክ ዲፕሎማቶቹ ለየሀገሮቻቸው መንግሥታት ያስተላልፋሉ ።

በጉባዔው አዳራሽ የአንድነት ስሜት የሚንፀባረቀው በመክፈቻውና በመዝጊያው ሥነሥርዓት ላይ ብቻ ነው ። ለዝግ ስብሰባ

በሮቹ ሲቆለፉ መሰዳደብና ጠብ ይጀመራል ። በየዓመቱም በዝግ ስብሰባ ወቅት ቢያንስ አንድ የቦክስ ትርኢት ይፈጠራል ። ፕሬዚዳንቶች ሲሰዳደቡና ሲሸሿጡ አስተርጓሚዎች በመደንገጥ እየተንተባተቡ ያስተረጉማሉ ። የስብሰባው ሊቀመንበርም "ሥነ ሥርዓት!" እያሉ በመምህ ሁሉም ሲንጫጩ አፍሪካ በየጎራው ትከፋፈላለች። ተራማጅ ነን የሚሉት በአንድ ወገን ፣ አፍቃሪ ምዕራብ የሆኑት በሌላ ወገን ፣ ለዘብተኞች በሌላ ጐራ መቧደን ይጀምራሉ ። በዚህ ላይ የክርስቲያን አገሮች አሉ ፣ የእስላሞች አገሮች አሉ ፣ አረቦች አሉ ፣ ጥቁር አፍሪካውያን በሌላ በኩል ይወግናሉ ። ፈረንሣይኛ ተናጋሪ አገሮች ፣ እንግሊዝኛ ተናጋሪ ነን ከሚሉት ራሳቸውን መለየት ይቃጣቸዋል ። በተጨማሪ አምስት ፖርቱጊዝ ተናጋሪዎች አንድ እስፓኚሽ ተናጋሪ አገር (ኢኳቶሪያል ጊኒ) ከሌሎች እንለያለን ባይ ናቸው ። በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት የሚሻኩቱ ጎረቤት ሀገሮችም በርካታ ናቸው ። ካርቱም በተደረገ አንድ ስብሰባ የዛየርና የአንጎላ ልዑካን አንድ ሆቴል ፎቅ ላይ እንዲያድሩ በስህተት ተይዞላቸው ሳለ ጠባቂዎቻቸው በጥላቻ በመፋጠጥ ሊታኩሱ ሲሉ የሆቴሉ ሥራ አስኪያጅ አንዳቸውን ወደ ሌላ ፎቅ በማዛወር ችግሩን አስወገደ ።

በየስብሰባው ላይ በግልጽ የሚታየው አፍሪካ በአንድ ከሚያስተሳስሯት ጉዳዮች ይልቅ የሚከፋፍሏት የበዙ መሆናቸው ነው ። በ1982 በምዕራብ ሰሃራ ጉዳይና በሙአመር ጋዳፊ የአአድ ሊቀመንበርነት ጉዳይ ላይ አፍሪካ በከፋ ደረጃ ተከፋፍላ ብዙ መሪዎች ከሊቢያው ስብሰባ ራሳቸውን በማግለላቸው ዓመታዊው ጉባኤ በምልዓተ ጉባኤ መጓደል ፈረሰ ። ከጥቂት ወራት በኋላ እንደገና በትሪፖሊ እንዲደረግ ተሞክሮ ዳግም ከሸፈ ። የአሁኑ አወዛጋቢ ነጥብ ደግሞ ቻድ በየትኛው ተቀናቃኝ ቡድን ትወከል የሚለው ጥያቄ ነበር ። በኋላም በ1983 እንደምንም በኢትዮጵያ ተሰብስበው ሊወስኑ ቢችሉም ጋዳፊ የአአድ ሊቀመንበርነት ስለተነፈጉ በቁጣ ስብሰባውን ረግጠው በመውጣት ወደ ሀገራቸው ተመለሱና በቻድ ላይ ጦርነት በማወጅ በሥልጣን ላይ የነበረውን መንግሥት ለመገልበጥ ሞከሩ ። በዚህ መልኩ ለአፍሪካ አንድነት ማለት እንደሕልም ሆነ ። የአንዱ አገር መሪ ምሁር ሲሆን የሌላው በውል ፊደል ያልለየ ነው ። የአንዱ አገር



ባለሥልጣኖች ማርክሲስት ነን ባይ ሲሆን የሌላው ካፒታሊስት ልሁን ባይ ነው ። የአንዱ አገር ዘላን ሕዝብ ከሌላው አገር እራሽ በእጅጉ የተለያየ ነው ። አንድ ቋንቋ የሚናገሩ መሪዎችም ምንም ያህል የሚያግባባቸው ነጥብ የላቸውም ። ኢትዮጵያና ሶማሊያ እድሜ ልክ ሲዋጉ ኖረዋል ። በየአንዳንዱ አገር ውስጥ ያሉት የተለያዩ ብሔረሰቦች እርስ በርስ ከመናቆር አልዘለሉም ። ታዲያ አንድ ሀገር ሊፈጥር ያልቻለውን ብሔራዊ አንድነት ሃምሳ አንድ አገሮች በምን ሁኔታ አንድነት ሊፈጥሩ ይቻላቸዋል? የቋንቋው ብዛት ፣ የጎሳው መበርከት ፣ የባህሎች ልዩነት ፣ የሃይማኖትና የፍልስፍና አለመመሳሰል ሲታይ አንድነትን ማጠናከር ብዙ ጥረትና ማስተዋልን የሚጠይቅ ነው ።

የአፍሪካ የአንድነት ጥያቄ እንደታለመው ባይከናወንና የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች ባይግባቡ አያስደንቅም ። በቅኝ ግዛት ዘመንም የአውሮፓ መሪዎች እንዲሁ ነበሩ ። የአውሮፓ ኃያላን የንግድ መስመሮችን ለመቆጣጠር ፣ ጥሬ ዕቃና ርካሽ ጉልበት ለማግኘት ፣ ለምርታቸው መሸጫ ገበያና ገገር ለማመቻቸት ፣ አፍሪካን በመቀራመት አምርረው ተሻኩተዋል ። አንዱ ሌላውን በማታለልና በብልጣብልጥነት ብዙ መጠላለፍ ነበራቸው ። እንግሊዝ ፣ ፈረንሣይ ፣ ጀርመን ፣ ጣሊያን ፣ ፖርቱጋል ሁሉም ይሻኩቱ ነበር ።

በኋላም በ1884 በበርሊን ተገናኝተው አሥራ አራት ሀገሮች ስለአፍሪካ ብዙ ተነታረኩ ። በዓመቱ በ1985 የበርሊኑን ስምምነት በመፈራረም በአፍሪካ ይህን አገር ይዣለሁ የሚል ለሌሎች ኃያላን በማሳወቅ መቆጣጠር እንደሚችል ተዋዋሉ ። በዚሁ ውል መሠረት ለተከታዩ አሥራ አምስት ዓመት የኃያላኑን የተጽዕኖ ክልል በመሉየት ለበላይነት ላለመፎካከር ተስማሙ ።

የበርሊኑ ጉባዔ አፍሪካን ለመከፋፈል እንጅ አንድነቷን ለመፍጠር አልበጀም ። የቅኝ ገዥዎች ያሰመሩት የሀገሮች ድንበርም ሰው ሰራሽና ትክክለኛ አከላለል የተከተለ አልነበረም ። ብሔረሰቦች የበዙባትን አፍሪካ ባህላዊ ተመሳሳይነት ያልጠበቀና ለዚህም ግድ ያላደረገ ክፍፍል በመሆኑ አንድ ቋንቋ የሚናገሩትን ብሔረሰቦች ለሁለትና

ለሶስት ክፋፍሎ በተለያዩ ሀገሮች በታተናቸው ። ለምዕት ዓመታት በቋንቋ ተመሳሳይነትና በጋራ ቅርስና ታሪክ ተሳስረው የኖሩትን ሕዝቦች በመለያየት ለትውልዶች የሚተርፍ ችግር ፈጠሩ ። በአግባቡ የተሰባሰበ አንድ ሕዝብ አልቀራቸውም ። ሁሉንም በታተኑት ።

በ1900 በአውሮፓ የነበሩ አፍሪካውያን የመጀመሪያውን የፓን አፍሪካ ጉባዔ በማካሄድ የአንድነት ስሜት በመፍጠር ለአፍሪካ አንድ ነትን በመሻት ቀዳሚው ርምጃ ነበር ። በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች 700,000 አፍሪካውያን ከቅኝ ገዢ ጌቶቻቸው ጐን ተሰልፈው ተዋግ ተዋል ። በ1940ዎቹ መጨረሻ የአህጉሪቱ መሪዎች ከፓን አፍሪካዊ ስሜት ወደ ነፃነት ትግል አዘነበሉ ። ጥቂቶቹ መሪዎች የአፍሪካ አገሮች ኅብረት (ዩናይትድ እስቴትስ አፍ አፍሪካ) በሚል አንድ ትልቅ አገር ሆና ነፃ እንድትወጣና እንድትመሠረት ተስፋ አድርገው ነበር ። ያም ቢቀር ቢያንስ እንግሊዝኛ ተናጋሪ የአፍሪካ አገሮችና ፈረንሣይኛ ተናጋሪዎቹ አንዳንድ የኅብረት መንግሥት በሰፊ ክልል እንደሚመሠርቱ ተመኝተው ነበር ። ሁሉም አልሆነም ። ይልቁንም አዲሶቹ ነፃ የሚወጡ ሀገሮች ተመሳሳይ ቋንቋና ባህል ታሪክ ያላቸ ውን ሀገሮች በአንድ የሚያሰባስብና የማይበታትን የሀገሮች ድንበር ከመከለል ይልቅ የቅኝ ገዢዎችን ሥርዓት ያጣ ወሰን ለማክበር ፈለጉ ። በውጤቱም ውጥንቅጣቸው የወጣ አገሮች ተመሠረቱ ፤ ዛሬም ተመሳሳይ ሕዝቦችን በአንድ መንግሥት በጋራ ድንበር ውስጥ ለማሰ ባሰብ የሚያወራ የለም ።

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አሁን ባለው መልኩ ፋይዳ እንደማ ይሰራ ብዙዎቹ የአፍሪካ መሪዎች በግል ያወራሉ ። በአሁኑ ቅርፁ የአፍሪካዊ ማንነትና የአንድነት ሕልም ማስታወሻ ከመሆን አይዘልም ብለው ያምናሉ ። በመጀመሪያ ደረጃ ድርጅቱ የአፍሪካን ክስተቶች ለመቆጣጠርና ተጽዕኖ ለማድረግ ኃይል እንዲኖረው ቻርተሩ መሻሻል አለበት ። በአአድ ዋናው ውሳኔ ሰጪ አካል የመሪዎች ጉባዔ ብቻ መሆኑ ቀርቶ ዋና ፀሐፊውም ከአሁኑ ላቅ ያለ ሥልጣን እንዲሰጠው ያስፈልጋል ። በተለይ በአስቸኳይ ጉዳዮች ላይ ውሣኔ ለመስጠትና ተግባራዊ ለማድረግ ሥልጣን ሊኖረው ይገባል ። በሶስተኛ ደረጃም



አባል ሀገሮች በአንድነት ስም በመሸፋፈንና አንድን አፍሪካዊ መሪም ሆነ አገር በተገቢው ከመንቀፍና ከመገሰፅ ይልቅ ዝምታን በመምረጥ ለአህጉሪቱ አጥፊ የሆነ ተግባር ከመፈፀም ሊታቀቡ ይገባቸዋል ።

የሚያሳዝነው አፍሪካም እንደሌላው ታዳጊ ሶስተኛ ዓለም ራሷን የምትገልጸው በመፈክርና በሰለቹ አባባሎች ነው ። ብዙ የአፍሪካ መሪዎች ብዙ በተናገሩና ጮህ ብለው በገለጡ መጠን የሚደመጡና ተሰሚነት የሚያገኙ ይመስላቸዋል ። ነገር ግን ቃላት መደጋገም ትር ጉም አጥቷል ። በአደባባይ የሚለፈለፈውና በግል የሚነገረው ግንኙነት የለውም ። ሕዝቡ እርስ በርስ መተራረብ እንጅ መወያየት አልጀመ ረም ።

አንዳንዶቹ መሪዎች አገራቸው ከደቡብ አፍሪካ ጋር የደራ ንግድ እያላት በንግግር ግን እንዲህ የሚያደርጉ አገሮች እንዲቀጡ ይለ ፍፋሉ ። የሲሸልስ መሪ በ1979 የአአድ የመሪዎች ዓመታዊ ስብ ሰባ ላይ ይህንኑ ተናገሩ ፤ አገራቸው ግን ንግድዋ ስድሳ በመቶ ከደቡብ አፍሪካ ጋር ነው ። እኚህ መሪ ሥልጣን የያዙት ሁለት ጊዜ በነፃ ምርጫ ያሸነፋዋቸውን እውነተኛ መሪ በመፈንቅለ መንግሥት አስ ወግደው ነው ።

በአአድ ዓመታዊ ስብሰባዎችና ከዚያም ውጭ የአፍሪካ ልዑካን በደቡብ አፍሪካ የሚታየውን ፍትህ የጐደለው የዘረኝነት ሥርዓት ቢኮንኑ እውነት አላቸው ። ነገር ግን በሃያ ዓመት ውስጥ ከሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሕዝቦቻቸው በራሳቸው መንግሥታት እጅ በተገደሉ በት አህጉር እነዚህ ቃላት ምን ያህል ተቀባይነት ይኖራቸዋል ። የኡ ጋንዳው ኢዲ አሚን በሽብር አገዛዝ ሕዝባቸውን እንደ ከብት ሲያርዱ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ አንድ ቃል ሳይተነፍስ የኖረው የአፍሪካ አንድ ነት ድርጅት የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ታጋዩን እስቲቭ ቢኮ ገደለ ብሎ ቢጮህ የቱን ያህል ተቀባይነት ያገኛል?

እንዲያውም የአአድ ዝምታ ለአፍሪካ ደም መፋሰስ አስተዋፅኦ አድርጓል ፤ አበረታትቷል ። አንድ ጊዜ በኡጋንዳ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ሊቀጳጳስ ፌስቴ ኪቪንገር እንዲህ አሉኝ ። "ማለቴ ፣

አአድ በ1975 ጭራሽ በካምፓላ ዓመታዊ ስብሰባውን በማዘጋጀትና አሚንን የዓመቱ የድርጅቱ ሊቀመንበር በማድረግ አሳፋሪ ድርጊት ፈጽሟል ። በስብሰባውም ላይ በደቡብ አፍሪካ ስላለው የሰብዓዊ መብት መረገጥ ጉዳይ ሲወያዩ ከአዳራሹ መቶ ሜትር በማይሞላ ርቀት በአሚን እሥር ቤቶች የማሰቃያ ክፍሎች የኡጋንዳ ዜጎች ጭንቅላት በመዶሻ ይፈለጥና እግሮቻቸው በፋስ ይቆረጡ ነበር ።"

ከአሚን በኋላ ኡጋንዳን የመሩት ፕሬዚዳንት ቢናይስ በ1979 በላይቤሪያ በተካሄደው ዓመታዊ ስብሰባ ላይ "ሰብአዊ መብት ረገጣን በተመለከተ እኛም ከእነሱ ባልተሻለ ሁኔታ ግፍ እየሰራን ሌሎቹን መንቀፍ ጥቅም የለውም" ሲሉ ነቅፈዋል ። አያይዘውም ንጉሠ ነገሥት ቦካሳ በማዕከላዊ አፍሪካ ሪፑብሊክ አክብሮት የነፈጓቸውን ሰማንያ ሕፃናት በመግደላቸው አወገዙ ። ከዚሁ ጋር የኢኩዋቶሪያል ጊኒ የእድሜ ልክ ፕሬዚዳንት ቢዩጎ አንድ ስምንተኛውን የሀገራቸውን ህዝብ መግደላቸውን በመኮነን ተናገሩ ። ቢናይሳ እነዚህን የነቀፉ ቃላት በአግባቡ ሲሰነዝሩ የጉባዔው አዳራሽ በፀጥታ ተሞላ ። አንዳንዶቹም በአዎንታ መልክ ራሳቸውን ይነቀንቃሉ ። ልውካኑ ተደናገጡ ። ከዚያ በፊት አንድ የአፍሪካ መሪ ሌላውን የአፍሪካ አገር በስም ጠቅሶ በሰብዓዊ መብት ረገጣ በስብሰባ ላይ ኮንኖ አያውቅም ። ቢናይሳ ንግግራቸውን ሲጨርሱ አንድም የአድናቆት ጭብጨባ አልነበረም ። "ወይ ጠጥቷል ፣ ወይም ከሃዲ ነው" በማለት አንድ የቤኒን ተወላጅ በእረፍት ሰዐት ሲያጉተመትሙም ሰማሁት ። ቢናይሳ ግን ሁለቱንም አልነበሩም ፤ ሆኖም ንግግሩ የመጨረሻቸው ሆነና ዳግም ለአአድ ስብሰባ ለመገኘት ዕድል ሳያገኙ ከአሥር ወራት በኋላ ከሥልጣን ተፈናቀሉ ።

አአድ ምናልባት አንድ ቀን አባላቱን ከሚያስተባብሩት ጉዳዮች ይልቅ የሚከፋፍሉት ነጥቦች እንደሚበዙ ለማመን ወኔ ይኖረው ይሆናል ። ሂስና በግልፅ መወቃቀስ ሊያናጉ የመቻላቸውን ያህል ጤናማና ገንቢ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለማመን ይችል ይሆናል ። ልዩነቶች ያሏቸው አገሮችም የጋራ ጥቅማቸው አደጋ ላይ የሚወድቅ ከሆነ በኅብረት እንደሚቆሙ ድርጅቱ አንድ ቀን ዋስትና ይሰጣው ይሆናል ።



የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በ1963 አአድ ሲመሠረት (ከሥልጣን ከመባረራቸው ከአሥራ ሁለት ዓመት በፊት) ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር ፤ "የምንሻው አንድነት የሚመጣው ቀስ በቀስ ነው. . ." ሲሉ ተንብየዋል ። ዛሬ የዚያን አስተያየት ትክክለኛነት የሚያስተባብል የለም ።

## ምዕራፍ ስድስት

# ተደጋጋሚ መፈንቅለ መንግሥታት

"አምላካችሁና አስተማሪያችሁ እኔ ነኝ ። የአምላክ መንገድ እኔ ነኝ ። ጨለማውን የማበራ እኔ ነኝ ። ከአሊ ሶሊህ ሌላ አምላክ የለም ።"

አሊ ሶሊህ
(የኮሞሮስ ፕሬዚዳንት ለሕዝባቸው ንግግር ሲያደርጉ)

በአፍሪካ የሚካሄዱት መፈንቅለ መንግሥታት አስገራሚ ባህርይ የቁጥራቸው ብዛት ብቻ ሳይሆን በሕዝቡ ሕይወት ላይ የሚያስከትሉት ለውጥ ኢምንት መሆኑ ነው ። ብዙውን ጊዜ መፈንቅለ መንግሥት የሚደረገው ማኅበራዊ ፍትሕ በማስገኘት ስምና የኢኮኖሚ ተሃድሶ በማምጣት ሰበብ ይሁን እንጅ በአብዛኛው በሁለቱም ዘርፎች መሻሻል ሲያስገኙ አይታይም ። ስለዚህም አንድ አፍሪካዊ ሰው መንግሥት መገልበጡን በሬዲዮ ሲሰማ ክስተቱን የሚወስደው እንደተለመደ ተራ ነገር ነው ። ምክንያቱም ቀደም ሲልም በተደጋጋሚ የሰማውና ሕይወቱን የማያሻሽልለት መሆኑን ስላየው ነው ። ለውጡን ያለክርክር ይቀበላል ፤ ለተሻለ ነገርም ተስፋ ያደርጋል ፤ እንደተነገረውም ይፈጽማል ።

በኢትዮጵያ የኃይለሥላሴ ፊውዳላዊና አፍቃሪ ምዕራብ መንግሥት በማርክሲስትና ገዳይ በሆነ የወታደሮች ቡድን እንደተገለበጠው ዓይነት በእርግጥ ሀገሮች ሥርነቀል የፖለቲካ ለውጥ ወደሚያመጡ አቅጣጫዎች ሊያመሩ ይችላሉ ። ነገር ግን ከመሬት ይዞታ

ፖሊሲ ለውጥ በስተቀር ገበሬው በአዲስአበባ መንግሥት ስለመለወጡ የሚያውቅበት ሁኔታ አይኖርም ነበር ። ብዙውን ጊዜ የመንግሥት ለውጦች የገጠሩን ሕይወት እስከዚህም አይለውጡም ። በገጠሬውና በከተማው መካከል ያለው ሰፊ ልዩነት በአፍሪካ መሠረተ ሰፊ ሕዝባዊ አመፅ ለምን እንደሌለ ይገልጣል ። መፈንቅለ መንግሥታቱ ሁሉ ከላይ አካባቢ የነበሩ ባለሥልጣኖች መለወጥ ብቻ ናቸው ። ይህ የመሪዎች መፈነቃቀል በአፍሪካ በጣም ስለተለመደ በምዕራቡ ዓለም በምርጫ የሚለዋወጠውን መንግሥት ዓይነት ሆኗል ። ልዩነቱ በአፍሪካ የሚለወጡት ባለሥልጣኖች ሲገደሉ ወይም ወደ እሥር ቤት ሲታጐሩ ፣ በምዕራቡ ዓለም በምርጫ የሚሸነፉት ግን ምቾት ባልተጓደለበት ሁኔታ ከሥልጣን የሚሰናበቱ መሆኑ ነው ።

በሴራሊዮን በ1967 ጄኔራሎቹ የሲቢሎችን መንግሥት አውርደው ሥልጣን ወሰዱ ። ከጥቂት ወራት በኋላ እነሱም በሌሎች የጦር መኮንኖች ተፈንቅለው ወደቁ ። እነዚህም ብዙ ሳይቆዩ በሃምሳ አለቆች አመፅ ተወገዱ ። ቤኒን የምትባለዋ አገር ደግሞ ከ1963—1972 ባሉት የአሥር ዓመታት ጊዜ ውስጥ አምስት ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ፣ አሥር የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች ፣ አሥራ ሁለት መንግሥታትና ስድስት ሕገመንግሥት አስተናግዳለች ። በጋና በ1979 የበታች መኮንኖች "የሕሊና ለውጥ" በሚል ስያሜ ሶስት መሪዎችን ገደሉ ፣ ዘላቂ ለውጥ ግን አላመጡም ። ገዳዮቹ ጠመንጃቸውን እንዳስቀመጡ ጥቁር ገበያውም ቀጠለ ፣ ጉቦም ዳግም አንሰራራ ፣ ወደጐረቤት ሀገር ካካዎ በኮንትሮባንድ ማጋዘም ቀጠለ ። በአፍሪካ ከነፃነት ወዲህ አሥራ አምስት አገሮች አንዳንድ ጊዜ መፈንቅለ መንግሥት አጋጥሟቸዋል ። ሌሎች አሥራ ሶስት አገሮች ሁለትና ሶስት መፈንቅለ መንግሥታት ተካሂዶባቸዋል ። እስከ 1983 ሃምሳ መንግሥታት ተገልብጠዋል ። በዚህም ሃያ ስምንት ሀገሮች መፈንቅለ መንግሥት ቀምሰዋል ። ሕዝቡም ኑሮው የተጐሳቆለ ስለሆነ ለውጦቹ የተሻለ አማራጭ የሚያስገኙለት እየመሰለው ብዙዎቹን የሥልጣን ንጥቂያዎች በደስታ ተቀብሏቸው ነበር ።

በጥቁር አፍሪካ ከ1957 እስከ 1962 ድረስ ለመጀመሪያዎቹ



ስድስት የነፃነት ዓመታት መፈንቅለ መንግሥት ስላልነበረ የፖለቲካ መረጋጋት ይታይ ነበር ። በ1963 የቶጐ የመጀመሪያ ፕሬዚዳንት የነበሩት ሲልባነስ ኦሊምፒዮ ጥገኝነት ለመጠየቅ አሜሪካን ኤምባሲ ሊገቡ ሲሉ በጥይት ተገደሉ ። እኚህ ሰው በአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆን ኤፍ ኬኔዲ የተደነቁ የአፍሪካ መሪ ነበሩ ። ኦሊምፒዮ ለሀገራቸው ዕድገት ያስገኙና በፖለቲካም ለዘብተኛ መሪ ነበሩ ። ነገር ግን ሁለት መቶ ሃምሳ ለሚሆኑት ወታደሮቻቸው ደመወዝ ለመጨመር ስላልፈቀዱ ብቻ ሕይወታቸውን መክፈል ነበረባቸው ። ወታደሮቹ በጥቂት ተኩሶች በቀላሉ ሥልጣን መውሰዳቸው ገረማቸው ። ከዚያ በፊት መፈንቅለ መንግሥት የማያውቀው አፍሪካም ተደነቀ ። ከዚያም ለተከታታይ የግልበጣ ሤራዎች በሩ ተከፈተ ። በኦሊምፒዮ ሞት በሠለጠነው ዓለም ተወዳዳሪ የማይገኝለት አህጉራዊ አለመረጋጋት ተከተለ ።

አፍሪካ እንደሌሎቹ ለምሳሌ እንበል እንደ ቻይና የመንግሥት አመራር ረጅም ልምድ ስለሌላት መፈንቅለ መንግሥት በተደረገ ቁጥር አስተዳደራዊ አሠራሮች ሁሉ ይናጋሉ ። ታዲያ የባሰ ከሆነ በአፍሪካ ለምን መፈንቅለ መንግሥት በተደጋጋሚ እንዲካሄድ ይደረጋል? ምክንያቱ በከፊል ከታሪክ ጋር የተያያዘ ነው ። ብሔራዊ ዓላማን በሚያስተጋቡ ኃይሎች ውስጥ የሰረፀው የዘረኝነት ፣ የቋንቋ ልዩነት ፣ የቅኝ ገዢዎች ያስመሯቸው ድንበሮች አግባብ ያለመሆን ፣ የኢኮኖሚው መሠረት መዋዠቅ ፣ ለዚህ የሚጠቀሱ ናቸው ። ከፊሉ ምክንያት ደግሞ የመሪዎችን ባህርይ የሚያንፀባርቅ ነው ።

የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች በራሳቸው ባለመተማመን የሕዝብን የነፃ አስተያየት መድረክ ዘጉት ። የተለየ አመለካከት ያላቸውና ተቃዋሚዎች ተገደሉ ፣ ታሠሩ ፣ ወይም ከአገር እንዲሰደዱ ተደረጉ ። ጋዜጦችና ሬዲዮኖች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ዋሉ ። ለፕሬዚዳንቱ ታማኝ ያልሆኑ (የፈለገውን ያህል አጥፊ ቢሆንም) እንደከዳተኛ ተቆጠሩ ። ያለመስማማቱ እያደገ ሥጋት እያየለ ሄደ ። እያንዳንዱ ሀገር በእንፋሎትና በታመቀ አየር የሚያበስል ብረትድስት ዓይነት ሆነ ። ከእሳቱ ቢያመልጥ ከእንፋሎቱ ማምለጥ አልተቻለም ። ታዲያ

የታመቀው እንፋሎት ከልክ በላይ ሲሆን የማይቀረው ፍንዳታ ይከሰታል ።

ቅኝ አገዛዝ የግድ መረጋጋትን አረጋግጦ ቆየ ። ቀጣይነት ላለው ሕግና ሥርዓት ምልክት ነበር ። ያ ዘመን ሲያከትም ጠንካራ ማዕከላዊ አመራር ጠፋ ። ኃይል ያለው ወታደሩ አካባቢ ብቻ ሆነ ። ያልተማሩና ለሥልጣን የቋመጡ መሪዎች በጠመንጃ አፈሙዝ መሪነቱን ነጠቁ ። የጦሩ ክፍል ጊዜ እየጠበቀ መንግሥት በመገልበጥ የሚመስለውን ዓይነት አስተዳደር መለማመጃ አደረገው ።

የአውሮፓ ኃያላንም በአፍሪካ ላይ የማይሰራ ሥርዓት ለመጫን ወደኋላ አላሉም ። የሸንጐ ዴሞክራሲያዊ አሠራር ለአፍሪካ ቅንጦት ነበር ። ይህ የወረሱት የአመራር ሥልት ሲከሽፍ ገሸሽ አደረጉት ፤ ሌላ አማራጭ መንገድ ግን አልቀየሱም ። ስለ አሮጌው ሕግ ሳይረዱ አዲስ ሕጐች ለማርቀቅ ሞከሩ ። የመጀመሪያው መፈንቅለ መንግሥትም ለተከታዩ ግልበጣ መንገድ ከመጥረግ በቀር የፈየደው ጉዳይ አልነበረም ።

በአፍሪካ ሥልጣን የያዘው ሰው በፈቃደኝነት አይለቅም ። በምዕራቡ ዓለም አንድ ፕሬዚዳንት ሲያጠፋ ክፉኛ ይነቀፍና ተጋልጦ ይወገዳል ። ጠቅላይ ሚኒስትርም በተከታዮቹ ዘንድ እምነት ካጣ ይወርዳል ። በኬንያ ይህን የመሰለ እምነት ያልተጣለበት መስሎ ከታየ እንደገና ሕዝቡ አስተያየቱን እንዲሰጥና ምርጫ እንዲካሄድ የሚፈቅድ ሐረግ በሕገመንግሥቱ ውስጥ ተጠቅሷል ። ነገር ግን በአንድም የአፍሪካ አገር ተግባራዊ ሆኖ አያውቅም ። ፕሬዚዳንቶች በጉልበት የእድሜ ልክ ሆኑ ። አንዱ እንዲያውም ንጉሠነገሥት ተባሉ ። መለወጥ የነበረባቸው ጊዜ ብዙ ቢያልፍም በኃይል ተፈንቅለው እስከተገደሉ ወይም እስከተባረሩ ድረስ የመግዛት መብታቸው ከላይ የተሰጣቸውና የማይገሰስ አድርገውት ይቆያሉ ።

በጣም ትንሽና ድሃ ሃገር የሆነችው ኮሞሮስ ነፃ በወጣች በሃያ ስምንተኛው ቀን የመጀመሪያው መፈንቅለ መንግሥት ጐበኛት ። በተከታታይም በየዓመቱ ተመሳሳይ ሙከራዎች ተደርገው ከሸፉ ። በሙከራዎችም ሕዝብ አለቀ ፤ እሥር ቤቶች ተጣበቡ ። መረጋጋት ስለ



ጠፋ ቅጥረኛ ወታደሮች በማስመጣት ሥልጣን ለመንጠቅ ሳይቋር ተሞከረ ። የነገውን ለመተንበይ ባለመቻል ሁሉም ብሔራዊ ስሜቱ ደብዝዞ በሕልም ዓለም የመኖር ያህል ሆነ ።

አሊ ሶሊህ ኮሞሮስ ነፃ ከወጣች ከስድስት ወራት በኋላ ሥልጣን ሲወስዱ ጥሩ መሪ መስለው ታይተው ነበር ። በኋላ ግን የእብድ ሰው ሥራ ፈጸሙ ። ምን እንደዚያ እንደለወጣቸው በውል ባይታወቅም ምናልባት አደንዛዥ ዕፅ በመውሰድ ወይም በመጠጥ ማብዛት ያለዚያም የፕሬዚዳንታዊ ኃላፊነት ከችሎታ በላይ ስለሆነባቸው ላይሆን አይቀርም የሚል መላ ምት አለ ። አንጐላቸው ዞረ ፤ ብሔራዊ ግብ ብለው ያለሙት ደበዘዘ ፣ ሀሳባቸው ሁሉ የግል ሥልጣንና ክብራቸውን ለማጉላት ብቻ ሆነ ። ምሁራንና ሂስ የሚሰነዝሩ ሁሉ ለሞትና ለእሥር ተዳርገው ደም መጣጭ አድርባዮች ብቻ በዙሪያቸው ቀሩ ።

በአንድ ወቅት አንድ የአሠራር ሥልት በሌላ ወቅት ደግሞ ሌላ ነገር እየሞከሩበት ሕዝቡንና አገሪቱን እንደአሻንጉሊት ተጫወቱባት ። አንድ ቀን 3500 የሚሆኑትን ጠቅላላ የሀገሪቱ የመንግሥት ሠራተኞች ከሥራ አባርረው ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ወጣቶችን ተኩ ። የኮሞሮስ ሕዝብ ብዛት አራት መቶ ሺህ ብቻ ነው ። ወጣቶችን የተኩት የምለውን ተቀብለው የቻይና መሰል ሶሻሊዝምን ለመመሥረት ያግዙኛል በሚል ነበር ። ወሎ አድሮ ደግሞ ከአሥራ አራት ዓመት በላይ ያለ ሁሉ የመምረጥ መብት እንዳለው አስታወቁ ። ሰን በትበት ብለውም ከእምላክ የተላክሁ ነቢይ ነኝ አሉ ። ቀጥለውም የቆዩ መዛግብትን በሙሉ አቃጥለው ሆቴሎችን በሙሉ ዘጉ ። ከታክሲ መኪና እስከ ዳቦ መሸጫ ሁሉንም የግል ንብረት ወረሱ ። የቻይና አማካሪዎችን በማስመጣትና የግል ጠባቂዎቻቸውን ከታንዛንያ በማድረግ የሚሰሩት መላው ጠፋቸው ። ሃይማኖትን እንደ እርግማን በማውገዝ ሴቶች እስላሞች እንዳይሸፋፈኑ አዘዙ ። አንድ ቀን መስጊድ ውስጥ ገብተው አማኞችን በመሳደብ “እምላክ ካለ እስቲ ጥሩትና ይምጣ” በማለት አፌዙ ።

አንዳንድ ጊዜ ለተከታታይ ቀናት በቤተመንግሥታቸው ውስጥ ከፍቅረኞቻቸው ጋር እየተሞነሸነሹ የሀገርን ጉዳይ ወደ ጐን ትተው

ይቀመጣሉ ። አንድ ሰሞን ሚስቶቻቸውን ፈቱና ወጣት ልጃገረዶችን ሁለተኛ ፎቅ በሚገኘው የቤተመንግሥታቸው መኝታ ቤት እየሰበሰቡ ውስኪ በመጠጣት ፣ ሀሺሽ በማጨስ ፣ ፊልም በማየት ፣ ሌሊቱን ያነጉ ጀመር ። ቀንም እንዲሁ በዚህ መስሉ መስመር የለቀቀ ወራዳ ተግባር በዞባቸው ፣ ዓይናቸው ደም ጉርሶና ራሳቸውን ዘንግተው መዋል ቀጠሉ ።

በሞሮኒ ከተማ ጉዳናዎች የወጣት ብርጌድ የሚባሉ የማይም ወጣቶች ጥርቅሞች እየተዘዋወሩ ለራሳቸው ስላልገባቸው አብዮት ዞብ በመቆም ሕዝቡን ያሰቃያሉ ። በጡንቻ ከማስገደድ በስተቀር የሚከተሉት ርዕዮተዓለም የለም ። የተቃወማቸውን ይገድላሉ ፣ ያስፈራራሉ ፣ ሴቶችን ያለፈቃዳቸው ለወሲብ ያስገድዳሉ ። ጥቃቅን ጥፋት ፈጸሙ የሚባሉ ምሁራንን ፀጉራቸውን ላጭተውና ፊታቸውን ኝጉርጉር ቀለም ቀብተው ሕዝብ በቀሰበሰበባቸው ጉዳናዎች በማዘዋወር መሳለቂያ ያደርጓቸዋል ። በዚህም ጊዜ ምሁራኑ ፈፀሙ የሚባለውን "ወንጀል" በድምፅ ማጉያ እየገለጡ በየአደባባዮች በማዞር አሳፋሪና አሳዛኝ ድርጊት ይፈፅሙባቸዋል ። በቻይና የባህል አብዮት ዘመን የተከናወነው ዓይነት መሆኑ ነው ።

አንድ ጊዜ አንድ የጀርመን ዲፕሎማት ለኮሞሮ እርሻ ልማት የሚሆን ገንዘብ ከቦን መንግሥት ስለሚሰጥበት ሁኔታ ለመነጋገር በአውሮፕላን ከማዳጋስካር ሞሮኒ ሲደርሱ አስገራሚ ትርኢት ተመለከቱ ። በዚያ ዕለት በአውሮፕላን ማቢያው አንዳንድ ጥፋት ፈጸሙ የሚባሉ ሰዎች በሰልፍ ሆነው በጅራፍ እየተነዱ ሕዝብ እንዲሳለቅባቸውና እንዲተፋባቸው እየተደረጉ ነበር ። ዲፕሎማቱ በመገረም ተመለከቱና የጠበቃቸው ተቀባይ ስላልነረ በአንድ አሮጌ የፈረንሳይ ዚታዎ ተሳፍረው ወደ ውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ሄዱ ። በዚያም እንደደረሱ ከሁለት ባለሥልጣኖች ነን ባዮች ጋር ውይይት ጀመሩ ። ባለሥልጣንኖቹ በግምት የአሥራ ሰባት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ናቸው ። ከዚያም በቀር ማንበብና መፃፍ አይችሉም ። ዲፕሎማቱ "የሚያስገርም ሁኔታ" በማለት ከጥቂት ሰዐት ቆይታ በኋላ ይዞአቸው በመጣው ቻርተር አውሮፕላን ወደ ሀገራቸው ተመለሱ ። የጀርመን ርዳትም የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ ።



በአንድ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትሩ አባስ ዮሴፍ ወኔ አገኙና "አገሪቱን በዚህ መልኩ ለአቅመ አዳም ባልደረሱ ልጆች ልናስተዳድር አንችልም ! አሁን እንደሚታየውም ይህን ያህል የበዛ ሕዝብ በየእሥር ቤቶች አጉረን ልንቀጥልም አይገባም" ሲሉ ለሶሊህ አሳሰቡ ። "ሕዝቡ አብደዋል እያለን ነው ! አገሪቱም ሽባ ሆና እየተሽመደመደች ነው" በማለት አጠንክረው አማረሩ ።

"ዝምበል!"አሉ ሶሊህ !'የታየኝ ትልቅ ጉዳይ አለ ! የወደፊት እድላችንን የምወስን እኔ ነኝ ያልሁትን ዘነጋኸውን!' በማለት አጉረመረሙ ። በማግሥቱ የሰባ አምስት ዓመት ዕድሜ ያላቸው የጠቅላይ ሚኒስትሩ እናት ባልተገለጠ ምክንያት ታስረው ጆንያ ለብሰው በመዘዋወር በአደባባይ የሕዝብ መሳለቂያ ከተደረጉ በኋላ ወደ ወህኒ ወረዱ ።

ሶሊህ የታያቸው አንድ ሕልም ነበር ። አንድ ሌሊት መጥፎ መጥፎ ሕልም አባነናቸው ። ሕልሙም አንድ ሰውና አንድ ውሻ ሊገድሏቸው ሲያሳድዷቸው የታያቸው ነበር ። ላብ በላብ ሆነው ባነኑና ቁርሳቸውን በልተው ብራንዲ ከጠጡ በኋላ አንድ ድንጋጌ አወጡ ። በዚህ ፕሬዚዳንታዊ ድንጋጌ በመላ ኮሞሮስ ያሉ ውሾች በአስቸኳይ እንዲገደሉ አዘዙ ። የወጣት ብርጌዶች በዕለቱ ድንጋጌውን ተግባራዊ በማድረግ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ውሾችን ገደሉ ።

ለዚህ ብሔራዊ እብደት የኮሞሮስ ሕዝብ የሰጠው ምላሽ ዝምታ ነበር ። ሕዝቡ በዝምታ ማለፉ ለምዕራቡ ዓለም የሚያስገርም ቢሆንም በአፍሪካ ሕዝቡ የመሪዎቹን የጭካኔ ርምጃ ስለሚፈራ ብዙውን ነገር በዝምታ ማለፉ የተለመደ ሆኗል ። ፕሬዚዳንቶች የፈለጉትን በማድረግና በመግደል ይገዛሉ ፣ በመቃወም ድምፅ የሚያሰማና የሚነሳሳ ሕዝብ የለም ። ጠቅላይ ግምጃ ቤቱን ዘርፈው ባዶ ቢያስቀሩት ፣ በሺህ ዜጎች ደም ቢታጠቡ ፣ እንደ ጥንቱ ነገሥታት ፈላጭ ቆራጭና ከሕግ በላይ ቢሆኑ የሚናገራቸው የለም ፤ የሕዝቡ ታዛዥነት አይጓደልባቸውም ፤

ጋያሉ ጌታቸው ፍርሃት ነው ። በሥልጣን መባለግና ዝርፊያ ሲበዛ የሕዝብ እንባ ሞልቶ ሲፈስ ባልተጠበቀ ሁኔታ ፕሬዚዳንቶች አደጋ ላይ ይወድቃሉ ። ሥልጣናቸው ብቻ ሳይሆን ሕይወታቸውም አይተርፍም ። በሚያዝያ ወር 1978 እ.ሲ ፣ ሶሊህን ያጋጠማቸው ይኸው ነው ።

ሶሊህ ቀደም ሲል ሥልጣን ለመያዝ ባካሄዱት መፈንቅለ መንግሥት በቅጥረኝነት የረዳቸው አንድ ዝነኛ ፈረንሳዊ የጦር መኮንን ቦብ ዴናርድ የሚባል ነበረ ። ይህ ሰው የሶሊህ የአብዮት አቅጣጫ ስላልጣመው ወደ ፈረንሳይ ተመልሶ ነበር ። በኋላም አንድ የኮሞሮስ ከበርቴና የቀድሞው የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት የነበሩት አህመድ አብደላ ለዳግመኛ መፈንቅለ መንግሥት እንዲተባበራቸው ጠየቁት ። ከበርቴው ሞሐመድ አህመድና የበፊቱ መሪ አህመድ አብደላ ሁለት ሚሊዮን ዶላር ሊሰጡት ቃል ገቡለትና ቦብ ፣ ዴናርድ ሥልት ማውጣት ጀመረ ።

ዴናርድ ሰላሳ የማይሞሉ የቤልጅግና የፈረንሳይ የቀድሞ ወታደሮችን በቅጥረኝነት አሰባስቦ ከፈረንሳይ በመርከብ በመንቀሳቀስ ሳይታወቅ በሌሊት ከሞሮ ደሴት ገባ ። በአማካሪነት ከአሊ ሶሊህ ጋር ቀርቶ የነበረው የቀድሞ ባልደረባው ጅን ጉልሰው አሳሳች ምክር በመስጠት የፕሬዚዳንቱ ጦር ወደሌላ አቅጣጫ እንዲንቀሳቀስ አደረገ ። ከዚያም በሌሊት የቦብ ዴናርድ አፋኝ ቡድን አባላት ፊታቸውንና እጃቸውን ከሰል በመቀባት ሲነጋጋ ሲል በልዩ ልዩ አቅጣጫ የአሊ ሶሊህን መኖሪያ ከበው በመግባት በቁጥጥር ሥር አዋሉዋቸው ። ይህን ለማከናወን የወሰደው ሶስት ሰዐት ብቻ ሲሆን ፤ የሞቱ የኮሞሮ ወታደሮች ቁጥርም አሥር ነበር ። ሰላሳ ቅጥረኛ ወታደሮች አገሪቱን በእጃቸው አስገቡ ። በቅጥረኞቹ ላይ የደረሰው ጉዳት አንድ የቁርጭምጭሚት ወለምታ ብቻ ነበር ። ሲነጋ ዴናርድ ወደ ፓሪስ ስልክ ደውሎ ውጤቱን ለአብደላ ገለጠላቸውና መምጣት እንደሚችሉ አስታወቃቸው ።

አብደላ ከተመለሱና በኋላ የሕዝብ አቀባበል ሥልጣን ከጨበጡ ከሁለት ሳምንታት በኋላ ቅጥረኞቹ አሊ ሶሊህን ገደሏቸው ። የተሰጠውም ምክንያት የማምለጥ ሙከራ ሲያደርጉ ነው የሚል ነበር ።



ከዚያም ዴናርድ ሬሳቸውን ሳይከፈን በግልፅ ላንድሮበር ከኋላ ጭነው ለሕዝብ እያሳዩ በከተማው በማለፍ ወጣ ብለው ለሚጠብቁት የሟቹ ፕሬዚዳንት እናት ፣ እህትና ሌሎች ዘመዶች በማስረከብ ብዙ ጫጫታ ሳያበዙ እንዲቀብሯቸው ትእዛዝ ሰጥቶ ተመለሰ ።

አፍሪካ አስደንጋጭና አስፈሪ ክስተት አጋጠማት ። ነጮች እንደገና ዛሬም የጥቁር ሕዝብን የወደፊት ዕድል ወሳኝ ሆነው ብቅ አሉ ። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ድርጊቱን በመቃወም ለአዲሱ የኮሞሮ መንግሥትና ለአብደላ እውቅና ነፈገ ። በድርጅቱ ዓመታዊ ስብሰባ እንዳይሳተፉም ከለከለ ። በኮሞሮስ የቅጥረኞች መኖር በቁስል ላይ ጨው እንደመነስነስ በመሆኑ የአፍሪካ ሉዐላዊነት ማፌኛያ ሆነ ። የአፍሪካ መንግሥታት የወደፊት ዕድላቸውን ለመወሰን የተሳናቸው መሰሉ ታየ ። የሲሸልሱ ፕሬዚዳንት አልበርት ፣ ሬኔ በሁኔታው በመቆጨት ይመስላል “እነዚህ ሰዎች ጓዛቸውን ጠቅልለው መባረር አለባቸው”በማለት ተናገሩ ። ይሁንና ራሳቸው ሬኔ ከዓመት በፊት ሥልጣን የጨበጡት በታንዛንያ ጥቁር ቅጥረኛ ወታደሮች ርዳታ ነበር ። (ጥቁሮች በመሆናቸው ብቻ አእድ ተቀብሎታል ።)

ዴናርድ በበኩሉ በመገረም “የአፍሪካ አገሮች ምን እንዳስቆጣቸው አላውቅም ፤ እኔ የምኖረው ሩቅ አገር እንደሆነ ያውቃሉ ። አሁንም ሂድ ካሉኝ እሄዳለሁ ። ማን ያውቃል ፣ ወደፊት ደግሞ አንዱ አገር እንደገና ይፈልጉኝና ይጠሩኝ ይሆናል” በማለት ተናገረ ።

“እድሜ ልኬን ትክክል ያልሆነ ዓላማ በመደገፍ ስዋጋ መኖሬን ሕዝብ ሲከሰኝ ቆይቷል ። አሁን ግን አገሩን ያጠፋ እብድ ፕሬዚዳንት በማስወገድ ትግል ተሳተፍሁ ። ሕሊና ያለው ፀረ–ኮሚኒስት መሪ ቦታውን እንዲይዝ አደረግሁ ። አሁን ትክክለኛ ጉዳይን ደግፌ ተሰልፌያለሁ ። ሕዝቡ ግን ዛሬም መጥፎ እንደሰራሁ ሁሉ ይከሰኛል ። አፍሪካ ለምን እንዲህ ውለታ ቢስ እንደሆነች አይገባኝም” ሲል ዴናርድ ተችቷል ።

ለኮሞሮ ሕዝብ ግን ዴናርድ ነፃ አውጭ ጀግና ነበር ። ከዕብድና ጨካኝ መሪ ገላግሏቸዋልና ። ባለፈበት መንገድ ሁሉ ይጨበጨብለ

ቃል ፤ እሱም ሰላምታ እየሰጠ ያልፋል ። የእሱ ምስል ያለበት ካናቴራ መሸጥ ጀመረ ። እሺን ለመጨበጥ የማይሯሯጥ ወጣት የለም ፤ አዛውንቶች ሳይቀር መንገድ ይለቁለታል ። አዲሱ መንግሥትም ከፍተኛ ሥልጣን ሰጠው ።

"አንድ ሰው አንድ ምቹ ደረጃ ላይ ሲደርስ አንድ ቦታ ረግቶ መኖር የሚመርጥበት ጊዜ ይመጣል ። እኔም እዚህ ኮሞሮስ ውስጥ መብላት ፤ መጠጣት ፤ መተኛት ፤ ማፍቀር ችያለሁ ። ሕዝቡ እስከፈለ' ገኝ ድረስ መቶ ሺህ ኩባውያን ቢመጡ ሊያስወጡኝ ይቸግራቸዋል' በማለት ዴናርድ አስገነዘበ ።

በእርግጥም ዴናርድ ቦታውን አግኝቷል ። የኮሞሮስ የዜግነት መብትና የኮሎኔልነት ማዕረግ ተቀበለ ። ስሙን ለውጦ ሙስጠፋ ማሀጁ ተባለ ። ጠመንጃውን አስቀምጦ በሰላም መኖር መጀመሩን አስታወቀ ። አንዲት የሆቴል ቤት አስተናጋጅ አገባና ኑሮውን በዚያው መሠረተ ።

ቅጥረኞቹ ቁልፍ የሚኒስትርነት ቦታዎችን ወሰዱ ። የመከላከያና የመገናኛ ሚኒስትርነቱን ያዙ ። የፖስታና የስልክ አገልግሎቶችን አስጀመሩ ። ጤና ጣቢያዎችንም ከፈቱ ። አዲስ ጦር ሠራዊት አቋቋሙ ። መኖሪያቸውንም ቀድሞ የፈረንሣይ ቅኝ ገዢዎች በነበሩባቸው ሰፈሮች አደረጉ ። በአፍሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ ነፃ የወጣች ሀገር በአውሮፓ ቅጥረኞች አመራር ትተዳደር ጀመር ።

እኔ ኮሞሮስ የደረስሁት ወዲያው አሊ ሶሊህ እንደተገደሉ ነበር ። በአፍሪካ እንደተለመደው በጥቂት ሳምንታት ውስጥ የሕዝቡ አስተሳሰብ ተቀይሯል ። በአውሮፕላን ጣቢያው በትህትናና ሞቅ ባለ አቀባበል ያስተናገዱኝ የኢሚግሬሽን ሠራተኞች ከወር በፊት የውጭ ጋዜጠኞችን ይደበድቡና ያስሩ የነበሩ ሰዎች ናቸው ። ዛሬ ስለለውጥ አስፈላጊነት የሚናገሩ የኮሞሮስ ባለሥልጣኖች ቀደም ሲል የሶሊህን አምባገነናዊ አመራር ሲደግፉ የነበሩ ናቸው ። ዛሬ የሶሊህን አመራር አረመኔነት በይፋ የሚያስተጋቡ ወጣቶች በእሱ ዘመን ሕዝቡን ሲያሰቃዩ የነበሩና በአደባባይ በምሁራን ሲሳለቁ የነበሩ ወጣቶች ናቸው ።



እንዴት በቅጽበት እንዲህ ሊቀየሩ ይችላሉ፤ ብዬ የጠየቅኋቸው ሰዎች በመገረም ትከሻቸውን ያነቃንቁና "እኛ የታዘዝነውን ማስፈጸም ብቻ ነው" ይሉኛል ።

ኮሞሮስ በአህመድ አብደላ አመራር መልካም አቅጣጫ ያዘች ። የተወረሱ ተቋሞች ተመለሱ ። ከፈረንሳይ ጋር ግንኙነቷን አጠበቀች ። ነፃ ምርጫ ተካሄደ ። ወጣቶች ትምህርት ጀመሩ ። የመንግሥት ሠራተኞችም ሥራ ቀጠሉ ። ፕሬዚዳንቱን ለማነጋገር ጥያቄዎችን አዘጋጀሁና ቀጠሮ ያዝሁ ። በቀጠሮው ቀን ሾፌራቸው አንድ ሰዐት ዘግይቶ መጣ ። ጥይት በበሳሳት ሬኖ መኪና ይዞኝ ሄደ ። በረንዳው ላይ አንድ ጠና ያሉ ሰው ተቀምጠዋል ። እሳቸው ዘንድ እንዳቀረበኝ ሰላምታ ሰጠሁና "ዘግይቼ ስለመጣሁ ፕሬዚዳንቱን ይቅርታ ይጠይቁልኝ" አልኳቸው ። "አያስፈልግም ፤ እኔው ነኝ ፕሬዚዳንቱ" በማለት አብደላ መለሱልኝ ።

ከባህሩ ጥግ ድምፅና ከዘምባባ ዛፎች የነፋስ እንቅስቃሴ በስተቀር ሌላ የሚሰማ በሌለበት መኖሪያቸው ቃለምልልሱን ቀጠልን ። የእሳቸው መፈንቅለ መንግሥት እውነተኛ ዲሞክራሲን ለማምጣት ለመጀመሪያ ጊዜ በአፍሪካ የተደረገ እንደሆነ ይናገራሉ ። "አሁንም በርዕዮተዓለም ካልተጠመድን በስተቀር ደሴቶቻችን ሰላም የሰፈነባቸውና የበለፀጉ ይሆናሉ ። ከውሽንፍር በኋላ ፀጥታ አለ ። የዛሬው ሁኔታ ነፃነታችንን እንደገና የመጨበጥ ያህል ነው" አሉኝ ።

ቦብ ዴናርድን በተመለከተ የኮሞሮስ ሕዝብ እንዲኖር ፈቅዶለታል ። ነገር ግን አፍሪካውያን ስለማላሉትና ብዙ ችግር የሚያስከትል ስለሆነ ኮሞሮስ እንዳትገለል የግድ መውጣት ነበረበት ። በዚህም ዴናርድ ወደ ፈረንሣይ ለመመለስ ተስማማ ። አብደላም ከፍተኛ የወጭ ግብዣ አደረጉለት ። በዚህም ላይ ባደረጉት ንግግር "ማንም ምንም ይበል አንተ ብሔራዊ ጀግናችን ነህ ። በኩራት ልትራመድ ይገባሀል ። ወደ ኮሞሮስ ለመምጣት በፈለግህ ጊዜ ሁሉ በሩ ክፍት ነው ። በቱሪስት መልክ መምጣት ትችላለህ" በማለት አሰናበቱት ።

በነጋታዉ ቀን ዴናርድ ከኮሞር ያገባትን ሚስቱን ተሰናበተና ቀደም ሲል በሌላ ወርኀት ያገባትን ዛየራዊ ሚስት ይዞ ወደ ፓሪስ ተመለሰ።

በአንድ ወቅት የሲሸልስ ፕሬዚዳንት የነበሩት ጀምስ ማንሀም ሲናገሩ ፤ "የአፍሪካ አመራር ግራ የገባው ነው ። አንዳንድ አሳፋሪ ክንዋኔዎች አሉ ። በየትም ሀገር ጢመንጃና የተከፉ ሕዝቦች አሉ ። ከነፃነት በኋላ የጠበቁት ተስፋ በብዙ አገሮች ባዶ ሆኖ ቀርቷል ። እውነቱን ልንገርህ ፣ በአፍሪካ ብዙ ሰዎች የቅኝ ግዛት ዘመንን ይመርጣሉ፤ የተሻለ ነፃነት ነበራቸው።

"ይህ ሁሉ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ዐረ—የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ጩኸት ዋጋ ቢስ መፈክሮች ናቸው ። የሕዝቡን አስተሳሰብ ከብሔራዊ ችግር ይልቅ ወደሌላ እንዲያተኩር የማዘናጊያና ሰበብ መፈለጊያ መፈክሮች ናቸው ። የጥቁር አፍሪካ መሪዎች ከሚገባው በላይ ስለ ደቡብ አፍሪካ ዘረኛ ፖሊሲ በማውራት በራሳቸው ቤትና ደጃቸው ላይ ያሉትን ችግሮች ለመርሳት ይሞክራሉ ።" በማለት የገለጡት የሲሸልሱ ፕሬዚዳንት በጠቅላይ ሚኒስትራቸው ተገለበጡ ። ጠቅላይ ሚኒስትራቸው የነበሩት አልበርት ሆኔ ሊገለብጣቸው እያሴሩ እንደ ሆነ ሰምተው የነበረ ቢሆንም ፣ ፕሬዚዳንት ጀምስ ማንሀም ግን ሊቀድሟቸውና ሊያስሯቸውም ሆነ ሊገድሏቸው አልፈለጉም ። "የፖለቲካ እስረኛ እንኳን ኖሮኝ ስለማላውቅ ሬኔን ቀድሜ መግደል አልቻልሁም። ድክመቴ ያ ሊሆን ይችላል ። ምክንያቱም በአፍሪካ ውስጥ ፕሬዚዳንት ከሆንህ ጨካኝ መሆን አለብህ ። ያለዚያ ርህራሄ ካሳየህ ትፈነቀልና ምናልባት ሕይወትህንም ታጣለህ" ሲሉ አጫወቱኝ ። ዛሬ ማንሀም በለንደን ቤታቸው ከምታምር አውስትራሊያዊ ጋዜጠኛ ጋር ምቹ ኑሮ ይመራሉ ።

ጀምስ ማንሀም ፕሬዚዳንት የነበሩት በሰላሣ ሰባት ዓመታቸው ነበር ። ደስተኛ መዝናናት የሚወዱ ነበሩ ። በየጊዜው ወደ ውጭ ሀገር ለጉብኝት መውጣት ይወዳሉ ። በአንድ ወቅት በአንዲት ሴት ታምተው ወሬው በጋዜጣ ሲወጣ የፖለቲካ ባለሥልጣኖቻቸውን ሰብስበው የሴትዮዋን ፎቶግራፍ በማሳየት ስለጉዳዩ አስረዱ ። ወዲያው ከሶስት ሳምንት በኋላ በተደረገ ምርጫ ሕዝቡ መረጣቸው ። "እኛ ትንሽ አገር ስለሆን ያልሆነውን ለመሆን መሞከር የለብንም ። ከልኩ በላይ የሆነ የፖለቲካ ርዕዮተዓለም አያሻንም ፤ ራሣችንን እን



ሁን ፣" የሚሉት እኚህ መሪ ዓለምአቀፍ አውሮፕላን ጣቢያ አሠርተውና የሚያማምሩ ሆቴሎች በማነፅ አገሪቱን የቱሪስቶች መጉረፊያ አደረጓት ። የሕዝብ ግንኙነት ሥራ በማካሄይ አገሪቱን ለዓለም አስተዋወቋት ። ምኞታቸው በየዛፉ ሥር ደስተኛና ጊታር የያዘ ወጣት ማስቀመጥ ነበር ።

የማንሀም ዓይነት የቅንነት አመራር በአፍሪካ ዘላቂነት የለውም ። ስለዚህም በ1977 ለጋራ ንብረት ሀገሮች ስብሰባ ወደ ለንደን እንደሄዱ በመልካም ሁኔታ የሸኙዋቸው ጠቅላይ ሚኒስትራቸው ሬኔ ሬዲዮ ጣቢያውን በታንዛንያ ወታደሮች ተቆጣጠሩና (በየትም የአፍሪካ አገር እንደሚደረገው (ሥልጣን መንጠቃቸውን አወጁ ። ሲሸልስ ከኬንያ አንድ ሺህ ማይልስ ርቃ የምትገኝ ደሴት ስትሆን 60000 ሕዝብ ብቻ ያላት አገር ናት ። ሕዝቡ የተለያየ ዝርያ ቅልቅል ሆኖ የፈረንሣይ ፣ የአፍሪካ ፣ የሩቅ ምሥራቅ ድብልቅ ነው ። ማንሀም ራሳቸው የቻይና ዘር አላቸው ። የነፍስ ወከፍ ገቢ በዓመትስድስት መቶ ሃምሳ ዶላር ሆኖ በአፍሪካ ከከፍተኞቹ ሲሆን ፣ ማይምነትም እንዲሁ ሰባ አምስት ከመቶ ነው ።

ሬኔ ሥልጣን ከያዙ በኋላ የግራ ፖለቲካ ማራገብ ጀመሩ ። ኤኮኖሚውን በከፊል ወረሱ ። ተቃዋሚዎቻቸውን አሰሩ ። ኡጋንዳን ባመስቃቀሉ የታንዛንያ አማካሪዎች በመመራት የጦር ሠራዊት መሠረቱ። የቱሪስቶች ቁጥር እየቀነሰ ፣ ኤኮኖሚዋ እየተዳከመ ሄደ ። ሀሳብን ያለስጋት የመግለፅ ነፃ ፕሬስ እየተዳከመ መጣ ። በ1980 የሲሸልስ መንግሥት በግልበጣ ሥልጣን የያዘበትን ሶስተኛ ዓመት ያከበረው በወታደራዊ ሰልፍ በብረት ለበስ መኪናዎችና በወታደር ማጓጓዣ ካሚዮኖች ታጅቦ ነበር ። ያ ሁሉ መሣሪያ በሰልፍ ሲያልፍ የዘምባባ ዛፎች በድምፁ ይውረገረጉ ነበር ። በዛፎቹ ሥር የቆሙት ወጣቶች ማንሀም እንደተመኙት ጊታር መያዝን ትተው ጠመንጃ እንዲሸከሙ ሆነዋል ።

"በሌላ መልኩ ተመልከተው እስቲ ፣ በሕይወት ተርፌ እኖራለሁ ። ስንቶቹ የቀድሞ የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች ናቸው ይህን የመሰለ እድል ያገኙት? ከዚህም በቀር በእኔ ዘመነ መንግሥት ሁሉም ደስተኛ

ነበር ፤ ይህን ሊሉ የሚችሉ የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶችስ ስንት ናቸው?” በማለት ማንህም ለንደን አግኝቼ ባነጋገርኳቸው ወቅት አስረዱኝ ።

በ1816 የአሜሪካ ምክር ቤት ለሰው ልጅ ፍቅር ያላቸውን አሜሪካውያን በቡድን በማደራጀት መርከብ ተኮናትረው ወደ ቅድመ አያት አገራቸው ወደ አፍሪካ መመለስ የሚፈልጉ ነፃ የወጡ ባሮችን እንዲያጓጉዙ አደረገ ። ለዚህም ተግባር ምክር ቤቱ 100000 ዶላር በመለገስ መርከቦች እንዲዘጋጁ ሆነ ። ከስድስት ዓመታት በኋላ በተከታታይ 45000 የቀድሞ ባሮች ወደ ምዕራብ አፍሪካ ተመለሱ ። መኖሪያ ሀገራቸውንም ላይቤርያ ብለው ሰየሙ ። ሊበርቲ(ነፃነት) ለማለት ነው ። ዋና ከተማቸውንም በዘመኑ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጀምስ ሞንሮ ስም ሞንሮቢያ ብለው ሰየሟት ። በ1947 ላይቤሪያ የመጀመሪያዋ የአፍሪካ ሪፑብሊካዊ አገር ሆነች ። የአሜሪካ ዓይነት መስተዳድር መሠረተች ። ባንዲራቸውም አንድ ኮከብ ብቻ ያለው ሆኖ የአሜሪካ ዓይነት ሆነ ። ብሔራዊ መርሀቸውም “የነፃነት ፍቅር ወደ ዚህ አመጣን” የሚል ነበር ።

አዲሶቹ ጥቁር ሰፋሪዎች የአኗኗር ዘይቤአቸው የቀድሞ ነጭ ገዢዎቻቸው ዓይነት ሆኖ ነዋሪዎችን ስድሳ ጐሣዎች በመጨቆን መብት አሳጥተዋቸው እስከ 1950 ቆዩ ። ንግዱንም አስተዳደሩንም በእጃቸው በማስገባት ልጆቻቸውን ለትምህርት ወደ ውጭ ሀገር ይልኩ ነበር ። በባህላቸው ሁሉ አፍሪካዊነታቸውን ንቀው አሜሪካዊ ዓይነት ሆኑ ። ለልጆቻቸው ሳይቀር አሜሪካዊ ስሞቻቸውን አወረሱ ።

የሚገበያዩበት ገንዘብ የአሜሪካ ዶላር ነው ። ፖሊሶቻቸው የሚለብሱት ዩኒፎርምም የቀድሞ የአሜሪካ ፖሊሶች ይለብሱት የነበረው ዓይነት ነው ። አንዳንድ ከተሞቻቸው ሳይቀር ስማቸው ሜሪላንድ ፣ ኒው ጆርጂያ ፣ ሉዚያና የተሰኙ ናቸው ። በሰንበት ቀናት ሬዲዮ ጣቢያው የአሜሪካ ብሥራተ ወንጌል ሙዚቃዎች ሲያሰማ ይውላል ። በሞንሮቢያ መሀል ከተማ በሚገኘው የባብቲስት ቤተክርስቲያን እሁድ እሁድ የሚሰማው መዝሙር ቅላፄው ልክ በደቡብ ዩናይትድ እስቴትስ እንደሚስተጋባው ዜማ ነው ።



አፍሪካውያን ለረጅም ዘመናት በላይቤርያ መጤ ባህል ማዘውተር ሲሳለቁ ኖረዋል ። እንዲያም ሆኖ ግን ላይቤርያ የምትደነቅበት የተረጋጋ አስተዳደር ነበራት ። በመላ አፍሪካ መንግሥታት እንደዶሚኖ ሲረግፉ የላይቤሪያ ፖለቲካ እንደ ጠንካራ አለት የጠበቀ ነበር ። ውስጣዊ ኃይልና ዘላቂነት ያለው ይዘት ነበረው ። እስከ 1980 ድረስ ለ133 ዓመታት አንድም መፈንቅለ መንግሥት አልተከሰተም ። በ1971 ፕሬዚዳንት ዊሊያም ተብማን ሲሞቱ ምክትል ፕሬዚዳንታቸው ሆነው ለሃያ ዓመት ያገለገሉት ዊሊያም ቶልበርት በሕገመንግሥቱ መሠረት ተክተው መሥራት ቀጠሉ ። በዚያ ወቅት ቶልበርት “ይህ አገር የመረጋጋት እውነተኛ ምሳሌ በመሆኑ እንኩራበታለን” ሲሉ ተናግረዋል ።

የፖለቲካ ፍልስፍናቸውን ሰብዓዊ ካፒታሊዝም በማለት የሚጠቅሱት ዊሊያም ቶልበርት የሃይማኖት ሰው ነበሩ ። “ፍላጐታችን እያደጉ በሚሄዱበትና የተፋጠነ ለውጥ በሚታይበት ዓለም ክብር ግባችን ለመድረስ ላይቤሪያወን መላ የተፈጥሮ ሀብታቸውን በመግራትና በማልማት ያልተቋረጠ ዕድገት ለማግኘት መጣጣር አለባቸው” ሲሉ አሳሰቡ ።

ቶልበርት ተወዳጅ ጨዋና ብቁ አፍሪካዊ መሪ ነበሩ ። በአድሉና ምዝበራ አይታሙም ። ይሁንና ሦስት የአስተዳደር እንከኖች ነበሩባቸው ። በአንድ በኩል ላይቤርያ በፖለቲካዋ አፍሪካዊ አቅጣጫን መከተል ነበረባት ። በሁለተኛ ደረጃ ዜግነት የሚታዩት ነባር አፍሪካውያን ቅሬታቸው እንዲወገድ ከመጤዎቹ አፍሪካውያን ጋር በእኩልነት መታየትና መስተናገድ ነበረባቸው ። ሶስተኛው ችግር በብረት ፣ በደን ፣ በጎማ ዛፍና በአያሌ መርከቦች ምዝገባ ገቢ ላይ የተመሠረተው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እንደገና መዋቀርና ትክክለኛ አመራር መያዝ ነበረበት ። ቅኝ ግዛት ሆና ስለማታውቅ ላይቤሪያ በቅኝ ገዢዎች የተገነቡ ትምህርት ቤቶች ፣ መንገዶች ፣ ሆስፒታሎችና የሠለጠነ የአስተዳደር መዋቅር አልነበራትም ። ከውጭ ያገኘችው የልማት መዋዕለ ንዋይም ትንሽ ነው ። በነፃነት መቆየትዋ ራሱ ሕዝቦችዋን የጐዳበት ሁኔታ አለ ።

ቶልበርት በእነዚህ ሶስት ዘርፎች ሁሉ የማይናቅ እድገት አስ

ፃኝተዋል ። የሚሄዱት በቦልስዋገን መኪና ሲሆን ፣ የሚለብሱትም ካኪ ማሪያን ልብስ ነው ። የተጨቆኑ ዜጎችን በመንግሥት ሥራ እንዲሳተፉ በማድረግ የሞራል ተሃድሶ አስገኙላቸው ። የደቡብ አፍሪካን ጥቁሮች የነፃነት ንቅናቄ ለማገዝ የገንዘብ መሰብሰብ ዘመቻ ጀመሩ። የኢዲ ፣ አሚንን አረመኔያዊ አመራር በመቃወም በይፋ ከነቀፉ ጥቂት ደፋር የአፍሪካ መሪዎች አንዱ ናቸው ። የመሪዎች ነፃ ምርጫ እንዲደረግ ግንባር ቀደም አርአያነት አሳዩ ። ሕገመንግሥቱንም አሻሽለው እራሳቸውም ቢሆኑ ለዳግመኛ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ እንደማይቀርቡ አስወሰኑ ። ይህም አንድም አፍሪካዊ ፕሬዚዳንት ያላደረገው ነው ። ነፃ የዩኒቨርስቲ ትምህርት ዕድል ለሁሉም እንዲሰጥም አድርገዋል።

አንዲት ሞንሮቢያዊ ከበርቴ ሩዝ ፣ ፊሊፕ በአንድ ወቅት ስንወያይ ፣ "እኛ ላይቤሪያውያን እድለኞች ነን ፣ በአፍሪካ እንደዚህ መረጋጋት የሠፈነበትና የግለሰብ መብት የሚከበርበት ጥቂት ነው ። ሌሎችን ፕሬዚዳንቶች በአገራቸው ላይ ለሚያሳዩት አምባገነንነት ካወገዝህ በላይቤሪያ ስላለው ሁኔታ ደግሞ ቶልበርትን ማድነቅ አለብህ" አለችኝ ። ወደ ሰለሣ ዓመት ለሚጠጋው የቶልበርት የአመራር ዘመን ሕዝቡ ለክብራቸው ሲዘምርላቸው ኖሯል ። ከምክትል ፕሬዚዳንትነት ጀምሮ ይህን ያህል ዘመን ለመሩት እኒህ ሰው ጄኔራሎቻቸው ሁሉ ሁሉ በታዛዥነት ትእዛዛቸውን ሲፈጽሙ ቆይተዋል ። በኋላ ግን በአፍሪካ እንደተለመደው በወታደሮቻቸው ተገድለው ያለክብሬታ እንደውሻ ተቀበሩ ።

በሚያዝያ ወር 1980 አንድ ምሽት ለሃይማኖት መሪዎችና ለዲፕሎማቶች የሪሴፕሽን ግብዣ አደረጉና ወደመኖሪያ ቤታቸው ሄዱ። እኩለ ሌሊት ሲሆን ፒጃማቸውን ለብሰው ፀሎት አደረሱና አልጋቸው ላይ ተኙ ። ከሁለት ሰዐት እንቅልፍ በኋላ ከጠባቂዎቻቸው አንዱ የነበረው ሳሙኤል ዶ ፣ የተሰኘ ሃምሳ አለቃ ከአሥራ ዘጠኝ የሥራ ባልደረቦቹ ጋር ሆኖ የቤታቸውን በር ሰብሮ በመግባት ተኩስ ከፈቱ ። ጥቂት ታማኞቻቸውን በማሸነፍ ወደ ፕሬዚዳንቱ መኝታ ክፍል አመሩ። በተኩሱ ልውውጥ የስልክ መስመሮች ስለተበላሹ ቶልበርት ወደ ጦር ካምፓቸው መደወል አልቻሉም ። ሳሙኤል ዶ ፣ እና ጓደኞቹ



የመኝታ ክፍሉን በር ሰብረው ሲገቡ ቶልበርት አልጋቸው ላይ ተጋድመዋል ። ወታደሮችም የቀኝ ዓይናቸውን አወጡና ጉትተው በመጣል በሶስት ጥይት ራሳቸውን ፈረካከሱት ።

ከሁለት ቀናት በኋላ የቶልበርት አስከሬን ከሞቱት ጠባቂዎቻቸው ጋር በካሚዮን ተጭኖ በዶዘር በተማሰ ምልክት ባልተደረገበት ጉድጓድ ውስጥ ከነፒጃማው ተወረወረ ። በዚያው ሰሞን የላይቤርያ ወታደራዊ መሪዎች የሰዓት እላፊ አወጁ ።

እንደዚያ የተከበሩና የሃይማኖት መሪ ጭምር ለነበሩት ቶልበርት ፀሎትም ሆነ ፍታት አልተደረገላቸውም ። ጭራሽ ሕዝቡ በፎቶግራፋቸው ላይ ድንጋይ እየወረወረ ይሰድባቸው ጀመር ። ቶልበርት በዚያን ዘመን የዓመቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊቀመንበር ነበሩ ።

ከግልበጣው በኋላ ሳሙኤል ዶ ፣ በማርቼዲስ መኪና እየተዘዋወሩና በፕሬዚዳንቱ መኖሪያ ቤት እያደሩ ሥልጣናቸውን ማረጋገጥ ቀጠሉ ፣ በትምህርት ያልገፉት ሳሙኤል ዶ ፣ ጋዜጣዊ ጉባኤ ጠሩና "የእኛ ኃላፊነት አዲስ ኅብረተሰብ መገንባት ነው ፤ ይህም ለሁሉም ሕዝቦች ጥቅም የሚበጅ እንዲሆን እናደርጋለን" በማለት ተናገሩ ። በኋላ ግን ለብዙዎች ሳይሆን ለጥቂቶች መቆማቸውንና በቅድሚያም የበቀል እርምጃዎችን በመውሰድ አምባገነንነታቸውን በተግባር አረጋገጡ ።

የሳሙኤል ዶ ፣ ወታደሮች መረን ተለቀው በሰበብ አስባቡ ሲቢሉን ሕዝብ በመዝረፍ ፣ ሱቆችን በመስበር ስቃይ ያሳዩት ጀመር ። ጥቂት ወታደሮች ኮንትኔንታል ሆቴልን ሰብረው በመግባት በመኝታ ክፍሎች ያሉትን ለስብሰባ የመጡ ልዑካን ንብረት ዘረፉ ። የቶልበርት ወዳጆችና የቅርብ ረዳቶች የነበሩ ሁሉ ታሰሩ ። ባለሥልጣን የተባለ አንድ ሳይቀር በእስር ቤት ታጎረ ። ዘጠና አንድ ባለሥልጣኖች በምዝበራና በሰብዓዊ መብት ረገጣ ወንጀል ተከሰሱ ።

ከሞንሮቢያ ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኝ የጦር ካምፕ ውስጥ የጦር ፍርድ ቤት ወዲያው ተቋቋመና ክሶቹን ማየት ጀመረ ። አምስት ሰዎች ያሉበት የጦር ፍርድ ቤት ለተከሳሾቹ ጠበቃ እንዳይቆምላቸው በመ

ከልክል ሥራወን ቀጠለ ። የተከሳሾች ቤተሰቦችና ሕዝቡ ተኮልኩሎ የቀድሞ ሚኒስትሮች ውስጥ ሱሪ ብቻ ራቁታቸውን እንደከበበት እየተነዱ ሲሄዱ ድምፁን አጥፍቶ ይመለከታል ። በጦር ካምፑ አቅራቢያ የእንጨት ምሰሶዎች ተተከሉ ። በስቅላት የሚቀጡ እንደሚኖሩ የሚጠቁም ነበር ።

በታክሲ ተሳፍሬ ወደ ጦር ካምፑ ሄድሁና ዘበኞችን እንዲያስገቡኝ ጠየቅሁ ። ጋዜጠኛ መሆኔን ስገልጥላቸው የሚከለክሉኝ መስሎኝ ነበር ። ነገር ግን እንድገባ ፈቀዱልኝ ። ወዲያው ሄጄ ፍርድ የሚሰጥበት ክፍል ውስጥ ገባሁ ። እንደደረስሁ የቶልበርት መንግሥት የበጀት ዲሬክተር የነበረው ፍራንክ እስቴዋርት በዳኞች እየተጠየቀ ነበር ።

የስቴዋርት ፀጉር ተንጨፍሮና አቧራ ለብሶ ለአሥር ቀናት በእስር ቤቱ ስሚንቶ ላይ ሲንገላታ መቆየቱን ያመለክታል ። ከላይ ካናቴራ ከታች ቀበቶ የሌለበት ግራጫ ሱሪና ነጠላ ጫማ አድርጓል ።

አምስቱ ከሳሾቹ በጥላቻ ዓይን እየተመለከቱት በጥያቄ ያጣድፉታል። እነዚህ ከሁለት ሳምንት በፊት የአገሪቱ መንግሥት ታዛዥ ወታደሮች የነበሩ ናቸው ። አሁን ግን የአዲሱ አመራር አካል አባላት ሆነዋል ። በግራ በኩል ቃል ተቀባዩ ታይፑን ይቀጠቅጣል ። ከአዳራሹ ኋላ ጠመንጃ የያዙ ወታደሮች ቆመዋል ።

ጥያቄና መልሱ እንደቀጠለ እስቴዋርት ከቤቶች ኪራይ በዓመት 32,000 ዶላር እንደሚያገኝና እርሻ ፣ ሱቅና ሌሎችም ንግዶች እንዳሉት ተገለጠ ። ሁሉም በሕጋዊ መንገድ ያፈራው ሀብት እንደሆነ ወተወተ ። ለዚህም ማስረጃ ለማቅረብ እንዲፈቀድለት ጠየቀ ። የተሰጠው መልስ ግን "ያን ማድረግ ጊዜ ማባከን ነው" የሚል ነበር ። በዚህም እንደተፈረደበት አወቀ ። ያልተረዳው ጉዳይ ቅጣቱ እሥራት ወይስ ሞት መሆኑን ብቻ ነበር ። ንብረቱን እንዴት ሊያፈራው እንደቻለ ለመግለጥም አልተፈቀደለትም ።

"አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን ቤቶች እየሠራ ማከራየት ይገባዋል?" የሚል ጥያቄ ከአንደኛው ዳኛ ቀረበለት ። "ይህ እንግዲህ



እንደአስፈላጊነቱና እንደመንግሥት ፖሊሲ ነው" ሲሉ እስቴዋርት መለሱ ። "ለመሆኑ የውሃና የመብራት ሂሳብዎን አሟልተው ከፍለዋል?" የሚል ሌላ ጥያቄ ከሌላው ዳኛ ቀረበ ። ይህን ሳይመልሱ ሌላው ደግሞ "ከዚህ የመጀመሪያው መፈንቅለ መንግሥት በፊት በነበሩት ፕሬዚዳንቶች ተብማንና ቶልበርት አስተዳደሮች ምን ልዩነት ነበረው?" የሚል ሌላ ጥያቄ ሰነዘረ ። በመጨረሻም "ለመሆኑ ይህ መፈንቅለ መንግሥት ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?" የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው ። ሕይወታቸውን ለማትረፍ ሲሉ "አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ዘግይቷል" ሲሉ መለሱ ። ጠያቂያቸው ፈገግ አለና "ጨርሰናል" አለ ።

በተከታዩ ቀን ሳሙኤል ዶ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጡና ሲጨርሱ የማስታወቂያ ሚኒስትራቸው ገብርኤል ኒሞሊ "በስምንት ተኩል እርምጃ የሚወሰድባቸው የቀድሞ ባለሥልጣኖች ሲገደሉ እንድንመለከት ጋበዙን ። በቦታው ስንደርስ በሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ተሰብስቧል ። የተፈረደባቸው አሥራ ሶስት የቶልበርት ባለሥልጣኖች በኩምቢ መኪና ውስጥ ሆነው ይቁለጨለጫሉ ። ያመጧቸው ወታደሮች ይሳለቁባቸዋል ።

ሃምሳ አለቃ ሳሙኤል ዶ በስፍራው እንደደረሱ ዘጠኙ ወንጀለኞች የሚባሉት ተጐትተው ተወሰዱና ከአንዳንድ የተተከለ ግንድ ጋር ታሰሩ ። የውስጥ ሱሪ ብቻ እንደለበሱ ናቸው ። የተናደደ መልክ የሚታይባቸው አሉ ። የቶልበርት ወንድም የነበሩት ፍራንክ ቶልበርት በድንጋጤ ተዝለፈለፉ ። እስቴዋርት ሁኔታውን ባለማመን አይናቸውን አፍጥጠው ሕልም መስሏቸዋል ። የገንዘብ ሚኒስትር የነበሩት ጀምስ ፊሊፕስ የውስጥ ሱሪያቸውን አረጠቡት ።

"እስኳድ ተኩስ!" የሚል ትዕዛዝ ተሰጠና የመጀመሪያዎቹ ዘጠኙ ፍርድ ተፈጸመባቸው ። የተሰበሰበው ሕዝብ "ነፃነት! ነፃነታችንን አገኘን!" በማለት አስተጋባ ። ወታደሮቹም ወደሞቱት ሰዎች እስከሬን ፈጥነው ሄዱና ሬሳዎቹን በካልቾ መምታት ቀጠሉ ።

ሳሙኤል ዶ ሥልጣን እንደያዙ መጀመሪያ ያደረጉት የወታደሮችንና የመንግሥት ሠራተኞችን ደመወዝ ,በእጥፍ መጨመር ነበር ።

የሀገሪቱ ካዝና ባዶ ስለነበር ይህ ጭማሪ የኤኮኖሚ ቀውሱን አባባሰው ። ብዙ ሳይቆይ በባለሥልጣኖች ግድያ የፈነደቀው ሕዝብ በአድራጎቱ የቸኮለ መሆኑን ተገንዝቦ ሀፍረት ተሰማው ። ሥልጣን ከአንዱ እጅ ወደሌላው ከመዛወሩ በስተቀር ሌላ ፋይዳ የለውም ።

ሃምሳ አለቃ ሳሙኤል ዶ ወዲያውኑ ራሳቸውን ጄኔራል ብለው ሰየሙ ። በየጥዋቱ ፀጉር አስተካካይ ወደ መኖሪያ ቤታቸው እየመጣ አፍሮ ፀጉራቸውን እያበጠረ ያስተካክላል ። በሞተር ቢስክሌተኞች ታጅበው እየተዘዋወሩና በተቃዋሚዎቻቸው ላይ በዝግ ችሎት እየፈረዱ በሕዝብ ፊት በመግደል ሥልጣናቸውን አጠናከሩ ። አሜሪካም በምዕራብ አፍሪካ ያላትን የተጽዕኖ ክልል ላለማጣት እንደ ጀግና ተንከባከበቻቸው ።

ቶልበርትን በመግደል ዶ እና ፖለቲከኛ ወታደሮቻቸው የላይቤሪያን ችግሮች ምልክቶች ብቻ ነው ያወቁት ። የችግሮቹ ምክንያቶች አልተመረመሩም ። መንግሥትን መምራት መፈንቅለ መንግሥት እንደ ማካሄድ ቀላል አልሆነላቸውም ። የመንግሥት ባለሥልጣኖችን ግድግዳ አስደግፎ መግደል ቀላል ሲሆን ፤ ለብሔራዊ ችግሮች መፍትሔ ማመንጨትና ተግባራዊ ማድረግ ግን በጣም የተወሳሰበ ሆነባቸው ። ሕዝቡም ነፃነት ከጠመንጃ አፈሙዝ ሊመጣ እንደማይችል ተገነዘበ ። ከወታደሩ መፈንቅለመንግሥት የተገነዘቡት አንድ ግልፅ ነገር ይህ የላይቤርያ የመጀመሪያ የሥልጣን ንጥቂያ የመጨረሻው እንደማይሆን ነው ።

በላይቤርያ የተካሄደው መፈንቅለ መንግሥት እያንዳንዱን የአፍሪካ ፕሬዚዳንት ከነከነው ። የዓመቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊቀመንበር በጥቂት ወሮበሎች የሚገደል ከሆነ ማን መተማመን ይችላል ። ማንም ከዚህ የሚድን የለም ። የፖለቲካ መረጋጋት በጥቁር አፍሪካ ይገኛል ማለት የማይጨበጥ ቅዠት ሆኗል ። ማንኛውም መንግሥት በቀላሉና በድንገት እንደ ፕሬዚዳንት ቶልበርት ሊገለበጥ ይችላል ። በአፍሪካ ከሚታየው የሥልጣኔ ጭላንጭል ጀርባ ኋላቀር የሆነ አረመኒያዊ ባህርይ እንደታሰረ አንበሳ በሰው ላይ ለመዝለል እድል እስኪያገኝ አድፍጦ ይጠብቃል ።



የቶልበርት አወዳደቅ ለሌሎች የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች ውድቀት ምክንያት በሆኑት ጉዳዮች ላይ የተመሠረተ ነው ። መጀመሪያ የሕዝቡን ፍላጐትና የሚጠብቀውን ተስፋ አነሳሱ ፤ በኤኮኖሚና በማህበራዊ እድገት ብዙ ተስፋ አሳደሩ ፤ ከገቡት ቃል እውን ያደረጉት ግን ኢምንት ነው ። በሁለተኛ ደረጃ ምዝበራን በመፍቀድ በሀብታምና ድሀው መካከል ያለው ልዩነት እጅግ እየሰፋ አፍሪካውያን ሊቀበሉት ከሚችለው በላይ እንዲሄድ አደረጉት ። በኋላም ሕዝቡ ከፍርሃትና ከለዘብተኝነት የሚያሳየው የማስመሰል አክብሮትና ፍቅር እውነት መስሎ ታያቸው ። በመጨረሻም ራሳቸው በፈጠሩት ሥርዓትና ለማሻሻል በሞከሩት አመራር ተደመሰሱ ።

እንደሌሎች የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች ሁሉ ቶልበርት ጥሩ ቃሎችን ይሰነዝራሉ ፤ ግን ተቃውሞ ሲአይልና የመረጋጋት ምሰሶዎች ሲሰነጣጠቁ አላስተዋሉም ። የአፍሪካ ታሪክ ትምህርቶች አምልጠዋቸዋል ።

የሚያሳዝነው በአፍሪካ ውስጥ ታሪክ ራሱን የመድገሙ ሁኔታ ይቀራል ብሎ ለማሰብ በጣም የጠበበ መሆኑ ነው ። አንድ አዝማሚያ ይቀጥላል ብለን ካሰብን አፍሪካ ብዙ የመፈንቅለ መንግሥት ክስተቶች ያጠቁዋታል ። በተከታዮቹ አስር ዓመታት ብዙ ይኖራሉ ። ምክንያቱም ከቃሉ በስተቀር ብዙ የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች ለአለመረጋጋት ምክንያቶች ትኩረት ለመስጠት አልፈለጉም ። ቶልበርትም ወደመጨረሻው ማሻሻሎች አድርገው ነበር ። ነገር ግን በጣም የዘገዩና ኢምንት ነበሩ ። እንዲያውም ያስገኙት ነገር ቢኖር ለተቃዋሚዎች ቅስቀሳ ተጨማሪ በር መክፈት ነው ። በዚህም ምክንያት ፕሬዚዳንቶች ፖሊሲዎቻቸውን ለማሻሻል ይፈራሉ ። ይህንንም አሻፈረኝ በማለት የፈሩት እንዲደርስ የሚያደርግ ሁኔታን ይፈጥራሉ ።

ለቶልበርት መገደልና ለሳሙኤል ዶ ወደ ሥልጣን መውጣት ምክንያት የሆኑ ድክመቶች በየትኛውም የአፍሪካ አገር ከላይቤርያ በከፋ ሁኔታ ይታያሉ ። የአገሮች ኤኮኖሚ እየሟሸሸና ፕሬዚዳንቶችም የሕዝቡን የመናገር መብት እያፈኑ በሄዱ ቁጥር የሚኖረው መጨረሻ አንድ ብቻ ነው ። የአፍሪካ አለመረጋጋት እንዲያውም ገና መጀመሩ ነው ።

## ምዕራፍ ሰባት

# የቅኝ ግዛት ውርስ

"እቅጩን ልንገርህ ፣ የቀድሞው ጊዜ ለአውሮፓውያን በማይታመን ሁኔታ ግሩም ነበር ። ሕግ ስላልነበረ ተሳካ ልን ። ሕግ ማለት እኛው ራሳችን ነበርን ።"

ላታም ሌስሊሙር
የዘጠና ዓመቱ እንግሊዛዊ መጤ በኬንያ

በ1977 የአውሮፓ ቅኝ ግዛቶች በብዛት ነፃ ወጥተው በምሥራቅ አፍሪካ አንዷት ትንሽ አገር ጅቡቲ ብቻ ቀርታ ነበር ። ይህች ጠፍ በረሃ አገር ለአንድ መቶ አሥራ አምስት ዓመታት በፈረንሣይ ሥር ትተዳደር ነበር ። ፈረንሣይ ክልሉን በሙቆጣጠር ወደ ሳይጎንና ማዳ ጋስካር ለሚጓዙት መርከቦቿ ነዳጅ መሙያ ጣቢያ አድርጋው ቆይታ ለች ። ጅቡቲ ማለት በአፋርኛ ቋንቋ ምግብ መቀቀያ ማሰሮ ማለት ሲሆን ይህ ሥፍራ አንዳችም የተፈጥሮ ሀብት የሌለውና ፈረንሣይ በየዓመቱ መቶ ሚሊየን ዶላር ታወጣበት የነበረ ቦታ ነው ። ሁለት ፋብሪካዎች ብቻ ነበሩ ። አንዱ የኮካኮላ ሌላው የፔፕሲ ፋብሪካ ነው ። ከጥቂት የጓሮ ቲማቲም በስተቀር ሌላው ሁሉ የምግብ ምርት ከውጭ የሚገዛ ነበር ። ጨው ከሆላንድ ፣ አትክልትና እንቁላል ከኢትዮጵያ፣ ሥጋ ከኬንያ ፣ የሚጠጣ ውሃ ከፈረንሳይ ታስመጣለች ። የአፋርና ኢሣ ሕዝብ ብዛት በጅቡቲ 320,000 ነው ።

ጅቡቲ የሀገሪቱ ብቸኛዋ ከተማ ስትሆን ጥቂት ቡና ቤቶች አሏት ። የፈረንሣይ ወታደሮችና ሲቢሎች በቡና ቤቶች በረንዳ ተኮ

ልኩለው በቀኑ ሙቀት በላብ እየ(ነ)መጡ የሸሚዛቸውን ቁልፎች
እስከ ወገባቸው ከፍተው የሞቀ ቢራ እየተጋቱ ጊዜ ይገድላሉ ። ማታም
ሙቀቱ አያስተኛም ። የአየር መቅዘፊያው አየሩን ለመግፋት ሲያጉረ
መርም ያድራል ፤ ግን አየሩ በቀላሉ የሚንቀሳቀስ አይደለም ። ሁሉም
በሙቀቱ ኃይል ፈዝዞ ሲያዘግም ይውላል ። የአፍሪካውያኑን መኖሪያ
ክልል ከሌላው ክፍል የሚገድብ አጥር ፈረንሣዮች አሠርተዋል ።
ይህም የሆነው የፈረንሣይ ፕሬዚዳንት ቻርልስ ዴጎል በ1960ዎቹ
ጅቡቲን ሲጎበኙ የተቃውሞ ሰልፍ ከተደረገባቸው በኋላ ነው ።

በጅቡቲ 15000 ፈረንሣውያን ይኖሩ ነበር ። ወታደሮች ፤ ነጋ
ዴዎች ፤ የመንግሥት ሠራተኞችና ሌሎችም ይገኙባቸዋል ። በ1977
ብዙዎቹ ዕቃዎችን መቀርቀብ ጀምረዋል ። ከአገራቸው ውጭ ሌላውን
ቤታቸውን ሊለቁ ነው ። ኢንዶቻይና የነበረውን ቤታቸውን ለቀዋል፤
የምዕራብ አፍሪካ ቅኝ ግዛቶቻቸውም ሄደዋል ፤ ጅቡቲም በቅርቡ
ታሰናብታቸዋለች ።

ጅቡቲ ነፃነቷን ስትቀዳጅ ፕሬዚዳንት የሆኑት ሀሰን ጉሌድ
አፕቲዶን በፈረንሣይ የተሰየሙ ናቸው ። እሳቸውም የስድሳ አንድ
ዓመት አዛውንት ሲሆኑ ከብት አርቢ የነበሩና የስድስተኛ ክፍል
ትምህርት ያጠናቀቁ ናቸው ። ጅቡቲ ነፃ ከመውጣትዋ ጥቂት ቀናት
ቀደም ብሎ ወደዚያው ሄድሁና ሀሰን ጉሌድ ቤት ደረስሁ ። መቀመ
ጫቸው ላይ ሸለብ አድርጓቸው እንዳሉ ሰላምታ ሰጥቼ ተቀመጥሁ ።
ቀና አሉና እንኳን ደህና መጣህ በማለት ጠርሙስ ኮካኮላና የፈረን
ሣይ ሲጋራ አስቀረቡልኝ ። ቤታቸው ባለሶስት መኝታ ቤት በስሚ
ንቶ የተገነባ ሆኖ ጥቂት አሮጌ የቤት ዕቃዎች በሳሎኑ ተደርድረዋል ።
ዘጠና በመቶ በረሃ የሆነችውና ምንም የምታመርተው የሌላት ሀገራ
ቸው ወደፊት እንዴት ልትቀጥል እንደምትችል ስጠይቃቸው ስለ
ወደፊቱ ምንም የተጨነቁ አይመስሉም ነበር ።

“ምን ችግር አለው ፤ አንተ ስትወለድ ምንም ገንዘብ አልነበረ
ህም አይደል? ከዚያም ስራህና ትንሽ ገንዘብ በማግኘት የተሻለ
መኖር ቻልህ ። እኛም እንዲሁ እናደርጋለን ፤ ኃላፊነታችንን እንድን



ቋቋም ነፃነቱ ሲሰጠን መፍትሔውን እናገኛለን ። ብዙ አማራጮች
አሉን ፤ ጨው ፤ ቱሪዝም ፤ አወቶማቲክ ኃይል ፤ ምናልባትም እንደ
ሆንግኮንግ ነፃ ወደብ በማድረግ ፤ በዚህ ላይ የፈረንሣይ ድጐማም
ይኖራል” በማለት አስረዱኝ ።

በሰኔ ወር 1977 ጅቡቲ ነፃ ስትወጣ ብዙም ፌስታ አልነበ
ረም ። ጥቂት የሶማሊያ ነፃ አውጭ ነን ባዮች ሊረብሹ ሲሞክሩ
ተተኮሰባቸውና አንድ ሰው ሞቶ የቀሩት ከአጥሩ ውጭ ተገደቡ ።
ጥቂት ተጋባዥ እንግዶች የተጠሩበት ግብዣ ተደረገና ከዚያም
ከኢትዮጵያ የሚመጣ ጫት እየቃሙ ተቀሙጡ ።

እኩለሌሊት ላይ የፈረንሣይ ከፍተኛ ኮሚሽነር ለባንዲራቸው
ሰላምታ ሰጡና እንዲወርድ አደረጉ ። ሃምሳኛዋ የአፍሪካ ነፃ ሀገር
ጅቡቲ ተወለደች ። ከፈረንሣይ መርከብ ሃያ አንድ ጊዜ መድፍ ተተ
ኮሰ ፤ ርችቱም ሰማዩን ወገግ አደረገው ። በባብኤል መንደብ ሠርጥ
መተላለፊያ አቅራቢያ የምትገኘው ጅቡቲ በርችቶቹ ብርሃን ፈነደ
ቀች ። የተሰበሰበው ሕዝብ ደስታውን ገለጠ ። ሥነሥርዓቱ በዚያው
አበቃና ሁሉም ወደ ጉሮኖው ሲገባ ጅቡቲ በፀጥታ ተዋጠች ።

ጆን ጉንተር የሚባል የታሪክ ሰው በ1953 “ኢንሳይድ አፍሪካ”
በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሐፍ የአውሮፓውያን አፍሪካን በቅኝ
መያዝ በአብዛኛው አልሚ ጎን ነበረው በማለት የምዕራባውያንን
አመለካከት ይጋራል ። የቅኝ አገዛዝን በመሠረቱ አይደግፍም እየተ
ባለ የሚነገርለት ይህ ሰው በመጽሐፉ ውስጥ የሚከተለውን አስ
ፍሯል ።

“አውሮፓውያን አህጉሩን አውድመው ሊሆን ይችላል ፤ ነገር
ግን የሥልጣኔ በርም ከፍተውለታል ። ቅኝ አገዛዝ ለዛሬው ብሔረተ
ኝነት ምቹ ሁኔታ ፈጠረ ፤ ወደ ዴሞክራሲ የሚያመራውን ጐዳናም
ከፈተ ። አውሮፓውያን ባርነትን አስወገዱ ፤ የጎሳ ጦርነትም አጠፉ ።
መገናኛዎችን ዘረጉ ፤ የኑሮ ደረጃን አሳደጉ ፤ የተፈጥሮ ሀብቶችን
አለሙ ፤ ሳይንሳዊ የእርሻ ዘዴን አስተዋወቁ ፤ ወባንና ሌሎች በሽታ
ዎችን ለመቆጣጠር ታገሉ ፤ የጤና አገልግሎትን አቋቋሙ ፤ ጎሳዎችን

ከአረመኔያዊ አሠራር ፋቀቅ በማድረግ የሰከነ አስተዳደርና ቢያንስ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ በሕግና ፍትሕ ላይ የተመሠረተ መንግሥት ሰጣቸው ። ይህም የነጮች ሕግ እየተባለ የሚጠቀሰው ነው ። ከሁሉም ይበልጥ ክርስትናንና ምዕራባዊ ትምህርትን አመጡ ።. . .”

እነዚህን ቃሎች ስናነብ የሚመጣብን ሀሳብ ምናልባት ጉንተር በአብዛኛው የእንግሊዝ ገዢዎችን በማነጋገር ጊዜውን አጥፍቷል እንጂ በቂ አፍሪካውያንን አላነጋገረም የሚል ነው ። ምክንያቱም ጠቃሚ ሥራዎች ብሎ የጠቀሳቸው ዘላቂ አልነበሩም ። አውሮፓውያን እንደለቀቁ ወዲያው ሚሸሹ ። አውሮፓውያን ለአፍሪካ አገሮች ሰው ሰራሽ መሠረት አኖሩላቸውና ሁኔታው ሲለወጥ በድቡሽት ላይ እንደተሰራ ቤት ተናዱ ። ወየ ነፃነት ሊሸጋገር የቻለው አንደኛው ዓይነት ቅኝ አገዛዝ ብቻ ነበር ፤ ኤኮኖሚያዊ ባርነት ።

ሁለቱ የጥቁር አፍሪካውያን አገሮች ኢትዮጵያና ላይቤርያ ብቻ ቅኝ ሳይገዙ በመቅረታቸው በእህጉሪቱ ኋላቀር ከሚባሉት አገሮች ውስጥ መዳመራቸው እርግጥ ሲሆን ፣ ባለሥልጣኖቻቸውም ላለመልማታቸው ምክንያቱ የቅኝ አገዛዝን ቁሳዊ ጠቀሜታ ያለማግኘታቸው እንደሆነ አድርገው ይጠቅሳሉ ። ነገር ግን በአፍሪካ ቅኝ አገዛዝ ያስከተለው ሁኔታ እጅግ በአመዛኙ አፍራሽ ነበር ። እንግሊዝ፣ ፈረንሣይ ፣ ፖርቱጋል ፣ ቤልጅግ ፣ ጀርመን ፣ እስፓኝ ፣ አህጉሪቱን ገበጣ ተጫዋቾች ጉድጓድ እንደሚከፋፈሉ ተቀራምተዋት ነበር ። ፍላጐታቸውም የራሳቸውን የኢኮኖሚ ጥቅም ለማሟላት ነው ። ባርያ ለመግዛት ፣ የዝሆን ጥርስና ሌላም ጥሬ ዕቃ ለመዝረፍ ፣ በወደቦች ለመገልገል ፣ ለሸቀጣቸው ማራገፊያ ገበያ ለማግኘት ፣ ሥራ ያጡማይም ዜጎቻቸውን አምጥተው በማፍሰስ ለማስፈር ሲሉ ነው ። አውሮፓ በምንም ዓይነት ለአፍሪካ እድገት ተጨንቃ ቅንጣት ያሰበችው ነገር አልነበረም ። ያ ፣ እድገት አውሮፓን እስካልጠቀመ ድረስ ቦታ የለውም ። ሕግና ሥርዓት እስከተጠበቀ ድረስ የቀረው ሁሉ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ነበር ።

የሀገራቸውን ግምጃ ቤት ላለማሟጠጥ ሲሉ ጥሬ ገንዘብ የሚያስገኙ የእርሻ ምርቶችን ማምረት ጀመሩ ። በጋና ካካዋ ፣ በሴኔጋል አኩሪ አተር ፣



በማላዊ ትንባሆ ፣ በኬንያ የሻይ ቅጠል ፣ በታንዛኒያ ቃጫ ፣ በአንጐላ ጥጥ ማምረት ቀጠሉ ። እነዚህ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች ስለነበሩ ለአፍሪካ ምግብ አልሆናትም ። በአውሮፓ ላይ የነበራትን ጥገኝነትም አልቀነሰውም ። ስለዚህም አፍሪካ ወደ ነፃነት የተሸጋገረችው ያለኢንዱስትሪያዊ መሠረት ነበር ። የየአንዳንዱ አገር ኤኮኖሚ የተመሠረተው ለአፍሪካ ርባና በሌለው አንድ ዓይነት ምርት ላይ ነበር ። ለዚያውም ይህም ቢሆን በዓለም ገበያ ዋጋውን ምዕራባውያን እንዳሻቸው ስለሚያዋዥቁት አስተማማኝ ጥቅም አይገኝበትም ። ለምሳሌ በ1977 የደቡብ አሜሪካ ቡና በውርጭ ሲመታ ኬንያ ከቡና ምርት እጥፍ ዋጋ አፈሰችና ዋጋው ዘላቂ መስሏት አያሌ መዋዕለ ንዋይ አፍስሳ የቡና ልማቷን አስፋፋች ። ከሁለት ዓመት በኋላ ግን ዋጋው ወርዶ ዘጭ በማለቱ የልማት ዕቅድዋ ተናጋ ።

የአውሮፓ ኃያላን የአገሮችን ድንበሮች ሲያሰምሩና ሲወስኑ የጐሳዎችን አሰፋፈር ስላልተከተሉና ግድ ስላላደረጉ አፍሪካውያንን የባሰ ከፋፈሏቸው ። ሀብታምና ድሃ እንዲኖር አደረጉና ለመረጡት ጐሣ በማዳላት ለእነሱ የሚስማማቸው የመሰላቸውን ብሔረሰብ አስተዳደሩን እንዲይዝ በማድረግ እነዚህ በፍጥነት ወደ ብሔራዊ ከበርቴነት እንዲያድጉ ፣ ሌላው በድህነት እንዲወሰን አደረጉ ። የታደለው ክፍል ለትምህርትም ፣ ለሥልጣንም ምቹ ሁኔታ ስላገኘ ሀብትና ተሰሚነት በማግኘት ሥልጣኑንም ለንብረት ማካበቻ ተጠቀመበት ። በጥቂት ሀብታሞችና በብዙኃን ድሀው መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ ሄደ ።

አውሮፓውያን አፍሪካን ለአምስት መቶ ዓመት በበላይነት በቀጽዕኖአቸው ሥር አድርገው ሲመሩ ነጮቹ ይገዙ የነበረው ቅኝ አገዛዝ ለዘለዓለም የሚኖር አስመስለው ነበር ። ፖርቱጊዞች ከአምስት መቶ ዓመት በፊት ሞዛምቢክና አንጐላን ሲይዙ ዘለዓለም የእነሱ ሆኖ የሚቀር መስሏቸው ነበር ። የሁሉም ቅኝ ገዢዎች አስተሳሰብ እንዲያ ስለነበር አውሮፓውያን የአፍሪካን አገሮች ለብሔርነት ያዘጋጁት ወደመጨረሻው ነበር ። በዚያን ጊዜ በጣም የዘገየ ጅምር ነበር። ስለዚህም ነፃ የሚወጡት አገሮች ለአውሮፓውያን ኅብረተሰብ ተብሎ

የተዋቀረ ለእነሱ ግን የማይበጅ ቢሮክራሲያዊ መዋቅርና የኤኮኖሚ ተቋሞችን መውረስ ተገደዱ ። ከአፍሪካውያን ሁኔታ ጋር ሊጣጣም አልቻለም ። አፍሪካውያኑ ሰፊ የትምህርትና የሥልጠና ዕድል ስላላገኙ ብቃት አልነበራቸውም ። ከሃያ አምስት ዓመት በፊት አውሮፕላን ሊያበሩ ቀርቶ መኪና አልነዱም ። የባንክ ሥራ እስኪያጅ ወይም የኮርፖሬሽን ድሬክተርነት ለነጮች የታለመ ስለነበር አፍሪካውያኑ ያ ፣ ኃላፊነት ሊወድቅባቸው እንደሚችል አላለሙትም ነበር ።

ጅቡቲ ነፃ ስትወጣ ሶስት በባችለር ዲግሪ የተመረቁና መቶ የማይሞሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ዜጎች ነበሯት ። ኮንጎ ደግሞ አንድ ከፍተኛ ደረጃ ያለው የመንግሥት ሠራተኛ ብቻ ነበራት ። ሞዛምቢክ ዘጠና በመቶ ሕዝቧ ማንበብና መፃፍ የማይችል ነበር ። ዛየር በበኩሏ ከሃያ አምስት ሚሊዮን ሕዝቧ ከዩኒቨርሲቲ የተመረቁት አንድ ደርዘን የማይሞሉ ነበሩ ። እንደ ጊኒ ቢሳውና ኬፕቬርዴ የመሳሰሉት በርካታ አገሮች ደግሞ አንድም አፍሪካዊ የሕክምና ዶክተር ፣ የሕግ ጠበቃ ወይም የሂሳብ አዋቂ አልነበራቸውም ። ምናልባትም ከናይጄሪያ በስተቀር ሌላ የአፍሪካ አገር ከንዑስ ከበርቴው የሚመደብ በጥረቱ ተምሮ እዚያ የደረሰ በርካታ ጉልማሳ ያለው አልነበረም ።

በ1950ዎቹ አጋማሽ የአፍሪካ ለነፃነት መዘጋጀት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አልነበረም ። በዓለም የሞራል ሁኔታ ተለውጧል ። ቅኝ ግዛቶችን ከነፃነት ተዋጊዎች ጋር እየተቋቋሙ ይዞ መቆየት ወጭው እያሌ ሆኖ ነበርና ከፖርቱጋል በስተቀር አደጋ ተቋቁመው ለመቀጠል የፈለጉ አልነበሩም ። እንግሊዝና ፈረንሳይ ሻንጣቸውን ጭነው መውጣትን በመምረጥ ነፃ የሚወጡት አገሮች የካፒታሊዝምን ፈለግ ሳይለቁ እንደሚቀጥሉ ተስፋ አደረጉ ። የወረሱትን የምዕራብ የፖለቲካ ሥርዓት ተከትለው ኃላፊነትን የሚወጡ አገሮች የመሆን ባህርይ እንደሚላበሱ ተስፋ አሳደሩ ። በ1957 የእንግሊዝ ጉልድ ኮስት የጋና ሪፑብሊክ ተብላ የመጀመሪያዋ ከቅኝ ግዛት የተላቀቀች ጥቁር አፍሪካዊት ሀገር ሆነች ። በዓመቱ የፈረንሳይዋ ጊኒ ሁለተኛዋ ሆነች ። በ1960 አሥራ ሰባት አዲስ ሀገሮች 198,000,000 ሕዝብ ያቀፉ ነፃ ክልሎች ሆነው ተወለዱ ።



የነፃነት ዓመት እየተባለ የሚጠቀሰው 1960 የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር በነበሩት ሀሮልድ ማክሚላን የትንቢት ንግግር ተጀመረ። ለደቡብ አፍሪካ ነጮች ምክር ቤት ባሰሙት ቃል “. . . ከወር በፊት ከለንደን ከመጣሁ ጀምሮ ያስገረመኝ ጉዳይ የአፍሪካዊነት አስተሳሰብ ጥንካሬ ነው ። በተለያዩ ቦታዎች የተለያየ መልክ ይኑራቸው እንጂ በየቦታው እየተከሰቱ ነው ። በዚህ አህጉር የለውጥ ነፋስ እየነፈሰ ነው ። ወደድንም ጠላንም ይህ እያደገ የመጣው የብሔርተኝነት አስተሳሰብ የፖለቲካ እውነት ነው ። ሁላችንም በትክክለኛነቱ ልንቀበለው ይገባል ፣ ብሔራዊ ፖሊሲያችንም ይህን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት” በማለት አስገነዘቡ ።

ያ ፣ ንግግር ከመቶ ዓመት በፊት ቢደረግ ኖሮና አውሮፓ አፍሪካን በቅኝ ላለመያዝ ብትወስን ኖሮስ? አፍሪካ ዛሬ በምን ሁኔታ ላይ ትገኝ ነበር? በመጀመሪያ የጥንቱ የማሊ ግዛት ዛሬ ዘጠኝ የደረሱ ሀገሮችን ሁሉ ያጠቃለለ እንደነበር ስናስታውስ አፍሪካ ሰፊና ራሳቸውን የቻሉ ክልላዊ ሀገሮች ይኖሯት እንደነበር ማመዛዘን እንችላለን ። ይህም እንደ ጀርመንና ጣሊያን የ1800 ዓ.ም. ግዛቶች ማለት ነው ። ጠንካራው ቋንቋውንና ባህሉን በደካሞች ላይ ይጭናል ። ይህም ዘረኝነትን ይቀንስ ነበር (ያለደም መፋሰስ ባይሆንም) ፤ አፍሪካም በተገቢው ወቅት በፕሬዚዳንቶችና በነገሥታት ትመራ ነበር ፤ ከዚህም የብሔራዊ ስሜት ሊከተል ይችል ነበር ።

በሁለተኛ ደረጃ ቅኝ አገዛዝም ባይኖር አፍሪካ ከእስያ የባሰ ከምዕራባውያን የአስተሳሰብ ተጽዕኖ ልትገለል አትችልም ነበር ። ደቾች በደቡብ አፍሪካ ሰፍረው የነጭ የበላይነት መመሥረታቸው የሚቀርም አልነበረም ። ሚሲዮኖችና በኋላም ነጋዴዎች ከለንደንና ኒውዮርክ እንዲሁም ቶኪዮ መምጣታቸውና ገበያና ጥሬ ሀብት ለማግኘት መሯሯጣቸው የማይቀር ነበር ። አፍሪካውያንም ለትምህርት አውሮፓና አሜሪካ በመሄድ ስለችግሮቻቸው በመገንዘብ ወደሀገራቸው መመለሳቸው የማይቀር ነበር ። በእርግጥም ከቅኝ ገዢዎች ያላነሰ ትምህርት ቤቶችን ፣ ሆስፒታሎችን ለመገንባት ብቃት ይኖራቸው ነበር ። አፍሪካ የአውሮፓን የፖለቲካ ሥርዓት መገልበጥ ሳይኖር

ባት የራሷ አቅጣጫ ይኖራትና አለመረጋጋትን ገና ድሮ ልታስወግድ ትችል ነበር ። ከሶስተኛው ዓለም መቆጠርዋ የማይቀር ቢሆንም አፍሪካ በራስዋ እርምጃ እንድትለማ ብትተው ኖሮ እንደ ጅቡቲ የመሳሰሉ ጥቃቅን አገሮች ባልተፈጠሩም ነበር ።

ቅኝ ገዢዎች አንዳንድ ትምህርት ቤቶችን ፣ አውራ ጐዳናዎችን ፖስታ ቤቶችንና ቢሮክራቶችን ትተውላት ሄደዋል ። ነገር ግን ለአፍሪካ አህጉር ያወረሱት አስከፊ ነገር የዝቅተኛነት ስሜት ነው ፤ ራስን ለማወቅ ግራ የሚያጋባ ስሜት ። ዞሮ ዞሮ ሰዎች ለምዕት ዓመታት እንደ ቅኝ ገዢዎች ብልህ አይደላችሁም እየተባለ ሲነገራቸው መቆየታቸው ያንን እንዲያምኑ ዝንባሌ ያድርባቸዋል ።

ይህንን ስሜት የኮተኮቱት ሚሲዮኖች ናቸው ። መጽሐፍ ቅዱስን ሊያስተምሩ ወደ አፍሪካ በመጉረፍ የሕዝቡን ባህልና እምነት ለወጡት ። እነዚህ ሚሲዮኖች ያስተላለፉት መልእክት አውሮፓውያንና የአኗኗር ዘይቤአቸው የበላይነት እንዳለው የሚወተውት ነው ። በዚህም ስብከታቸው ሥልጣኔ የሚገኘው ከእነሱ ጋር ተመሳስሎ ለመኖር በመፍቀድ ብቻ እንደሆነ ነተረኩዋቸው ።

በ1972 ኢጣሊያዊው ደራሲ አልበርቶ ሞራቢያ ስለአፍሪካ በፃፈው መጽሐፍ ውስጥ ፤ “ሃይማኖት ራሱ እርጅቶና ከተጨባጩ ጋር አልጣጣም ብሎ እንዲሟሽሽ ከመተው ይልቅ በአንድ ጥፊ ለማጥፋት መሞከር አደገኛ ነው ። በተለይም ኋላቀር ሃይማኖት እምነትም ባህልም ስለሆነ ለመገፍተርና ለመጣል አደገኛ ነው ። ለአንድ ሰው ባህላዊ መሠረቱ ሲናድና ሲከዳው እንደማየት የከፋ ስቃይ የለም” ብሏል ።

ይከፋም ይልማም ሚሲዮኖቹ ተልዕኮአቸውን አከናወኑ ። የክርስትናን ሃይማኖት በመዝራት ሥር እንዲሰድ አደረጉ ። ስለዚህም ዛሬ ጨቋኝ መሪዎችና ማርክሲስት መንግሥታት እንቅፋት ቢደረድሩም በጥቁር አፍሪካ እንደቤተክርስቲያን ጠንካራ ተቋም ያለ አይመስልም ። ይህ ተቋም የምዕራቡ ዓለም ግፊት ቢኖርበትም መሠረቱ ከዚያው ከአፍሪካ ነው ። ብዙ ፕሬዚዳንቶችም የክርስትና እምነት ተከታዮች ናቸው ።



ሚሲዮኖች አሁንም በብዛት ወደ አፍሪካ እየጐረፉ ነው ። በዛየር ብቻ 5,000 ሚሲዮናውያን አሉ ። በኬንያ 3,000 ይደርሳሉ ። በብዙ አገሮች ሚሲዮኖች ቤተክርስቲያንዋ ከምትችለው ቁጥር በላይ ይፈለጋሉ ። በምዕራቡ ዓለም የቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ ሲዳከም በአፍሪካ እየተጠናከረ ሄደ ። በአፍሪካ የክርስትና ሃይማኖት እየጐለበተ ስለሄደ በ2,000 ዓ.ም. አህጉሪቱ በዓለም ከፍተኛ የክርስቲያኖች ቁጥር የሚኖርባት ትሆናለች ። በአሁኑ ጊዜ 200,000,000 ክርስቲያኖች ሲሆኑ ይህም የሕዝቡ አርባ በመቶ መሆኑ ነው ። 100,000,000 የሚሆኑ አፍሪካውያን የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው ። የቀሩት ደግሞ የተለያየ እምነትና ወግ ያላቸው ናቸው ።

በናይሮቢ የሚገኘው አንግሊካን ቤተክርስቲያን ተመራማሪ ዴቪድ ባሬት ባቀረበው የዓለም ሃይማኖቶች ጥናት እንደዘገበው በአፍሪካ በየዓመቱ ስድስት ሚሊዮን ሰዎች የክርስትና ሃይማኖትን ይቀበላሉ። ከእነዚህ ውስጥ ሁለት አምስተኛው አዲስ አማኞች ሲሆኑ የቀሩት ከክርስቲያን ቤተሰብ የሚወለዱ ናቸው ። እስልምና ደግሞ በአፍሪካ በየዓመቱ በሶስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን የሚጨምር ሲሆን ፣ ከሞላ ጐደል ሁሉም ከእስላም ቤተሰብ በመወለድ የዚያ ተከታዮች የሚሆኑ ናቸው ።

በአፍሪካ የክርስቲያኖች ቁጥር የመብዛቱን ያህል የእምነታቸው ጥንካሬ ጥያቄ የሚያስከትል ነው ። እንደሚመስለኝ ቤተክርስቲያን ተከታይ ያገኘችው ዘመናዊነት በማሳየትዋ ከኋላቀርነት የተላቀቁ እየመሰላቸው ነው ። ለተራው አፍሪካዊ ክርስትና በተአምር ማመንን ተገቢ ያደርግለታል ፤ ያም ብዙውን የተጨነቀ አፍሪካዊ ይስበዋል ።

ቤተክርስቲያን አምሳት ሚሊዮን የሚበልጡ የአፍሪካ ስደተኞችን ለመርዳት ምን ያህል እጅዋን ዘርግታለች፣ በድርቅና በረሀብ እንዲሁም በበሽታ የተጐዱትን ለመርዳትስ የቱን ያህል ጥረት አድርጋለች የሚሉትን ጥያቄዎች በሚመለከት ጠቃሚ ድጋፍ መስጠቷን መመለስ ቢቻልም ከሥር ከመሠረቱ ጀምሮ የአፍሪካ ቤተክርስቲያናት ለነጮች አገዛዝ መሣሪያ በመሆን መስራታቸው የማይካድ ነው ። ቤተክርስቲያናት የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ ግዛት ለመላቀቅ ባደረጉት

ትግል ንቁ ተሳትፎ አላደረጉም ። ምክንያቱም በአፍሪካ የተመሰረቱት የነጭ ሚሲዮናውያን ቄሶች በአቀራረባቸው በአስተሳሰባቸው ዘረኛ ስለነበሩ ነው ። ከዚህም በቀር የተለያዩ የአፍሪካ አምባገነን መሪዎች ለምሳሌ በኡጋንዳ ፥ በርዋንዳ ፥ በብሩንዲ ፥ በማዕከላዊ አፍሪካ ወዘተ በሺህ የሚቆጠሩ አፍሪካውያንን ሲጨፈጭፉ የተቃውሞ ቃል አል ተነፈሱም ፤ ምክንያቱም አፍሪካውያን አፍሪካውያንን መግደል ልማዳቸው ነው የሚል አስተሳሰብ ስለተጠናወታቸው ነው ። “የክርስቲያን ሃይማኖትን ባናላብሳቸው ኖሮ ምን ይደራረጉ እንደነበር ለማሰብ ይዘገንነኛል” በማለት በብሩንዲ የሚገኝ አንድ አሜሪካዊ ሚሲዮናዊ አጫወተኝ ። በደቡብ አፍሪካም ቤተክርስቲያን የምታስተምረውን እምነት ራስዋም አልተከተለችውም ። ምክንያቱም በዘረኛው መንግሥት ፖሊሲዎች ብዙዎቹ አሥርቱ ቃላተ ወንጌል ሲጣሱ ቃል አል ተነፈሰችም ።

በቅርቡ አንድ የደቡብ አፍሪካ የፕላስቲክ ፋብሪካ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሞተና ለቀብሩ ነጮችም ፥ ጥቁሮችም ፥ ሕንዶችም ያሉበት ብዙ ሕዝብ በቤተክርስቲያን ለፀሎት ተሰብሰበ ። በዚህ ዓይናቸው የቀላው ነጭ ቄስ ጥቁሮች ካልወጡ ምንም ሥርዓተ ፀሎት አይካሄድም በማለት ተናገሩ ። ቤተ ክርስቲያኑ ለነጮች ብቻ የሚያገለግል ስለነበረ ነው ።

በኋላም የሟቹ ባለቤት ሮቢና ስሚዝ ነጮችም ጥቁሮችም ከቤተ ርስቲያን እንዲወጡና ቄሱ ብቻቸውን እንዲቀሩ አድርገው በሜዳ ላይ በሌላ የሃይማኖት ሰው ሥርዓተ ፀሎት ተደርጎ እንዲለያዩ አደረጉ ። “በዚህ ዓይነት ራሳችንን ክርስቲያን አድርገን መቁጠር እንችላለን?” ሲሉ ሚስስ ስሚዝ ነቀፉ ።

በደቡብ አፍሪካ ተመሳሳይ የክርስትና ሃይማኖት እምነት የሚከተሉ ጥቁሮችና ነጮች አንድ ላይ መሰብሰብ አይችሉም ። ጥቁሮች ሌላ ቤተክርስቲያን እየሰሩ ለብቻ ይሰበሰባሉ ። በ1974 የሲኖዶሱ ስብሰባ የደች ቤተክርስቲያን ለይስሙላ ያህል በዘረኝነት ላይ የተመሠረተ ስብከቷን እንድታቆም ተወሰነ ። በዚህም ምክንያት ከዚያ ወዲህ ለስሙ ያህል የዘር እኩልነትን ትደግፋለች ። ነገር ግን “አዲስ



ኪዳን የሕዝቦችን በተለያየ ቀለማቸውና ዘራቸው ተለያይተው ሥርዓተ ፀሎት እንዲያደርጉ መደንገጉ ኃጢያት አይደለም” በሚል ዘረኝነት ተቀባይነት ያለው ሞራላዊ ሥርዓት እንደሆነ ተቀብለውታል ።

በምዕራብ አፍሪካ በሴኔጋል የአትላንቲክ ውቅያኖስ ጠረፍ ጎሬ የምትባል ትንሽ ደሴት አለች ። በዚች ደሴት ቅኝ ገዢዎች የፈጸሙት ግፍ አሻራና ጠባሳ በጉልህ ይታያል ። የጎሬ ደሴት ጎዳናዎች አቧራማና ጠባብ ናቸው ። ወደ ኮረብታው የሚወስደውን ዙሪያ ጥምጥም መንገድ ተከትለን ስንጓዝ አፋፉ ላይ ፊቱን ወደባህሩ ያዞረ የጥንት ሰባራ መድፍ እናገኛለን ። መድፉ አጠገብ ከሁለት መቶ ዓመታት በፊት በደቾች የተገነባ አሮጌ ሕንፃ ይገኛል ። የምድር ቤት ክፍሎቹ ፀጥታ ሰፍኖባቸው ይታያሉ ። የባህሩ ሞገድ ከግድግዳቸው ጋር ይላተማል ። በመስኮቶቻቸው የአትላንቲክ ውቅያኖስ ከአድማስ አድማስ ወለል ብሎ ይታያል ።

በሚሊዮን ለሚቆጠሩና ወደ አሜሪካ ለተወሰዱ አፍሪካውያን ነፃነታቸው ያበቃውና ባርነት የጀመረው በዚህ ቦታ ነው ። ዛሬ በአሜሪካ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ጥቁሮች ምንጅላቶች እንደከብት እየተነዱ በጥርነት የተጋዙት ከዚህ ሥፍራ ነበር ። በዚህ ጨለማ ቤት ውስጥ አረቦች ጥቁሮችን እያጎሩ እንደከብት ሲሸጡ ሲለውጡ ኖረዋል። የአውሮፓ ባርያ ገዢዎችም መርከባቸውን እያስጠጉ ምርጥ ባሮችን ይሸምቱ ነበር ። ባሮቹ በዚህ ሕንፃ ምድር ቤት ከግድግዳ ጋር እንደ ከብት በሰንሰለት ታስረው ገዢ እስኪያገኙ ይቆያሉ ። ከዚያም በመርከብና በጀልባ ረጅሙን የባህር ጉዞ አጠናቀው ባርያ አሳዳሪ ጌታ የሚሆናቸው ግለሰብ ዘንድ ይደርሳሉ ። አፍሪካውያኑ በአህጉራቸው የመጨረሻዎቹን ሳምንታት የሚያሳልፉት እዚህ ቦታ ነው ።

ከባርያ መነገጃ ቢሮው ዝቅ ብሎ በሚገኘው መመዘኛ ክፍል የባሮቹ ጡንቻ ፥ የሴቶች ጡትና የሕፃናቱ ጥርስ ይመረመራል ። የሰው ልጅ የሚለካበት መመዘኛው ጡንቻ ፥ ጡት ፥ ጥርስ ነበር ማለት ነው። ስለዚህ በዚሁ ቆይታቸው ባሮቹን ፥ እንደከብት በማድለብ እያንዳንዱ ቢያንስ ሰባ ኪሎ ግራም እስኪመዝን ይቀለባሉ ። በሕመም ወይም በሌላ ምክንያት ክብደታቸው የሚፈለገው ደረጃ ላይ ሊደርሱ ያልቻ

ሉት በአረብ ዶክተሮች ውሣኔ ዋጋ እንደሌላቸው ተቆጥረው በጓሮ በር በኩል ወደ ባህር ይጣሉና የአሰነባሪ ራት ይሆናሉ ። የአመራረጡ ሂደትና አፈጻጸም ከሁለት መቶ ዓመት በኋላ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በናዚዎች የተደረገው ዓይነት ነው ።

ወደ ጎሬ ደሴት ከአሜሪካውያን ቱሪስቶች ጋር ሄጄ እንደተመለከትኳት ዛሬ ፀጥታ የሰፈነባትና ምንም ወንጀል የማይፈጸምባት ደሴት ናት ። አምስት መቶ የሚደርሱ ሰዎች ሲኖሩባት መኪናዎች የሉም ። የአፍሪካ ሕፃናት እንደተመለከቱን ወደ እኛ ሮጡና ጥቁሮች ቱሪስቶችን "ባርያ ተብላችሁ የተሸጣችሁበትን ቤት ላሳያችሁ?" እያሉ በየእግራችን ሥር ይሽከረከሩ ጀመር ።

የባርያ መሸጫው ቤት ከጥቂት ዓመታት በፊት ሙዚየም ሆኗል። የሙዚየሙ ኃላፊ ጆሴፍ ንዲያ አቀባበል አደረገልንና አስጎበኙን ። የውቅያኖሱ ማዕበል ዛሬም የሕንፃውን ግድግዳ ይለትማል ። ከሁለት መቶ ዓመት በፊት ከእኔ ጋር ያሉት ጥቁር አሜሪካውያን ቱሪስቶች ምንጅላቶች በዚህ ቤት ታጉረው በሚሸጡበት ጊዜም የባህሩ ሞገድ እንዲሁ ከግንቡ ሲላተም ነበር ። ያን ጊዜ "ፋይፍ ብራዘርስ ፣ ዲያኔ ፣ ሬጅና ኮክ ፣" የተሰኙ መርከቦችና፣ ሌሎችም ከዚህ ሥፍራ ባሮችን ሲያጓጉዙ ነበር ። ለዘለቄታው ከተወሰዱት ባሮች ውስጥ ከሰባት አንዱ በባህር ጉዞ ላይ ይሞት እንደነበር ይነገራል ።

በጎሬ ደሴት የባርያ መገበያያው ሕንፃ በዚህ መልኩ በታሪክ መታሰቢያነት የተጠበቀ ቢሆንም በሌሎች የአፍሪካ አገሮች ግን ተመሳሳይ ቤቶች አርጅተውና ፈራርሰው እንዲወድቁና የታሪክ ቅርስነታቸው እንዲጠፋ ሆን ተብለው ተትተዋል ። ለምሳሌ በዛንዚባር ደሴት ባሮች በጨረታ ይሸጡበት የነበረው የድንጋይ ግንብ አዳራሾች ዛሬ የአትክልትና ፍራፍሬ መሸጫ መደብሮች ሆነዋል ። በጋና ደግሞ የተሸጡ ባሮች መተላለፊያና መቆጣጠሪያ የነበሩት ማማዎች እየፈራረሱ ናቸው ። በናይጄሪያም የቀረ ነገር ቢኖር ጥቂት የባሮች ማሰሪያ ሰንሰለቶች የነበሩና ሀብሎችን ከግድግዳው ጋር ለማሰር የተጣበቁ ብረቶች ብቻ ናቸው ። በሴራሊዮን ባሮች ነፃነታቸውን በማወጅ ስብሰባ ያደርጉበት የነበረ ግዙፍ ዛፍ ዛሬም በዋናው አደባባይ



መሃል ይገኛል ፣ ነገር ግን ማንም ለታሪክ አሻራነቱ ግምት አይሰጠውም ። በዚህም የተነሳ የአፍሪካ ሕፃናትና አዲሱ ትውልድ የቆየ የባርያ ሽያጭ ታሪኩን በጎላ መልኩ ሳይሆን በጥቂቱ በእርግማን መልክ ብቻ እንዲያውቅ የተተወ ነው ። ብዙ አፍሪካውያን ማስታወስ የማይፈልጉት የታሪካቸው አንዱ ምዕራፍ ነው ።

ጥቁር አሜሪካዊ ጎብኝዎች ስለጥንቱ አባቶቻቸው አሻሻጥን ሲያስረዳቸው ቤትክርስቲያን እንደገባ ሰው በፀጥታ ያዳምጣሉ ። ንድያም እያዘዋወረ በየክፍሉ ለሶስት ምዕት ዓመታት ስለተካሄደው የባርያ ሽያጭ ሁኔታ አስረዳን ። የሰው ልጅ እንደ ዕቃ በሰንሰለት ታስሮ እየተነረተ እንዴት ይሸጥ እንደነበረ የፍርድ ቤት አቃቤ ሕግ ዓይነት ገለጣ አደረገልን ። ለማምለጥ የሞከሩ ባሮች ቋንጃቸው እንደሚሰነከልና ጅማታቸው ተስቦ አንካሳ እንዲሆኑ እንደሚደረግ አስረዳን ። እየጮሁ የሚያስቸግሩ በብረት ቀለበት ከንፈራቸው ይለጠጥና አፋቸው ይታሸግ ነበር ።

ከኒውዮርክ የመጡት አንድ ጎብኚ ጌራልዲን ፌር እንዲህ ሲሉ የተሰማቸውን ገለጡልኝ ። "ምን እንደሚሰማኝ ለማወቅ ገና ብዙ አላብሰለሰልሁትም ። ሆኖም በታሪክ ከሚያስተምሩን ብዙ ልዩነት አለው ። ሲነግሩን የኖሩት ግማሹን እንኳ አይሆንም ። እዚህ በዓይን እያዩ የመረዳቱን ያህል የሚሆን የለም ። ምዕራብ አፍሪካን ማየት ፣ የጎሬን ደሴት መመልከት ፣ ለእኔ ማንነቴን እንድረዳ ፣ ሥር መሠረት ያለኝና ቅድመ አያቶቼ የመነጩበት የራሴ እናት ሀገር እንዳለኝ በጥልቀት እንድገነዘብ አድርጎኛል ።"

ትክክለኛው ቁጥር ተመዝግቦ ባይገኝም ከአሥራ ስድስተኛው እስከ አሥራ ዘጠነኛው ምዕት ዓመት ከምዕራብ አፍሪካ ወደ አሜሪካ የተወሰዱት ባሮች ቁጥር ከ10,000,000 እስከ 15,000,000 እንደሚደርስ ይታመናል ። በ1790 የባርያ ንግድ ስለተጧጧፈ በዓመት 70,000 ያህል አሜሪካ ይራገፉ ነበር ። ከምሥራቅ አፍሪካ ደግሞ ከ1770 እስከ 1896 ባርያ ሽያጭ ቀጥሎ እስከ 3,000,000 ሊደርሱ የሚችሉ ባሮች በአብዛኛው ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ተወስደዋል ። አንዳንድ የታሪክ ፀሐፊዎች በጠቅላላ ከአፍሪካ በሽያጭ የተጋዙት ባሮች ቁጥር 50,000,000 እንደሚደርስ ይናገራሉ ።

ባርያ አሳዳሪነት በአሜሪካ እንደ ተቋም የተመሠረተው ዘግይቶ ነው ። የመጀመሪያዋ ባሮች የጫነች መርከብ ዩናይትድ እስቴትስ የደረሰችው በ1619 ሲሆን ፣ እስከ 1681 ድረስ በአሜሪካ 2,000 ባሮች ብቻ ነበሩ ። በአሽከርነት የተወሰዱ አውሮፓውያን ቁጥር ደግሞ 6,000 ነበረ ። ሆኖም አሜሪካ ለጥጥ እርሻ ለትንባሆ ተክልና ለሸንኮራ ተክል ልማት ብዙ ርካሽ የሰው ጉልበት ስላስፈለጋት የባርያ ንግድ ወዲያው ተፋፋመ ። ስለዚህም በ1860 ማለትም በእርስ በርስ ጦርነቱ ዋዜማ የአሜሪካ ባሮች ቁጥር 4,400,000 የነበረ ሲሆን ፣ ጠቅላላ የአሜሪካ ሕዝብ ብዛት 36,000,000 ነበረ ። ይህም አኃዝ የሚያመለክተው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከቅርብ ጊዜ የባሮችና የነጮች ቁጥር ሲነፃፀር በመቶ ያው መሆኑን ነው ። ከ1860 እስከ 1970 ከአሜሪካ ሕዝብ ጠቅላላ ቁጥር የጥቁሮች ብዛት ስምንት ነጥብ አንድ በመቶ ነበር ። በ1980 ወደ አሥራ አንድ ነጥብ ሰባት በመቶ ከፍ ብሏል ።

ለባርያ ሽያጭ መስፋፋት ወንጀል ተጠያቂ የሚሆኑት ሁሉም ወገኖች ማለትም ነጮች ፣ አረቦችና አፍሪካውያን ራሳቸው ጭምር ናቸው ። ምክንያቱም በአብዛኛው ባርያ ነጋዴ አረቦች ባሮችን የሚገዙት ወደ አፍሪካ አህጉር መሀል ገብተው ሳይሆን የአፍሪካ የጐሳ መሪዎችና ንጉሶች እስከ ወደብ እያመጡ ስለሸጡላቸው ነው ። የአፍሪካ ንጉሶችና የጎሳ መሪዎች ደግሞ ይህን ያደረጉት እየተለወጠ በሚሄደው ዓለም ውስጥ አንዳንድ የሚያጓጓቸውን ነገሮች ማለትም እንደ ልብስ ፣ ጌጣጌጥ ፣ ሲጋራ ፣ መጠጥ ፣ ጠመንጃ ፣ ብረታብረት ፣ ወዘተ . . . የመሳሰሉትን ለማግኘት ሕዝባቸውን መለወጫ ስላደረጓቸውና ለሽያጭ ስላቀረቡ ነበር ። ይህም የባርያ ንግድ በአህጉሩ መሃል ያሉ ንጉሶችን ሀብታም ሲያደርጋቸው በወደብ ዳርቻ ደግሞ አዲሱን የአፍሪካውያን ነጋዴዎች መደብ ፈጠረ ።

በዚያን ዘመን በአፍሪካ ውስጥ የነበሩ ጦርነቶች ለሀብትና ለሥልጣን ሲባል የሚካሔዱ ነበሩ ። የመሬት ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ዝቅተኛ ነበር ። ምንም እንኳን የግዛት ማስፋፋትና የተፈጥሮ ሀብቶችን መቆጣጠር ጠቀሜታው ባይናቅም በዚያን ዘመን ዋናው የጥንካሬ



መለኪያ የሰው ኃይል ነበር ። በዚህም የተነሳ የጦርነቶች ዓላማ ተጨማሪ መሬት ለመቆጣጠርና የቆየ ቂምን ለመበቀል ከመሆኑ ሌላ የተከታዩን ሕዝብ ቁጥር ለማብዛትም ነበር ። በባርነት የሚሸጡት ጥቁሮችም በአብዛኛው በጦርነት የተማረኩ ነበሩ ። የቀሩት ደግሞ ወንጀል የፈጸሙ ፣ ዕዳ ያልከፈሉና ሌሎች በተለያዩ ምክንያቶች ያፈነገጡትና የተናቁ ሰዎች ነበሩ ። አንዳንዶቹም ሳያውቁ የጐሣቸውን ክልል አልፈው በመገኘት የተማረኩ ምስኪኖች ናቸው ። ያም ሆነ ይህ ባርያ ሽያጭን ያመጣው ራሱ አፍሪካዊው ነው ማለት ይቻላል ። የራሱን ሰዎች እየያዘ ለዓረቦች ይሸጥ ይለውጥ ጀመር ። ዓረቦች ደግሞ በተራቸው ለአውሮፓውያን መሸጥ ጀመሩ ። ስለዚህ የዚህን አሳፋሪ ተግባር ኃላፊነት ሶስቱም ተካፋይ ናቸው ።

አውሮፓውያን በበኩላቸው ባሮችን ለመሰብሰብ የቻልነው በአፍሪካ የተለመደ የእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት ነው ይላሉ ። አረመኔ ንጉሥ ከሚገድለው ፣ የሰለጠነ ክርስቲያን ባርያ አሳዳሪ ማግኘቱ ይሻለዋል ቢሉ የተሻለ ይሆን ነበር ። አብያተ ክርስቲያናት የሰውን ልጅ መሸጥ መለወጥ ሞራላዊ ወንጀል አልኮነኑም ። በአውሮፓ ከ1700 ጀምሮ አልፎ አልፎ ተቃውሞ ቢሰማም የአንድ አህጉር የሰው ኃይል ሀብት ሲዘረፍ ተከታታይነት የነበረው ክርክር አልተሰማም ።

የሚያስደንቀው ደግሞ ባርያ ሽያጭን ለማስቀረት እርምጃ የተወሰደው በአፍሪካ ውስጥ ሳይሆን ከአፍሪካ ውጭ ነው ። በ1803 ዴንማርክ ዜጎችዋን ከባርያ ንግድ እንዲታቀቡ ከለከለች ። እንግሊዝ ደግሞ በ1807 ተመሳሳይ እገዳ አወጣች ። አሜሪካ በበኩልዋ በ1808 ፈረንሳይ ደግሞ በ1818 ተመሳሳይ ርምጃ ወሰዱ ። ያም ሆኖ ግን አሜሪካ ባርያ መግዛትዋን ቀጠለች ፤ አፍሪካውያንና አውሮፓውያን ይህን ከፍተኛ የገቢ ምንጭ መዝጋት ስላልፈለጉ ባርያ ሽያጭ በመላው ዓለም ቀጠለ ። እንግሊዝ ግን አቋሟን አጠንክራ ውሳኔዋን ተግባራዊ በማድረግ ባርያ የሚያጉዙ መርከቦችን ለማስቆምና ለመፈተሽ ሃያ የጦር መርከቦች በምዕራብ አፍሪካ ዳርቻ በማሰማራት ተጽዕኖ ማድረግ ጀመረች ። በዚህም እንቅስቃሴ ከ1825—1865 እንግሊዝ 1,287 መርከቦችን በማሰር 130,000 ባሮችን ነፃ አውጥታለች ። እንዲያም

ሆኖ በዚያው ጊዜ ውስጥ 1,400,000 ባሮችን የያዙ መርከቦች ሾል
ከው ለማለፍና አሜሪካ ለማራገፍ ችለዋል ።

ለባርያ ሽያጭ መቆም ወሳኝ ጉዳይ የሆነው የአሜሪካ የእርስ
በርስ ጦርነትና በዚያም ፍፃሜ የባሮች ነፃነት መታወጁ ነው ። ከዚያ
በኋላ የቀሩት ባርያ ገዢ አገሮች ኩባና ብራዚል ብቻ ስለነበሩ ሁለት
ገበያዎች ብቻ መቅረታቸው ለነጋዴዎች አስጊ ስለሆነ ተዳከመ ።
ስለዚህም በአፍሪካ አንድ አሳዛኝ የታሪክ ወቅት ተደመደመ ። ወዲ
ያው ደግሞ ሌላው ጭቆናና አፈና ቅኝ ግዛት በሚል ስያሜ ይጀ
ምራል ።

ባርያ ሽያጭ የኋላኋላ በአፍሪካ ላይ ስላስከተለው ችግር የቀረበ
ዝርዝር አላጋጠመኝም እንጅ በመሠረቱ ሃምሳ ሚሊዮን ሕዝብ አብ
ዛኞቹ ወንዶችና በእድሜ ወጣትና ጐልማሳ የሆኑ ማጣትዋ ያደረ
ሰባት ጉዳት ቀላል አይሆንም ። ይህ የሰዎች ገፈፋ በአፍሪካ እስከ
ዛሬ ኢኮኖሚያዊ ፡ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ተጽዕኖ ማስከተሉ እው
ነት ነው ። በአፍሪካ የሰው ቁጥር መቀነስ በኢኮኖሚዋ ላይ ያስከ
ተለው ችግር ቀላል ነው ሊባል ይቻላል ። ኤኮኖሚዋ ከእጅ ወደ
አፍ በመሆኑና በዚያው የቀሩት ሴቶችም በብዛት መውለድ ስለቀ
ጠሉና በቂ መሬትም ስላላቸው አልተጎዱም ይባል ይሆናል ። ሆኖም
አፍሪካ ጠንካራ ጡንቸኛ ዜጎቿን ተዘርፋለች ። ቤተሰቦች በዚሁ ምክ
ንያት ተበታትነዋል ። ጎሳዎችም ጦረኞቻቸው የደረሱበት ጠፋባቸው ።
ነጮች አስፈሪ ፡ ኃያልና የበላይ ሆነው ታዩ ። ጨካኝ ስለነበሩ ተፈሩ፤
ኃይለኛም ስለነበሩ ተከበሩ ። ይህ ሁኔታ መፈጠሩ በአፍሪካውያን ላይ
ያሳደረው የሥነልቦና ተጽዕኖ እጅግ አጥፊ ነው ።

አውሮፓ ቅኝ ግዛቷን ማስፋፋት ስትጀምር በአረብ አፍሪካ
ጠንካራ የመከላከል ተቃውሞ ገጠማት ። ፈረንሳይ ቱኒዝያን ለመቆ
ጣጠር 30,000 ወታደር አስፈለጋት ። እንግሊዝ ሱዳንን ለመቆጣጠር
አሥራ ሁለት ዓመት ያህል የጦርነት አደጋ አልተለያትም ። ጥቁር አፍ
ሪካ ግን ለነጭ ገዢዎች በቶሎ እጅ መስጠትዋ የሚያሳፍር ነበር ።
ያለትግልና ጦር ሳትሰብቅ ቀስት ሳታቃና እጅ ሰጠች ። አፍሪካ ከው
ጭው ዓለም ጋር ባላት ግንኙነት የመጀመሪያዎቹ የጥርጣሬና የዝቅ



ተኝነት ዘሮች ተዘሩ ። አፍሪካ ቀድሞውኑ የባርያ ንግድን ተቃውማ
ብትቋቋም ኖሮ የቅኝ አገዛዝ ዘመን ወደጠረፎችዋ ባልተስፋፋም
ነበር ። ይህም ሆነ ፤ የአፍሪካ ታሪክ ሂደት ተለወጠ ።

አንድ ጊዜ ከአንድ ጋምቢያዊ የመንግሥት ሠራተኛ አብዱላ
ሴካ ጋር "ሩትስ" የሚለውን መጽሐፍ የፃፈው አሌክስ ሀሊ ሥር
መሠረቱን ወደአጠናባት ጁፋር ወደተባለች ሥፍራ በጋምቢያ ወንዝ
ላይ በጀልባ ስንጓዝ አመለካከቱን አጫወተኝ ። "አንዳንድ ጊዜ ተቀ
ምጬ ሳስብ ከሁለት መቶ ዓመት በፊት ተወልጄ ቢሆን ኖሮ የእኔና
የቤተሰቤ ሕይወት ምን ይመስል እንደነበረ አሰላስላለሁ ። ልገምተው
አልችልም ። ምናልባት አንድ ሰው እኔን ራሴን ወይም ልጆቼን ለመሸጥ
ይሞክር ይሆናል ። ወይም እኔ ራሴ ሌላውን በመሸጥ በለው ጡ መጠጥ
ወይም ጌጥ እገዛበት ይሆናል ። ጊዜው ሩቅ ስለሆነ እንዲህ አደርግ
ነበር ብሎ ለማሰብ ያዳግታል ። ከአሁን ወዲያ የምናስበው አይደለም።
እግዚአብሔር ደግ ነውና ያለፈውን እንድንረሳ አድርጎናል "በማለት
አወጋኝ ። በነገራችን ላይ "ሩትስ" የተሰኘው መጽሐፍ በሃያ ሚሊ
ዮን ቅጅ ተሸጧል ፤ በሰላሳ ሁለት ቋንቋዎች ተተርጉሟል ።

አፍሪካ የጥንቱን ልትረሳ አትችልም ። ሃያ አምስት ሚሊዮኑ
የአሜሪካ ጥቁሮችም አፍሪካ የሩቅ እናት ሀገራቸው ፡ እጆቿን ዘርግታ
ልጆቿን የምትጣራና የጥቁርን ክብር ፡ የባህል ፍቅርን ፡ የእኔ እነት
መታወቂያቸውን ለማላበስ ቃል የምትገባላቸው ስለሆነች የጥንት መሠ
ረቷን አይረሱትም ። ባለፉት አሥርት ዓመታትም በአሥር ሺዎች
የሚቆጠሩ ጥቁር አሜሪካውያን ይህን ጥሪዋን መልሰዋል ። በዚያ
ጊዜ ራስን ከመውቀስና ራስን ከመጥላትም በራስ መኩራትን ፡ በራስ
መደሰትን ፡ የጥቁር መሠረታቸውን የማድነቅን አመለካከት አጎለበቱ ።
ወደአፍሪካ መመለስ ለአንዳንድ አሜሪካውያን ያስደስታቸዋል ፡ ለሌ
ሎችም በሕልም ዓለም ከመኖር ይገላግላቸዋል ። ዞሮ ዞሮ ሁሉም
የሚስማሙበት ግን አፍሪካ እናት ምድራቸው ስትሆን ዩናይትድ
እስቴትስ ደግሞ ቤታቸው መሆኗን ነው ።

በምዕራብ አፍሪካ ለዓለም የጤና ድርጅት ሃያ ያህል የጤና
ፕሮግራሞችን ሲያስፈጽሙ ለብዙ ዓመታት በዚያ የቆዩት አሜሪካዊ

ዶክተር ዴቪድ ፍሬንች ከልምዳቸው የተገነዘቡትን አጫወቱኝ ። "በመጀመሪያ ደረጃ እንደ አሜሪካዊ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እንደ ጥቁር ነው የምንታየው ። ከዘጠኝ ዓመት በፊት አፍሪካን መጀመሪያ ስጎበኝ አፍሪካውያን ጥቁር አሜሪካውያንን የሚንቁ መስሎ ተሰማኝ። አሜሪካ ሄደን ስለቀረንና ለሶስት መቶ ዓመታት በዚያው ስለቆየን ተጠርጣሪ ሆነናል ። አሁን ሳጤነው ግን አፍሪካውያን የተማሩ ጥቁሮች የት ናቸው ያሉት? የሚል ጥያቄ እያነሱ ነው ። ዩናይትድ እስቴትስ ያሉት ከሆኑ ለምን መጥተው የእድገት ጥረታችንን አያግዙም? እያሉ ናቸው ።

አባባሉ ተገቢ ቢሆንም ጥቁር አሜሪካውያን በብዙ አገሮች ተቀባይነታቸው እስከዚህም አይደለም ። ለምሳሌ ስለአብዮት ለማጥናት የማኦ ማኦ ትግል ወደተጀመረባት ኬንያ የሄዱ ጥቁር አሜሪካውያን በመንግሥትም በሕዝብም ቸል ተብለውና መሳለቂያ ሆነው መመለስ ግድ ሆኖባቸዋል ። ሕዝቡ የዕለት ጉሮሮውን ለመሙላት መሯሯጥ እንጂ ስለፈለጉት አርእስት ጉዳይ ሊያወጋቸው ምቾቱ የለውም ። ስለዚህም አብዮት በነፃ ሕዝብ መካከል የሚወራ የንዑስ ከበርቴው መደብ የቅንጦት ተግባር ሳይሆን አይቀርም የሚል ግንዛቤ አድሮባቸው ተመለሱ ።

በኢትዮጵያ ለጉብኝት የሄዱት ጥቁር አሜሪካውያን ደግሞ የሰላም ልዑካንን (ፒስኮር) ጨምሮ በሕዝቡ ተናቁ ። ልክ ጥቁር አፍሪካውያንን እንደሚንቁት ኢትዮጵያውያኑ ጥቁር አሜሪካውያንንም ተጠየፏቸው ። ኢትዮጵያውያን ቆዳቸው ፈካ ያለና ፊታቸው እንደ አውሮፓውያን ስልክክ ያለ በመሆኑ ጥቁሮችን ይንቃሉ ። አሜሪካ ጥቁር ዲፕሎማቶችን ስትልክ ወይም ስትመድብ የአፍሪካ መንግሥታት ደስ አይላቸውም ። የተናቁና ደካማ ሰዎች የተላኩላቸው ስለሚመስላቸው ነው ። አንድ ጊዜ በኬንያ የአሜሪካ አምባሳደርም ፣ የፒስኮሮች ኃላፊም ፣ የእርዳታ ድሬክተሩም ጥቁሮች ስለነበሩ አንድ ኬንያዊ ኮክቴል ላይ አግኝቶኝ"አሜሪካ ደካማ ጥቁሮችን ትታ ለምን ጎበዝ ዲፕሎማቶችን አትልክልንም" በማለት ጠየቀኝ ። አባባሉ ትክክል አልነበረም ። አፍሪካውያን አሁንም በቅኝ ተገዢነት አስተ



ሳሰብ ስለተተበተቡ ነጮች ከጥቁሮች ይበልጣሉ ብለው ስለሚያስቡ እንጂ ጥቁር ዲፕሎማቶች ከነጮች አይተናነሱም ። በሁሉም የሙያ ዘርፍ ከፍተኛውን ቦታ ነጮች ይዘው ስለቆዩና በሙያተኝነትም እየተላኩ ስለሚያስተምሩና ስለሚሰሩም ይህ ዓይነት አስተሳሰብ ቢያድርባቸውም አይፈረድባቸውም ።

በአፍሪካ የግለሰብ ነፃነት ብዙዎቹ የማያገኙት ትልቅ ስጦታ ስለሆነ ጥቁር አሜሪካዊ የበለጠ ክብር ፣ ነፃነትና ዋስትና በአገሩ ላይ ሲኖረው አፍሪካውያን ግን በአገራቸው የላቸውም ። "ጥቁር አሜሪካውያን ወደ አፍሪካ እንምጣ ወይ ብለው ሲጽፉልን" አለኝ አንድ በምዕራብ አፍሪካ የሚኖር ክሊፎርድ ሻርፕ የተባለ ጥቁር አሜሪካዊ ሜካኒክ ፤ "ለመዝናናት አስባችሁ አትምጡ ፣ የበላይነት ስሜት ካላችሁ አትምጡ ፣ ያለችግር ለመኖር ከሆነ ሃሳባችሁ አትምጡ ፣ አፍሪካን በእድገት ጥረትዋ ለመርዳት ካሰባችሁ ግን የማገዝ ስሜትና የሚሲዮኖች የመንፈስ ጥንካሬ ኖሮአችሁ ብትመጡ መልካም ነው። ምክንያቱም በየዕለቱ አንዳንድ ችግሮች እንደሚያጋጥሟችሁ የታወቀ ነው" ብዬ እመልስላቸዋለሁ በማለት አስረዳኝ ።

ሻርፕ ከነሚስቱ ወደ ኮናክሪ የመጣው ጥቁር ፕሬዚዳንት በሚመራት አፍሪካዊ የጥቁር አገር ለመኖር ክብር ስለተሰማው ነው ። የአሜሪካ ፓስፖርታቸውን እንደያዙ መቆየቱን ቢመርጡም በአፍሪካ በመኖራቸው ይኮራሉ ። እዚህ የመጡት ለሶስት አገሮች በነዋሪነት እንዲቀበሏቸው ከጠየቁ በኋላ ናይጄሪያ መልስ ስላልሰጣቸውና ጋና ደግሞ መመዘኛውን አታሟሉም የሚል መልስ ስለላከላቸው ነው ። ኮናክሪ እንደገቡም ፕሬዚዳንት ሴኩቱሬ ተቀብለው ስላነጋገሯቸው በኩራት ያወጉታል ። ስለፖለቲካ ግድ ስለሌላቸው ብዙም አይጨነቁም ።

በኬንያ የባህር ጠረፍ በሞምባሳ የበልግ ወራት ሲገባደድ እንቅስቃሴ ይቀዘቅዛል ። የሚተነፍሱት አየር ያጥራል ፣ ይወብቃል ። በዚያ የሚገኙ ዕቃ ጫኝዎች የደረቀ ዓሣ መያዣ ሣጥን ተሸክመው ራቁታቸውን በአሸዋማው የባህር ዳርቻ ይዳክራሉ ። ከፍ ብለው የቆሙት የእንጨት ጀልባዎች ላይ ያሉት ሕንዶችም የመጨረሻውን የወቅቱ

ዓሣ ጭነው ወደ ሕንድ ለመጓዝ በጉጉት ይጠባበቃሉ ። የእንጨት ጀልባዎች በሰሜን ሕንድ ውቅያኖስ ሲመላለሱና አፍሪካን ከሕንድና ከፋርስ ባህረሰላጤ አገሮች በንግድ ሲያገናኙ ኖረዋል ። በጥንት ጊዜ እነዚህ ጀልባዎች ወደ አፍሪካ ጠርሙሶችና የብረታብረት ውጤቶች እያመጡ ፤ ሲመለሱ ደግሞ ባሮች ፥ የዝሆን ጥርስ ፥ የእንስሳ ቆዳዎችና የደን ውጤቶች ይዘው ወደ አረቢያ ይመለሱ ነበር ። በዚህ ቦታ ጥንት ፖርቱጊዞች የሰሩት መመልከቻ ከፍታ ቦታ ያለ ሲሆን ፥ በአሥራ አራተኛው ምዕት ዓመት የተገነባ ነው ። ባለጀልባዎች እዚያ ሲደርሱ ከመመልከቻው ላይ ባንዲራ እያውለበለቡና ከበሮ እየደለቁ ይቀበሏቸዋል ። ባለ ጀልባዎቹም እንደደረሱ በደስታ እጃቸውን ዘርግተው አምላካቸውን እያመሰገኑ ቀደም ብለው ደርሰው የሚጠባበቁ ጓደኞቻቸው ጋር ሰላምታ ይለዋወጣሉ ። ይህ የሞምባሳ ወደብ ከዳር እስከዳር በጀልባዎች ስለሚጨናነቅ የውቅያኖሱን ውሃ ለማየት ያዳግታል ። . . .

እስከ 1945 ድረስ በየዓመቱ ከአራት መቶ የሚበልጡ ጀልባዎች ይጐበኙታል ። በኋላ ግን የንግድ መስመሮችና ገበያዎች ተለወጡ ፤ የትራንስፖርት መገልገያዎች ወደ አውሮፕላን ተቀየሩ ። ፈጣን የሞተር ጀልባዎችና መርከቦች ተሰማሩ ። ስለዚህም የእነዚህ የእንጨት ጀልባዎች ቁጥር እየቀነሰ መጣ ። ዛሬ አምስት ሳምንት የሚወስደውን ከኩዌት ወይም ከቦምቤይ ሞምባሳ ጉዞ የሚያደርጉት በዓመት ከአሥራ ሁለት የማይበልጡ የእንጨት ጀልባዎች ናቸው ። እንደቀድሞው በሆታ የሚቀበላቸው ባለጀልባ በሌለበት ፀጥ ያለ ወደብ በቀስታ ይጠጋሉ ። ጊዜው አልፎባቸዋል ፥ በታሪክ ያላቸው ሚና ግን እንደተጠበቀ ነው ። ምክንያቱም እነዚህ ጀልባዎች የአፍሪካን ባህርይ በመለወጥ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሌሎች የውጭ ሕዝቦች ተምሳሌት ናቸው—እስያውያን ። በአፍሪካ እስያዊ የሚባሉት ጠየም ያለ ቀለምና ሉጫ ፀጉር ያላቸው ሲሆኑ ፥ ሕንዶችን ፥ ፓኪስታኖችንና ሌሎችንም ያጠቃልላል ።

ከአንድ ምዕት ዓመት በላይ እስያውያን በአፍሪካ የኖሩት ከሁለቱም ሳይሆኑ ነው ። በከፊል በሕጋዊ ዜግነት ፥ በከፊል በስደተኛነት ነው።



ከአንዱም ሳይሆኑ የኖሩ ናቸው ። ነጋዴና ጀልባ ቀዛፊ ሆነው የመጡ ናቸው ። አንዳንዶቹም ለአውሮፓውያን በአሽከርነት የመጡ ሲሆን አውሮፓውያኑም ሆኑ አፍሪካውያኑ በወዳጅነት አልተቀበሏቸውም ። አውሮፓውያኑ በንቀት ፥ አፍሪካውያኑ ደግሞ በጥርጣሬ ፥ ይመለከቷቸዋል ። እንዲያም ሆኖ አዲሱ ዓለም ላቀረበላቸው ፈተና አልተበገሩም ። እንዲያውም አፍሪካውያን መሥራት የተሰሳናቸውን እያከናወኑ ቀጠሉ ። እንቅፋቶቹን ሁሉ አልፈው ነጭ ያልሆኑ የአፍሪካ ሙያተኞችና የገንዘብ ደላሎች ሆኑ ።

ሕንዶች በ1700 አካባቢ በጀልባዎቻቸው ወደ ምሥራቅ አፍሪካ መጡና በኬንያ ጠረፍና በዛንዚባር የንግድ ሱቆች ከፍተው ንግዱን በበላይነት ያካሂዱ ጀመር ። ብዙዎቹ ባርያ አቀባባዮች ነበሩ ። ሌሎች ወደ መሐል ተጉዘው ገቡ ። ትናንሽ ሱቆች በመክፈት በምሥራቅ አፍሪካ ጠቃሚ አገልግሎት ማበርከት ጀመሩ ። የምሥራቅ አፍሪካ የገጠር ሕዝብ የተዋወቃቸው የመጀመሪያዎቹ የውጭ ዜጎች ሆኑ ። እስያውያኑ አፍሪካውያኑን ሰነፍ አድርገው በመቁጠር በድንቁርናቸው ለማትረፍ ወደኋላ አላሉም ።

ባርነት ሲወገድና አፍሪካውያኑ በእርሻዎች ላይ የጉልበት ሥራ ለማበርከት አሻፈረን ሲሉና በከፍያ እንኳን ለመሥራት እምቢተኞች ሲሆኑ ፥ በሺህ የሚቆጠሩ ሕንዶች በእንግሊዞች ተቀጥረው ለቀን ሠራተኝነት ወደ ምሥራቅ አፍሪካ መጡ ። በ1896 ከሕንድ 32,000 ሰዎች ተወሰዱና ከሞምባሳ ወደ ኡጋንዳ የሚወስደውን ባቡር ሐዲድ ዘረጉ ። ይህም ምሥራቅ አፍሪካን ለአውሮፓ ሠፋሪዎች አመቻቸት ። ሌሎች ደግሞ ወደ ሞዛምቢክ ተወስደው ከቢየራ ወደ ዚምባብዌ የሚወስደውን ሐዲድ ገነቡ ። በሽታ ፥ ሙቀትና ወባ እንዲሁም አውሬ በሺህ የሚቆጠሩትን ገደለ ።

ከሁለቱ የዓለም ጦርነቶች በኋላ እንግሊዞች በሺህ የሚቆጠሩ እስያውያንን ወደ ምሥራቅ አፍሪካ እንዲመጡ በማበረታታታቸው የተሻለ ኑሮ ፍለጋ በብዛት ፈልሰው መጡ ። ቅኝ ገዢዎችም ለሕንዶችና ለአፍሪካውያኑም የመኖሪያና የንግድ ክልል ለይተው በመስጠት “የአውሮፓን የአኗኗር ዘይቤ” እስኪለምዱ ድረስ ለንፅህና

ሲባል ያንን ማድረጋቸው ትክክል እንደሆነ አድርገው ተከራከሩ ። ሠራተኞችና ቆጣቢዎች ፣ ይሉኝታ የሌላቸው ነጋዴዎች በመሆናቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ የምሥራቅ አፍሪካን ኤኮኖሚ ተቆጣጠሩት ። ነጋዴም ፣ ወርቅና ብር ሠሪም ፣ የፋይናንስ ኃላፊም በመሆን እያሌ ሀብት አካበቱ ። አፍሪካውያን እሲያውያንን በዝባዥ አድርገው ሲቆጥሯቸው ፣ እሲያውያኑ ደግሞ አፍሪካውያንን ሰነፍና ዝቅተኛ አድርገው ተመለከቷቸው ።

"ብፈልግ ነገ ከምንም ተነስቼ በሶስት ዓመት ውስጥ እንደገና ሀብታም እሆናለሁ ። አፍሪካውያን በሥራና በንግድ ዘርፍ ደካማ ተፎካካሪዎች ናቸው ። እንደኛ መሥራት አያውቁበትም ። እኔ በበኩሌ በቀን አሥራ አራት ሰዐት ብሰራ ወይም ቅዳሜና እሁድም ያለዕረፍት ብሠራ ግድ የለኝም ። "ይህን ያጫወተኝ በሶማሊያ የሚኖር እስያዊ አንጥረኛ ነው ።

በ1950ዎቹ የሕንድ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ኔህሩ በአፍሪካ ያሉት እሲያውያን ለአፍሪካውያን የብሔረተኝነት እንቅስቃሴ ድጋፍ እንዲሰጡ ገፋፉ ። ነገር ግን ያን ያደረጉ እጅግ ጥቂቶች ነበሩ ። የቅኝ አገዛዝን አስከፊነት የሚገነዘቡ ቢሆንም በዚያ ሥርዓት ሥር ሰርተው መከበርን ስለተማሩና ነፃነት ከመጣ አፍሪካውያኑ ጥቅማቸውን ሥጋት ላይ ሊጥሉት እንደሚችሉ በመሥጋት ችላ አሉ ።

በኋላም እስያውያን ዜግነታቸውን ለመለወጥ ባለመፈለግ ልክ እንደ ነጮቹ ቆይተው ሁኔታውን ለማጤን መምረጣቸው የአፍሪካውያኑን ጥርጣሬ አረጋገጠ ። እውነትም እስያውያኑ አዲሶቹን ነፃ የአፍሪካ አገሮች በሙሉ ኃይላቸው ለማገዝና ለመገንባት ብሔራዊ ስሜቱ እንደሌላቸው በግልጽ ታየ ።

በ1970ዎቹ ብዙ መንግሥታት ኤኮኖሚውንና የሥራ መስኩን ሁሉ በአፍሪካውያን ለማስያዝ ባደረጉት ጥረት እስያውያኑ በያለበት ተዋከቡ ። እንዲያውም የእስያውያን መኖር ችግር ማስከተሉ ተስተዋለ ። በኡጋንዳ በ1971 እስያውያን በሙሉ እንዲቆጠሩና ተሰልፈው በየመንደሩ በጣታቸው እንዲፈርሙ ተደረጉ ። በጣታቸው አሻራ



እንዲፈርሙ የታዘዙት ሆን ተብሎ ለማበሳጨት ነበር ። እንግዲያው መፃፉንማ ከአስፈራሚዎቻቸው በተሻለ ያሞናሙኑታል ።

ከአሥር ወራት በኋላ ፕሬዚዳንት ኢዲ አሚን በኡጋንዳ የሚገኙ እስያውያን በዘጠና ቀናት ውስጥ አገሪቱን ለቀው እንዲወጡ በማዘዝ "የአገሪቱን አኮኖሚ መቆጣጠር ያለባቸው የኡጋንዳ ተወላጆች ናቸው" ሲሉ አወጁ ። ሰባ ሺህ እስያውያን አንድ ሶስተኛው ዜግነታቸውን ኡጋንዳዊ ያደረጉ ጭምር ከቤት ንብረታቸው ተባረሩ ። የታንዛንያና የዛምቢያ መሪዎች ርምጃውን ቢነቅፉም እስያውያኑ መድረሻ አጥተው ሲቅበዘበዙ በማየታቸው አፍሪካውያኑ ተደስተው በታል ፤ እስያውያኑም ቢሆን ብዙዎቹ ከበዘበዙት አኳያ ሲታይ ሲያንሳቸው መሆኑን አላጡትም ።

ማላዊ ደግሞ በ1970ዎቹ ትምባሆ የሚያበቅሉ እስያውያንን ፈቃድ ሰረዘች ። ታንዛንያም ንግዳቸውንና የቃጫ ተክላቸውን ወረሰች ። ደቡብ አፍሪካም እስያውያንን ሁለተኛ ዜጋ አድርጋ በይፋ አረጋገጠች ። በዚያ የነበሩ አንድ ሚሊዮን እስያውያን ተደናገጡ ። ኬንያም የእስያውያን ንብረት የሆኑ በሺህ የሚቆጠሩ ሱቆችን ወረሰችና በገጠሩ አካባቢ ምንም ዓይነት ሥራ እንዳያካሄዱ ከለከለች ። የኬንያ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ማርቲን ሹኩኩ "እስያውያን አገራቸው ይሂዱ" የሚል መፈክር በማሰማቱ የሕዝብን ስሜት ሳበ ።

በእነዚያ ዘመናት በግልጽ የታየው ነገር እስያውያን በአፍሪካ ምንም ተስፋ እንደሌላቸው ነው ። በገነቡት ሀገር ባይተዋር ሆኑ ። ስለዚህም የመጨረሻ ዕድላቸው በአዲሶቹ ጥቁር ፕሬዚዳንቶች እጅ ስለሆነ ሻንጣቸውን ቀርቅበውና ገንዘባቸውን በውጭ ባንኮች እያኖሩ የሚባሉትን በተጠንቀቅ መጠባበቅ ሆነ ። አንድ ሚሊዮን ተኩል የሚሆኑ እስያውያን በቀላሉ የተጋለጡ ፣ ለአደጋ የተመቹ ሕዳጣን ሆነው ታዩ ።

ዛሬ ግን ያ ሁሉ መዋከብና ተጽዕኖ ረግቦላቸዋል ። የእስያውያኑ በኤኮኖሚው መሳተፍ ገንቢ አስተዋጽኦ እንዳለው ታይቷል ። በተለይም እስያውያን በወጡበት በኡጋንዳ የኤኮኖሚ መንኮታኮት

በመከተሉ አመለካከቱን አለዝቦታል ። አፍሪካውያኑም ቢሆን ዛሬ እንደዚያን ጊዜ በእስያውያን ተገፋን ብለው አይሰጉም ።

አንድ በኬንያ የሚኖር እስያዊ ሱኒ እስላም አብዱል ሀሚድ ያለፈው ዓይነት ሕንዶችን የማስወጣት ርምጃ ወደፊት አይኖርም ብሎ ተስፋ እንደሚያደርግ ገለጠልኝ ። የአርባ ዓመቱ ጎልማሳ ሀሚድ በምሥራቅ አፍሪካ ትልቅ ከሚባሉት ማተሚያ ቤቶች የአንዱ ባለቤት ሲሆን ፣ በኬንያ የሚኖሩ 200,000 እስያውያን ሱኒ እስላሞች ኮሚቴ አባል ነው ። ይህ ኮሚቴ በኤኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ ተሰሚነት ያለው በጥቁር አፍሪካ ትልቁ ስብስብ ነው ።

"የልጆች ትውልድ ከእንግዲህ ራሱን ሕንድ አድርጎ ሊቆጥር አይችልም ። ቋንቋውን ለመማር እንኳ አይጨነቁም ። የተሳሰርነው ከኬንያ ጋር እንጅ ከሕንድ አይደለም ። ቤተሰቦቻችን እዚህ ከመጡ አንድ መቶ ዓመት አልፏቸዋል ። እስያውያኑ ዛሬ የአፍሪካ ጎሳ ሆነ ዋል" አለኝ ።

ሀሚድ የጀልባ አዳሽ ልጅ ሲሆን ከሞምባሳ ወደ ናይሮቢ ሲመጣ ሙልጭ ያለ ድሃ ነበር ። ድህነትን ያመለጠው ጠንክሮ በመ ሥራት ነው ። "እስያውያን ገንዘብ በመቆጠብ የሚያክላቸው የለም ። ገንዘብ የመሰብሰብ ፍቅራችን ከአይሁዶች የሚመሳሰል ነው ። አፍሪ ካውያን የሚጠሉን አንዱም ለዚህ ሳይሆን አይቀርም" አለኝ ።

በቅኝ ግዛት ዘመን እስያዊው ከነጩም ከጥቁሩም ሳይሆን መሀል ቤት የቀረ ነበር ። የነጮች መብት አልነበረውም ፣ የጥቁሮችን ያህ ልም ጫና አልነበረበትም ። የተለየ የመኖሪያ ክልል ተሰጥቷቸው እስያውያን ልጆቻቸውን ወደ አውሮፓውያን ት/ቤትም ሆነ ወደ አፍሪካውያን ት/ቤቶች መላክ አይችሉም ነበር ። በ1950ዎቹ አውሮፓ ውያን ለራሳቸው ልጆች ትምህርት በዓመት በልጅ 180 ዶላር ይመድባሉ ። ለእስያዊ ልጅ ደግሞ በዓመት 65 ዶላር ፣ ለአፍሪካዊ 5 ዶላር ብቻ ለትምህርት ይመድቡ ነበር ። በሥራ አቀጣጠር እስያዊ ተመሳሳይ ሥራ ከሚሠራ አፍሪካዊ ስድስት እጥፍ ደመወዝ ሲያገኝ ከአውሮፓዊው ደመወዝ ደግሞ በአንድ ሶስተኛ ያነሰ ያገኛል ።



ጆን ካርማሊየሚባል የናይሮቢ ሮታሪ ክለብ ሊቀመንበር የሆነእስያዊ ደግሞ የደረሰበትን ሲያጫውተኝ ፤ "ሰዎች ከሰላሣ ዓመት በፊት በዚህ ቦታ የነበረውን ይዘነጋሉ ። እኔ ከለንደን ዩኒቨርሲቲ ተመርቄ ስመለስ እንግሊዛዊት ሚስት አግብቼ በመምጣቴ በኬንያ የመጀመሪያው በጋ ብቻ የተደባለቀ ዘር ነበርሁ ። መሬት መግዛት የቻልሁት አንዳንድ ቦታ ዎች ብቻ ነው ። በናይሮቢ ከተማና በአገሪቱ ሰሜናዊ ክፍለሀገር ሆቴል ገብቼ ምግብ የሚያቀርብልኝ አልነበረም ። ከቤተሰቤ ጋር ከከ ተማ ውጭ ለሽርሽር በመኪና ስሄድ አቁሜ ሻይ መጠጣት የምችል በት ቦታ አልነበረም ። የዘር መድሎው ሥርዓት (አፓርታይድ) ልክ እንደ ደቡብ አፍሪካ ጠንካራ ነበር ።"

በ1950 ካርማሊና ባለቤቱ ጆአን በኬንያ የመጀመሪያውን የሁ ሉም ዘር ልጆች የሚማሩበት ት/ቤት አቋቋሙ ። ለነጮች ብቻ አባል ነት የሚፈቅደው የናይሮቢ ሮተሪ ክለብ ሁለት ጊዜ የካርማሊን ማመ ልከቻ ውድቅ ካደረገ በኋላ በ1958 በአባልነት ሲቀበለው የተበሳጩ ሁለት ፈረንጆች በእለቱ ከአባልነት ክለቡን ለቀው ወጡ ። በ1980 ግን የሁሉም አመለካከት ስለተለወጠ የሮተሪ ክለቡ ሊቀመንበር ሆኖ የተመረጠው በሙሉ ድምፅ ነበር ። ዛሬም ቢሆን በኬንያ የዘር መድሎ በጥቂቱ ይታያል ። ሆኖም ይህን ያህል የጠነከረ መናናቅም ሆነ ጥላቻ እንደሌለ ይናገራል ። "አሁን የሚታየው መድሎ በሶስት ምክንያቶች ነው ። አንዱ ምቀኝነት ወይም ቅናት ነው ። ምክንያቱም እስያውያን በሙሉ ሀብታሞች ናቸው ። ሁለተኛው እስያውያኑ ከሌላው ስለማይቀ ላቀሉና ከራሳቸው ዘር ጋር ብቻ ተሳስረው ስለሚኖሩ ነው ። በእኛ በኩል የሚታየው ትልቁ ስህተት ይህ ነው ። ሶስተኛው እስያውያንና አፍሪካውያን በአኗኗር ዘይቤአቸው በጣም ይለያያሉ ።

"አፍሪካውያኑ ዛሬ በላቀ ሥልጣን ላይ ስለሆኑ የድሮ ቂማቸውን ለመበቀል መሞከራቸው አልቀረም ። ይህም የሰው ልጅ ባህርይ ነው ። ቀድሞ ስለተጨቆነ ዛሬ በተራው ሌላውን መጨቆን ቢያሰኘው አል ፈርድበትም ። ያልተለመደም አይደለም ።"

ይህ የጠቀሰልኝ የዘር መድልኦ አይነት በዘዴ የሚካሄድ ነው ። ለምሳሌ በአውሮፕላን ጣቢያ የእስያውያን ሻንጣ ምንጥር ተደርጐ

ይፈተሻል ። ቦርሳቸውና ኪሳቸው ሳይቀር እንደወንጀለኛ ይበረበራል ። አፍሪካዊው የጉምሩክ ሠራተኛ እስያዊውን በማበሳጨት ይደሰታል ። እስያዊውም ቢያጉረመርም የባሰ እንደሚከርበት ስለሚያውቅ በትህትና የተጠየቀውን ሁሉ ያደርጋል ።

አፍሪካዊና እስያዊ የኬንያ ዜጐች ለአንድ የሥራ ቦታ ቢቀርቡ ወይም ዩኒቨርስቲ ለመግባት ቢጠይቁ ቅድሚያ የሚሰጠውና ተቀባይነት የሚያገኘው ጥቁሩ አፍሪካዊ ነው ። በኬንያ ጦር ሠራዊት ውስጥ ያሉት እስያውያን መኮንኖች ከሻለቃ ማዕረግ በላይ ለመሾም ያላቸው ተስፋ ኢምንት ነው ።

በ1982 በኬንያ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ በተደረገ ጊዜ እስያውያን ሱቆቻቸው በሁከቱ ውስጥ ተዘረፉ ። እስያውያንም የሚያዋጣቸውን አቅጣጫ በመከተል በዝምታ የፈረሰባቸውን መልሰው መገንባት ጀመሩ ። "እኛ እስያውያን በቅኝ ግዛት ዘመን በመነገድና ለአውሮፓውያን በማገልገል ብዙ ገንዘብ ስላተረፍን በቅኝ ገዢዎች ላይም መራር ጥላቻ የለንም" በማለት አንዲት እስያዊ ሴክሬተሪ አወጋችኝ ።

የአፍሪካ አገሮች የፖለቲካ አቅጣጫ የቅኝ ገዢዎቻቸውን አገሮች ፈለግ የተከተለ ነው ብሎ ለመደምደም ያስቸግራል ። የጦርነቶች ብዛት ፣ የመፈንቅለ መንግሥት መደጋገም ፣ ወታደራዊ አገዛዝ መመሥረቱ ሁሉ በእንግሊዝም በፈረንሣይም ቅኝ ግዛት በነበሩት አገሮች ሁሉ ተመሳሳይ ነው ። ሁለቱም ቅኝ ገዢዎች ጥሩ የፖለቲካ ሰዎችን የቀረጹትን ያህል አረመኔ እብድ መሪ የሆኑትንም የኰተኰቱ እነሱው ናቸው ። ሁለቱም በኤኮኖሚ ግንባታ የተሳካላቸው አገሮች ፈጥረዋል ፤ (ኬንያና አይቮሪ ኮስት) በኤኮኖሚ የተንኮታኰቱ አገሮችም አፍርተዋል ፤ (ታንዛንያና ጊኒ) ። በጎሳ የተከፋፈሉት አገሮችም ኡጋንዳና ቻድን የመሳሰሉት የሁለቱ ቅኝ ግዛቶች ነበሩ ። የተረጋጋ ፖለቲካ ያላቸውንም አስተዳድረው ነበር ፤ (ሴኔጋልና ማላዊ) ። በየጊዜው በሁከት የተዋጡት ጋናና ቤኒንም አንዱ የፈረንሣይ ሌላው የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ነበሩ ። ስለዚህ ያም ገዛቸው ያ ፣ ቅኝ አገዛዝ በአፍሪካ ያደረሰውጉዳት ራሳቸው አፍሪካውያን በራሳቸው ላይ ካደረሱት የበለጠ አይደለም ።



አንድ ግልፅ የሆነ ነገር ግን የፈረንሣይ የቅኝ ግዛት ውርስ ላቅ ያለና በግንኙነትም ጠንከር ብሎ የቀጠለ ነው ። በባህልና በኤኮኖሚ ጠንካራ ግንኙነት መስርታ የቀጠለች ፈረንሣይ ስትሆን ከቀድሞ ግዛቶችዋ ጋር የሞቀ ወዳጅነት አላት ። የሴኔጋል የቀድሞ ፕሬዚዳንት ሊዮፖልድ ሴዳር ሴንጎር በፈረንሣይ የተማሩና በፈረንሣይ አገር ሚኒስትር ደረጃ የነበራቸውና ቅኝ ገዢዋን አገር ከአገራቸው ያላነሰ የሚወዱ ናቸው ። የፈረንሣይ ስሪት የሆነ ነገር ሁሉ ያደንቃሉ ። የእረፍት ጊዜያቸውን ሁሉ የሚያሳልፉት ፈረንሣይ ውስጥ ነው ።

ይህ የሆነበት ምክንያት የፈረንሣይ ቅኝ አገዛዝ ዘዴ ወይም ፖሊሲ ከራስ ማመሳሰል ወይም አንዳንዶቹ እንደሚሉት የባህል ኢምፔሪያሊዝም ነበር ። ከማዕከል ቀጥታ አመራር በመስጠትና በመጫን ለጎሳ መሪዎች የተወሰነ ሥልጣን ብቻ ይተውላቸው ነበር ። እንግሊዞች የመጡት ለመሥፈር ሲሆን ፈረንሣዮች ግን ለማስተዳደር ነው ። የእንግሊዝ መጤዎች ስዋሂሊ ቋንቋ ሲለምዱ ፈረንሣይ ግን በራሷ ቋንቋ በመግዛት ተገዢዎቹም ፈረንሣይኛ እንዲማሩ አስገደደች ። እንግሊዝ ከጎሳ መሪዎች ጋር ውል በመፈራረም ስትሠራ ፈረንሣይ ግን ወጣቶችን ፓሪስ በማስተማርና የፈረንሣይን ባህል ተላብሰው እንዲያድጉ በማድረግና አንድ ፈረንሣዊ ሊኖረው የሚችለውን መብት ሁሉ (ዜግነትን ጨምሮ) በመስጠት የምሁራን መደብ ፈጠረች ።

ፈረንሣይ በቅኝ ግዛቶችዋ ላይ የነበራት ትኩረት ባህላዊ ሲሆን ፣ የእንግሊዝ ግን ኤኮኖሚያዊ ነበር ። ይህን ጥቅም ለማራመድ እንግሊዝ መሠረተ ልማቶችን ዘርግታ በኋላም ትታላቸው ሄደች ። ያም ቢሆን አላስወደዳትም ። እንግሊዛዊ ምሁራንን ለማሰብ የተተከሉትን ሐውልቶች ሕዝቡ አፈራረሳቸው ። በኬንያና በዛየር የሆነው ይኸው ነው ። ነገር ግን የፈረንሣይ ቅኝ ግዛት በነበሩ የምዕራብ አፍሪካ አገሮች የፈረንሣይ ታላላቅ ሰዎችን ለማክበር የቆሙ ሐውልቶች እንዳሉ ሲሆኑ ፣ ድልድዮች ፣ መንገዶች ፣ አደባባዮች ሁሉ በፈረንሣይ ዕውቅ ሰዎች ስም እየተጠሩ ቀጥለዋል ። ለምሳሌ ጆን ቤዴል ቦካሳ በማዕከላዊ አፍሪካ ሥልጣን ሲይዙ ያሰሙት መፈክር "ቪቭ ላ ፍራንስ"

(ፈረንሣይ ለዘለዓለም ትኑር) የሚል ነው ። በቻርልስ ዶጎል የቀብር ሥነሥርዓት ላይም ተንሰቅስቀው "አባባ! አባባ!" እያሉ ሲያለቅሱ ሕሊናቸውን ስተው በሽክም ነበር ከመቃብሩ ቦታ የተወሰዱት ።

ፈረንሣይ በተለያዩ አጋጣሚዎች በቀድሞ ቅኝ ግዛቶችዋ ውስጥ መሪዎቹን ለመገልበጥም ሆነ በሥልጣን ለማቆየት ወታደራዊ ኃይሏን ስትጠቀም ቆይታለች ። ሌሎች የአውሮፓ ኃያላን ከዚህ ዓይነት ተግባር የታቀቡ ናቸው ። ከዚህም ሌላ ፈረንሣይ በእነዚህ አገሮች አንዳንድ የቅንጦት ሽቀጦችን በማቅረብ ጣዕም ያለው ሕይወት አስለምዳቸዋለች ። ይህ በዋነኛነት የሚጠቅመው በዚያ የሚገኙ ፈረንሣዮችን ቢሆንም ለገዢው መደብ ጥሞታል ። በማሊ ዋና ከተማ በባማኮ ለምሳሌ በሳምንት ሁለት ጊዜ በአውሮፕላን ከፓሪስ የሚመጣ የፈረንሣይ ምግብ መግዛት ይቻላል ። ይህም አይስ ክሬምን ይጨምራል ። ዋጋውም አንድ ጋሎን 24 ዶላር ነው ። 50,000 ፋረንሣውያን በሚሠሩበት በአይቮሪኮስት በመንገድ ዳር ባሉ ቡና ቤቶች የፈረንሣይ ምግብ ማዘዝና የዕለቱን የፈረንሣይ ጋዜጣ "ለሞንድ" ገዝቶ ማንበብ ይቻላል ። እነዚህ ምንም የሌላቸው ድሀ አገሮች ከፈረንሣይ የበለጠ ፈረንሣይ ለመሆን እየቃጣቸው ነው ። በቡርኪና ፋሶ ዋና ከተማ ያለ አንድ ሱቅ ለምሳሌ ከፈረንሣይ መስኮች ተቀጥፈው የመጡ አበባዎችን በመሸጥ ያገለግላል ። ለማዕከዕዊ አፍሪካ ሪፑብሊክ ፈረንሣይ ከአገሪቱ አመታዊ የሰባ ሚሊዮን በጀት ግማሹን ትደጉማታለች ። ለስልክ አገልግሎት ትከፍልላታለች ። የመንግሥት ሠራተኞችን ደመወዝ ሃያ በመቶ ትሸፍንላታለች ። በጋቦን ደግሞ የመንግሥት ሥራዎችም ሆኑ የንግድ እንቅስቃሴዎች የሚካሄዱት እዚያ በሚኖሩ 30,000 ፈረንሣዮች ነው ። ከናይጀር ወደ ሌላ አፍሪካ አገር ከሚደረግ የአውሮፕላን ምልልስ ይልቅ ወደ ፓሪስ የሚደረገው በረራ ቁጥር ይበልጣል ። ከኮንጎ ወደ ሌላ የአፍሪካ አገር ስልክ ለመደወል ብትፈልግ የምትገናኘው በፓሪስ በኩል ነው ። በብዙዎቹ የፈረንሣይ ቅኝ ግዛት በነበሩ የአፍሪካ አገሮች የተለመደው መገበያያ ገንዘብ በፈረንሣይ የሚጠፈጠፈው የአፍሪካ ፍራንክ ነው ።

በ1958 የአፍሪካ የነፃነት ብሔራዊ ንቅናቄዎች እየጎለበቱ ሲሄዱ



ቻርልስ ዲጎል ለቅኝ ግዛቶች ምርጫ ሰጡ ። ነፃነት የመረጡ ነፃ ወጡ ፣ ሌሎች መቆየትን መረጡ ። ነፃ ለወጡት ፈረንሣይ ድጎማ መስጠት አቋረጠች ። በዚህ ወቅት ጊኒ ነፃነቷን በመጠየቅ በኋላ ፕሬዚዳንት የሆኑት ሴኩቱሬ "ጊኒ በባርነት ሀብታም ከመሆን ይልቅ በነፃነት ድህነትን ትመርጣለች" ሲሉ ተናገሩ ።

የአፍሪካ ሕዝቦች ዛሬ በነጮች ላይ ጥላቻ የላቸውም ። ፈረንጆችም በየትኛውም የአፍሪካ አገር በከተማም ሆነ በገጠር ለመዘዋወር የሚያሰጋ ነገር የለባቸውም ። ስለዚህም ከነፃነት በኋላም በዚያው የቆዩና ወደዚያ በመሄድ እየሰሩ መኖር የጀመሩ ብዙ ናቸው ። ለምሳሌ በአይቮሪ ኮስት ከነፃነት በኋላ በዚያ የሚኖሩት ነጮች ቁጥር ከበፊቱ ፀአምስት እጅ በለጠ ። በኬንያ የቀድሞ ባለእርሻዎች የነበሩ 5,000 እንግሊዛውያን የኬንያ ዜግነት ተቀበሉ ። በሞዛምቢክና በአንጎላ የሚገኙ ፈረንጆች ዜግነታቸውን ለውጠው ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን ቦታዎችን እንደያዙ ናቸው ። አፍሪካውያን በቅኝ ገዢዎች የተፈጸመባቸውን በደል ባይረሱትም ይቅር ብለዋል ። ለነፃነቱ የተዋጋውና የተደራደረው ዋናው የአድሎን ሥርዓት ለማስወገድ ነው ። ድል ከተጐናጸፈ በኋላ ከቅኝ ገዢዎች የተሻለ ሆደ ሰፊ ፣ ትዕግሥተኛና ሁሉን የሚያቻችል ሆነ ።

ለዚህ የነጮችና የጥቁሮች ግንኙነት መለወጥ ዓይነተኛዋ መስተዋት ኬንያ ናት ። አፍሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ የነፃነት ጦርነት የከፈተችው በኬንያ ከ1953—1956 የማኦ ማኦ ንቅናቄ በተነሳሳ ጊዜ ነበር ። ጆሞ ኬንያታ ከነጮች እሥር ቤት ተፈትተው የዘር መድሎ መወገድንና በእኩልነት ተቻችሎ "ከልባቸው" አፍሪካዊ ከሚሆኑ ነጮች ጋር መኖርን ሰበኩ ። በዚሁ በኬንያ ጦርነት በተካሄደበት ስሜናዊ ክፍል ዛሬ ነጮችና ጥቁሮች ገበሬዎች ጎን ለጎን በጉርብትናና በአዋሳኝነት እያረሱ ይኖራሉ ። ያለፈውን ቂም ረስተው በፍቅርም ባይሆን ያለጥላቻ አብረው ይሠራሉ ። የዚህም አስተሳሰብ መሠረቱ ጊዜው ተለውጧል የሚለው ግንዛቤ ነው ። ነገር ግን ነጮች በኬንያ የፈለገውን ያህል ሥር ቢሰዱም ከእንግድነት ውጭ በሌላ መልክ ሊታዩ አይችሉም ።

ከማኦ ማኦ ንቅናቄ መሪዎች አንዱ ,የነበረው ሰው ፍሬድሪክ

ዲራንጐ ለአራት ዓመት በአበርዳሬ ጫካ ከተከታዮቹ ጋር ሸፍቶ ሌሊት ሌሊት የነጮችንና ድጋፍ የከለከሉት ጥቁሮች ቤት በማጋየት ፥ ቀን ከእንግሊዝ ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች ተደብቆ ይውል ነበር ። ዲራንጎ—ዛሬ ፀጉሩ ሽበት የወረረው ሆኖ በአንድ የአበርዳሬ ክበብ ውስጥ ይሰራል ። ያን ጊዜ የመራው ጦርነት ተገቢና ውጤት ያስገኘ እንደነበረ ይናገራል ። ምክንያቱም ይላል “ዛሬ መሬት ማግኘት የቻልሁት በዚያ ትግል ውጤት ነው ።” ሁለቱ ልጆቹ ኤሌክትሪሽያን ሆነው በናይሮቢ ይሠራሉ ፤ ሌሎች ሰባት ልጆቹ ደግሞ በትምህርት ላይ ናቸው ። ያን ጊዜ በየጫካው የተሰደደው ታጋይ ዛሬ ባለድል ነው ።

“ከማኦ ማኦ ንቅናቄ በፊት ጥሩ አውሮፓዊ አልነበረም ። ይሰድቡን ነበር ፤ እንዳንማርም ከልክለው ቆዩ ። ዛሬ ሁኔታዎች ተለውጠዋል ። አሁን ይህ አገር የእነሱ ሳይሆን የእኛ ነው ። ግንኙነታችንም ጥሩ ነው ። የበፊቱን አስታውሰዋለሁ ፤ ግን ቂም አልይዝም ።.. በኩኩዩ ጎሳ ባህል አንድ አባባል አለ ። ከተጣላችሁ ፥ ካልተፋለማችሁ ጓደኛ አትሆኑም ። አንድ ጊዜ ታግላችሁ ከተዋጣላችሁ በኋላ ግን ጥላቻው ሁሉ ያበቃል”

የእንግሊዝ ሻምበል የነበረ ሳም ዌለር የተሰኘ ሰው ደግሞ ሲያጫውተኝ ፥ “ይህ ሰው ያን ጊዜ ወጣት ነበር ። ታዲያ ሁለት ጊዜ ያህል ከሩቁ አይቼው ልገድለው ስገሰግስ ግን ሾልኮ የገባበት ይጠፋብኛል ። ታዲያ ዛሬ የማኦ ማኦ ንቅናቄ በዚህ አካባቢ ተረስቷል ። የተረሳበት ምክንያት በከፊል ይመስለኛል አፍሪካውያን እንደ አውሮፓውያን ቂም አይዙም ። አፍሪካውያን ሴቶቻቸውንም አጥብቀው አይወዱም ፤ ጠላቶቻቸውንም አጥብቀው አይጠሉም ። የነጭ ጥላቻ ግን ለትውልዶች ይተላለፋል ። አፍሪካውያን እንደዚያ አይጠሉም” አለኝ ።

ከጦርነቱ በኋላ ዌለርም አራሽ ሆነ ። ከዚያም አዳኝና የቱሪስቶች አስጐብኝ ሆነ ። በመጨረሻም በእሱ ትውልድ የነበሩ አውሮፓውያን በአፍሪካ ለመቀጠል እድሉ እንዳላቸው ሲያምንበት የኬንያ ዜጋ በመሆን ኑሮውን በዚያው አደረገ ። ዛሬ ከከለቡ ፈቀቅ ብሎ በሚገኘው ተራራ አጠገብ ባለች ጎጆው ብቻውን ይኖራል ። ብራንዲ አቀረ



በልኝና ሬዲዮ ከፈተ ። በቢ.ቢ.ሲ. ዜና “የእንግሊዝ ገዢ ከለንደን ወደ ሮዴሽያ ሄዱ” የሚለውን ሲሰማ በመገረም ቅንድቡን ሰቀል አደረገ ። ሌላዋ የነጮች ቅኝ (ዚምባብዌ) መሄድዋ ነው ። መደርደሪያው ስለአፍሪካ በተፃፉ መፃሕፍት ተሞልቷል ።

በአፍሪካ የመጀመሪያዎቹ ነጭ ሰፋሪዎች በእንግሊዝ አገር ማስታወቂያ እያወጡ “አፍሪካ ለም ናት ፥ አየሩ ጤናማ ነው ፥ ርካሽ ጉልበት ሞልቷል ፥ ሥጋ እንደልብ ነው ፥ አትጠራጠሩ “. . . እያሉ ሠፋሪዎችን ለመሳብ ያስተዋውቁ ነበር ።

ይሁን እንጂ የኩኩዮዎቹ ትግል እየጠነከረ ሲሄድ ነጮች ተረበሹ ፥ በኃይል ርምጃ ሊያቆሙት እንደማይችሉ ተገነዘቡ ። በታህሣሥ 1963 ለኬንያ ነፃነት ለመስጠት የእንግሊዝ መንግስት በስብሰባ ተስማማ ። ከዚሁ ጋር በደጋው የኬንያ ክፍል ሶስት ሚሊዮን ጋሻ መሬት ለተተወላቸው ነጮች የሚሆን 100,000,000 ዶላር በብድር እና በስጦታ መልክ ለመመደብ ወሰነች ። እንግሊዞቹ በዚያው እንዲቆዩ ለማበረታታትም በምሥጢር ለእነዚህ ሰዎች ካስፈለገ ወደፊት የእንግሊዝ ዜግነት እንደምትፈቅድላቸው በመግለጥ ለአሁኑ ግን ኬንያዊ ዜግነት እንዲወስዱ አሳሰበች ።

በነሐሴ ወር 1963 ከነፃነት በፊት በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ፈረንጆች ከነሚስቶቻቸው በአበርዳሬ አውራጃ በሚገኝ ናኩሩ አዳራሽ ተሰበሰቡ ። ፀጥታ ነገሠ ፤ በአስቸኳይ ለቃችሁ ውጡ የሚባሉም መስኋቸው ነበር ። ወዲያው ከእንግሊዞች እሥር ቤት የተፈቱት ጆሞ ኬንያታ (ያን ጊዜ የሰባ ዓመት አዛውንት) ወደ መድረኩ ወጡና ከዘራቸው ላይ ደገፍ ብለው ቆመው እንዲህ አሉ ። “እኛ እንድትቆዩና በዚች ሀገር በደንብ እንድታርሱ እንፈልጋለን ። የዚህ መንግሥት ፖሊሲ ይህ ነው ።. . .መንግሥት የሚሻው ልምድ ስለሆነ ከየትም ይምጣ ከየት በሁለት እጃችን እንቀበለዋለን ። መሬታችሁን ማረስ ቀጥሉ ፤ ማበረታቻና የመንግሥት ጥበቃ ይደረግላችኋል ። የማንቀበለው ነገር ጦም ያደረ መሬት ብቻ ነው ።”

“ኬንያ ሰፊና ትልቅ ቅምጥ ሀብት ያላት ናት ። ሁላችንም በአንድነት በመተባበር መሥራትና ይህችን አገር ትልቅ በማድረግ ለሌ

ሎች የዓለም አገሮች የተለያዩ ዘሮች በአንድነት መሥራትና መኖር እንደሚችሉ እናሳያቸዋለን” አሉ ። ነጮች ባለማመን ተያዩና ተነስ ተው በጭብጨባ ደስታቸውን ገለጡ ።

ነጮቹ እንዲቆዩ ቢባልም ዞሮ ዞሮ ጥቁሮች የተዋጉት ለመሬት ስለሆነ መሬት ማግኘት አለባቸው ። አዲሱ መንግሥትም የሕዝቡን ድጋፍ ለማግኘት የግድ ይህን ማድረግ አለበት ። በኬንያ ያሉት የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ ሰፋፊ የከብት ማርቢያ ጣቢያዎች ከነ ጮች ተወስደው ለጥቁሮች ተቆራርሰው ቢሰጡ ምርታቸው ከእጅ ወደ አፍ ለሆነ ኑሮ ይሆናል ። ይህ ደግሞ ምንም የማዕድን ሀብት ለሌ ላት አገርና በሕዝብ ብዛት እየተጥለቀለቀች ለምትሄድ ሀገር ጠቀሜታ የለውም ። መሬት ተከፋፍሎና ተሸንሽና በትንሽ በትንሽ ሲሰጥ ምር ትም ይቀንሳል ፣ ታክሱም እንዲሁ ነው ። በ1975 ኬንያ ለራስዋ የሚበቃት ስንዴ ታመርት ነበር ። በ1980 ለሕዝቧ ቀለብ ከሚያስፈ ልገው 2,800,000 ኩንታል ስንዴ ግማሹን ከውጭ መግዛት ነበረ ባት ። ይህን በማጤን የናይሮቢ መንግሥት ኬንያ እንድታድግ ከተፈ ለገ መሬት ማከፋፈሉ ቀርቶ ነጮች እንደበፊቱ በስፋት እንዲያርሱ መደረግ አለበት ይላል ።

ነገር ግን የመሬት መጣበብ ትልልቅ እርሻዎች እንዲሸራረፉ ማድረጉ የማይቀር ነው ። በዚሁ ዓይነት የመኖርያ ቤት ችግር በከ ተማ ያለውን የነጮች ሰፈ ይዞታ ማስለቀቅ ያስገድዳል ። የሥራ እድል መጣበብም ነጮች የያዙትን የሥልጣን ቦታ እንዲለቁ መግ ፋቱ አይቀርም ። ዛሬ አብዛኞዎቹ አውሮፓውያን ልጆቻቸውን አውሮፓ በማስተማር ከአደጉበት አካባቢ ለተለየ ሕይወት እያዘጋጁዋቸው ነው።

አንድ ሰፋሪ ነጭ እንደነገረኝ ፤ “ልጆቼ አፍሪካን ከሚገባው በላይ እንዲወዱ ለማስተማር አልፈልግም” አለኝ ።



ምዕራፍ ስምንት

# ከሊዝበን በፍቅር

“በአንጎላ በቀን 600 ጎማዎች እያመረትን ነው ፤ እንዴት እን ዲያ መሥራት እንደቻልን ግን የሚያውቀው እግዚአብሔር ነው ። ሠራተኞች ጥዋት መጥተው አንዲት ነገር ይሞናሉ ፤ ከሠራ መልካም ። አልሠራ ካለ ግን ወደቤት መሄድ ብቻ ነው ።”

—የአጠቃላይ ጎማና ላስቲክ ፋብሪካ ሥራ አስኪያጅ

የዛሬውን እያድርገውና ከጥቂት ዓመታት በፊት የአንጎላ ዋና ከተማ ሉዋንዳ የአፍሪካ ሪዮዲጄኔሮ ትባል ነበር ። አንጎላም የብል ጽግናና የተትረፈረፈ ሀብት አገር ነበረች ። በዚህች የደቡባዊ ምዕ ራብ አትላንቲክ ውቅያኖስ ጠረፍ በምትገኝ ቅኝ ሀገር ሕይወት ምን ይመስል እንደነበር አንድን ፖርቱጋላዊ ብትጠይቀው ፈገግ ይልና ዓይኑን በመከደን ከንፈሩን በመሳም “እምፑዋ!” ይልሃል ።

አንጎላ ከሊዝቦን የተሻለች ለመኖር ምቹ የሆነች አገር እንደ ሆነች ይነግርሃል ። ወደሀገርህ ለመመለስ የምታስመኝ ሀገር አልነበ ረችም ። አገሬ መሄድ አልፈልግም የምታሰኝ ነበረች ። በሳምንቱ መጨረሻ የዕረፍት ቀናት በባህሩ ዳርቻ ወዲያው ከባህር የወጣ ሎብ ስተር የተበኘ ዓሣ እየተመገቡ መዝናናት የተለመደ ነበር ። የሚያማ ምሩ ሱቆች ዘመናዊ በሆኑ ልብሶችና ምግቦች ተሞልተው ማየት ዓይን የሚያጠግብ ነበር ። በባህሩ ወሽመጥ የተገነቡት ረጃጅም ፎቅ

ቤቶችና ለዕረፍት ቀን ማሳለፊላ በሉቢቶ የተሰሩት መዝናኛ ሰቀላዎች የፍሎሪዳን በዘምባባ የተሞላ ምዕራባዊ የባህር ዳርቻ የሚመሳሰል ነው ። ከአፍሪካውያኑ ጋርም እስከመጨረሻው አካባቢ ቁርቋሶ አልነበረም ።

ዋና ከተማው ሉዋንዳ የተቆረቆረው ከባህር ወሽመጡ ገባ ብሎ ባለው ጉብታማ መሬት ላይ ነው ። አውራ መንገዶቹ ሰፋፊና ግራና ቀኝ ዛፎች የተተከሉባቸው ናቸው ። የእግር መንገዶቹ በሞዛይክ ንጣፍ አምረው የተሰሩ ናቸው ። በየቦታው መናፈሻዎች ተከልለው በአበቦችና በተከረከሙ ተክሎች ተውበዋል ። በከተማዋ ውስጥ አንድ መቶ ሰባ ሆቴሎችና የዳንስ ክለቦች ከምሽቱ እስከ ንጋቱ ክፍት ሆነው አገልግሎት ይሰጣሉ ። ከተማውን ከሩቅ ሲመለከቱት ሃያ ሰባት ፎቅ ካለው ረጅሙ ፕሬዚዳንት ሆቴል አንስቶ በአስራ ሰባተኛው ምዕት ዓመት እስከተገነባ የፖርቱጋሎች የምሽግ ግንብ ድረስ መደዳውን ያለው ዓይን የሚስብ እይታ በአፍሪካ የትም የሚገኝም አይመስልም ። በተጨባጭ በአህጉሪቱ ውስጥ ከዚህ የሚያምር የከተማ ገጽታና የሚያስደስት የአኗኗር ዘይቤ የትም የለም ።

ለፖርቱጊዞች የሚያስደስታቸው ነገር በአንጎላ ተደስተው ለመኖር የተማሩ መሆን ወይም ሀብት ማፍራት የማያስፈልጋቸው መሆኑ ነው ። ነጭ መሆናቸው ብቻ ይበቃል ። 500,000 ፖርቱጊዞች የነበሩባት አንጎላ ከአፍሪካ ቅኝ ግዛቶች ሁሉ ነጮች የሚበዙባት አገር ናት። እንደሌሎቹ የፖርቱጋል ቅኝ ግዛቶች ሞዛምቢክ ፣ ጊኒቢሳው ፣ ኬፕ ቬርዴ ፣ ሳኦቶሜና ፕሪንቺፔ ፣ ለዘለዓለም ለመኖር አስበው የመጡ ነጮች አገር ናት ። ተራ ሥራዎች ሳይቀር ሾፌርነትም ፣ ፀጉር አስተካካይነትም ፣ ሆቴል አሳላፊነትም ፣ በፖርቱጊዞች የተያዙ ነበሩ ። ለሰባት ሚሊዮን አንጎላውያን የተተወላቸው ሥራ አሽከርነት ፣ ግርድና ፣ ተሸካሚነት ፣ የተክል ልማት ሠራተኛነት ብቻ ነበረ ። ከአምስት ምዕት ዓመት የፖርቱጋል ቅኝ ገዢነት በኋላ በ1975 አንጎላ ነፃ ስትወጣ ከሕዝቧ ዘጠና ስምንት በመቶ ማይም ነበረ ። የቴክኒክ ሙያ የነበራቸው በጣት የሚቆጠሩ ሲሆኑ ፣ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ያላቸው ኢምንት ነበሩ ።



የፖርቱጋል ቅኝ ግዛቶች ነፃ ሲወጡ ማርክሲዝምን በመከተላቸው በአፍሪካ ተራማጅ የሚባሉ አገሮች በረከቱ ። ነጮችም የአፍሪካውያኑን የበቀል ርምጃ በመፍራት ለቀው መውጣት ጀመሩ ። በአፍሪካ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ነጮች ወደ አውሮፓና ደቡብ አፍሪካ በብዛት ተሰደዱ ። ሊያጉዋጉዙ የቻሉትን ንብረትና ዕቃ ቁራንቁዋ ሁሉ በመርከብ ጫኑ ። ከሃያ ሺህ በላይ መኪናዎች በመርከቦች ተጫኑ ። የቀሩትን መኪናዎችም በመሰባበር ለአንጎላ አንድም እንዳይቀርላት አድርገው ወጡ ። የአሣ ማጥመጃ መርከቦችም ወደ ሊዝቦንና በስተደቡብ ወደአለው የናሚቢያ ዋልቪስ ቤይ የባህር ወሽመጥ ተወሰዱ ። የስልክ መነጋገሪያዎች ተቆርጠው ተጋዙ ። ታይፕ መፃፊያዎችም ተጫኑ ፤ የተክል ልማቶች ባዶ ቀሩ ፣ ቤቶች ተሰባበሩ ፣ ዶክተሮች ከሆስፒታል ኮበለሉ ። ፕሮፌሰሮች ከዩኒቨርሲቲዎች ለቀው ሄዱ ። በአንድ ሳምንት ውስጥ ከአንጎላ የባንክ ሠራተኞች ዘጠና አምስት በመቶው ለቀቁ ። የቀሩት ጥቂት የቢሮ ፀሐፊዎችና ተሸካሚዎች ብቻ ነበሩ ። ሁሉም ጥሎ ሲሄድ አንጎላ ራቁትዋን ቀረች ። የቀሩት 25000 ነጮችና የተንከራከሰች አገር ናት ። "የሠራነው ሁሉ የሚያኮራ አይደለም ፣ ግን ወደን እንዳልወጣን ታውቃለህ" አለኝ አንድ ፖርቹጋላዊ አስመጭና-ላኪ ።

ስለ ፖርቱጋል ቅኝ አገዛዝ ታሪክ አስከፊነት ማውሳት ተገቢ ነው ። ፖርቱጋል የቅኝ አገዛዝ አስከፊ ገጽታዎች ሁሉ ተምሳሌት ናት ። መዘበረች እንጂ ቤሳ ቤስቲን አልሰጠችም ። ሁለቱን የአፍሪካ ቅኝ ግዛቶቿን አሟጣ አልባ እንደሞተች ላም በመጣል ያላንዳች ትርፍራፊ ለኤኮኖሚ ውድቀት ዳረገቻቸው ።

ዛሬ የሉዋንዳን ከተማ ከሩቅ ስትመለከት የሕንፃዎች አደራደር እንደቀድሞው ዓይን ይማርካል ። ውስጡ ስትገባ ግን ባዶ ነው ። በየሆቴሉ ደጃፍ የምታገኘው ክላሽ ያነገቡ ወታደሮችን ነው ። በወደቡ የሶቪዬት መርከቦች ተኮልኩለዋል ፣ ጫኚ ሠራተኞች በስንፍና በየጥላው ሥር ሲያላግጡ ስለሚውሉ ዕቃዎቹ እየዛጉ ነው ።

የሉዋንዳ ከተማ የእግር መንገዶች ፈራርሰውና ንጣፋቸው ወላልቆ ድንጋዩ ገጧል ፣ መንገዶቹም የቆሻሻ መጣያ ሆነዋል ። ሰማይ ጠቀስ

ፎቶች በባላገሮች ተሞልተው በመተላለፊያ ኮሪደሮች የሽንት ሽታ
ይሰነፍጣል ። በሰገነቶች ድጋፍ ላይ መናኛ ልብሶች ተሰጥተዋል ።
ምግብ ቤቶች ወና ቀርተው የአይጥ መራቢያ ሆነዋል ። መናፈሻዎቹ
ዳዋ ለብሰዋል ። የተሰባበሩ መኪናዎች በየመንገዱ ቆመዋል ። ንጋት
ላይ ሰዐት አላፊ ሲነሳ ሴቶች ለዳቦ ሰልፍ ይኮለኮላሉ ። ተሰልፈው
የሚገዙት የዱቄት ወተት ከብራዚል የተገዛ ነው ። እስከ እኩለቀን
ሰልፉ ያለቅጥ ይረዝማል ።

ሉዋንዳ የተወረረ ከተማ ይመስላል ፤ ሕይወት አይታይበትም ።
ሱቆችና የምግብ ሸቀጥ መደብሮች መደዳውን ተዘግተዋል ፤ መስኮ
ቶቻቸው ተሰባብረዋል ። እስካሁን ያልተበላሹት የማስታወቂያ መብራ
ቶች ያለማቋረጥ ብልጭ እልም ይላሉ ፣ የሚያስተዋውቋቸው ምርቶች
ግን ከከተማው ከጠፉ ዓመታት ተቆጥረዋል ። የሕንፃዎች አሳንሰሮች
(ሊፍቶች) አይሰሩም ። የመንግሥት ሠራተኞች ያለሥራ ተጎልተው
ስልክም ሆነ ወረቀትና እርሳስ በሌለው ቢሮ ሲያዛጉ ይውላሉ ። ትል
ልቅ ሆቴሎች ውሃም ሆነ ፎጣ የላቸውም ። በምግብ ክፍላቸውም ከሾ
ርባና ዳቦ ሌላ አይገኝም ። ሕዝቡም ቅኝ ገዢዎችን የሚጠላውን ያህል
የዛሬውን ሕይወቱንም ጠልቷል ። በአንዳንድ መልኩ ያለፈው እንደ
ሚሻልም የሚናገሩ አሉ ።

አንጎላ ዛሬ እንዳልሆነ ሆና ትታይ እንጅ የተፈጥሮ ሀብታቸው
ከፍተኛ ከሚባሉ ብዙ የአፍሪካ አገሮች አንዱዋ ናት ። አንጎላ የሚ
ለው ስም ከጥንታዊ ንጉስዋ ስም ንጎላ የመጣ ሲሆን ፣ ስፋትዋ እስ
ፓኝ ፈረንሣይና ጣሊያን በአንድነት ካላቸው ስፋት ይስተካከላል ።
ከፖርቱጋል አሥራ አራት እጅ ትበልጣለች ። ከጠረፉ ወደ መሀል
ስትገባ የመሬቱ ከባህር ወለል ከፍታው እየጨመረ ወይና ደጋማ አየር
ጠባይ ያለው ይሆናል ። ብዙ የውሃ ተፋሰሶች አሉት ። አብዛኛው የአገ
ሪቱ ክፍል ዝናብ እንደልብ ያገኛል ። የአየሩ ሙቀት መካከለኛ ነው ።
በሚሊዮን ጋሻ የሚገመት ያልታረሰ ድንግል ለም መሬት ቢኖርም ፄፄ
የተባለ ነዳፊ ዝንብ ስላለና ከብቶች ስለሚገድል የእርሻ ልማት ተዳ
ክሟል ። በዚህም የተነሳ በደቡብ የአንጎላ ክፍል የጭነት እንስሳት
የሉም ።



በተፈጥሮ ሀብት ረገድ አንጎላ በጥቁር አፍሪካ አሉ ከሚባሉ
ሁለትና ሶስት ሀብታምና የታደሉ አገሮች አንድዋ ናት ። በባህሩ
ዳርቻ ያላት በባህረሰላጤው ኩባንያዎች የሚካሄድ የነዳጅ ክምችት
በቀን 5,000,000 ዶላር ያስገኝላታል ። (ከዚህ ነዳጅ ዘይት ስድሳ
በመቶ የሚሸጠው ለአሜሪካ ቢሆንም ለማርክሳዊው መንግሥት
ዕውቅና አልሰጠችም) ። በደቡብ አፍሪካ ሽፋን የሚካሄዱ የቡናና
የአልማዝ ምርትዋ እስከ ነፃነት ድረስ ከዓለም ከፍተኛ ከሚባሉት
የሚዳመር ነበር ። የብረት ማዕድን ምርቷ በዓመት 75,000,000 ዶላር
ያስገኝላት ነበር ። ከቃጫና ከጥጥ ምርትም 51,000,000 ዶላር ታገኝ
ነበር ። በተጨማሪም ለቤንጉዌላ ባቡር ሐዲድ መስመር አገልግሎትም
ከዛየርና ከዛምቢያ በዓመት 100,000,000 ዶላር ታገኝ ነበር ። በ1980
ግን አንጎላ ከነዳጅ ዘይት ገቢ ሌላ ምርቷ እጅግ ተመናምኖ ነበር ።
ከዚህ ገቢዋም አብዛኛው መንግሥትን ከሚቃወሙ ኃይሎች ጋር
ላለባት ጦርነት የሚውል ነበር ፡ ሁሉም በጦርነቱ ምክንያትና በእው
ቀትና በአመራር ጉድለት ወድሞ የዓመት በጀት መወሰን የማይቻል
በት ደረጃ ላይ ተደርሶ ነበር ።

አንጎላ እንዲያ የተንኮታኮተችው በድንገት ያለዝግጅት ነፃ
ስትወጣ ፖርቱጋሎች ለቀው በመጉረፋቸው ፣ የእርስ በርስ ጦርነቱ
በእርቅ ሊፈታ ስላልቻለ ፣ ማርክሲስቱ መንግሥት ችግሮች ሁሉ
በመፈክር የሚፈቱ ስለመሰለውና አዲሷ አገር የምትሻውን የሰለጠነ
የሰው ኃይል ለማፍራት ከመጣር ይልቅ አሜን ብሎ የሚገዛ ታዛዥ
ሕዝብ ለመፍጠር አምባገነንነቱን በማጠናከሩ ነው ። አንጎላ በቀድ
ሞውም በአሁኑም ተጠቂ ሆናለች ። በቅኝ ገዢዎች ያለርኅራኄ ተመዘ
በረች ፣ በብሔራዊ መሪዎችዋ ደግሞ በተሳሳተ አቅጣጫ ነጎደች ።
አፍሪካ የደረሰችበት ውድቀት ተምሳሌት ሆና እድልና እቅድ ቢቀና
ጁበት ኖሮ ምን ሊሆን ይችል እንደነበር ሊጠና የሚገባው ክስተት
ነው ። ምናልባትም አንድ ቀን የሁለቱ ተቃራኒ አቅጣጫዎች መቀራ
ረብ ይፈጠር ይሆናል ።

አንጎላ ለመድረስ የመጀመሪያው አውሮፓዊ የፖርቱጋል አገር
አሳሽ ዲኦጎ ካኦ ነበር ። በ1483 የኮንጎ ወንዝ ወደ አትላንቲክ ውቅ

ያናስ ከሚቀላቀልበት ሥፍራ ደረሰ ። ከሰባት ዓመታት በኋላ ፖርቱጋሎች ወደ ኮንጎ መርከቦች በመላክ ከክልሉ መሪ ንጉሥ ጋር ግንኙነት ፈጠሩ ። በመርከቦቹ ከሄዱት ሰዎች መካከል ቀሳውስት ፣ የእጅ ሙያተኞችና የምርት መሣሪያዎች ጭምር ለንጉሡ ስለተላኩ የሞቀ አቀባበል ተደርጎላቸዋል ። በዚህም በመደሰት ንጉሡ የክርስትናን ሃይማኖት ከመቀበሉም ሌላ ልጁን (አልጋ ወራሹን) ለትምህርት ወደ ፖርቱጋል ለመላክ ተስማማ ። በዚህ መልኩ በመከባበር የፖርቱጋልና የአፍሪካ ግንኙነት ተጀመረ ። ይህ ግንኙነት መልኩን እየለወጠ ሄዶ ከአምስት መቶ ዓመታት በኋላ ወራሪዎች በአንጎላ ፣ በሞዛምቢክና በጊኒ ቢሳው የነፃነት ተዋጊዎች ድል ተመትተው ለሁሉም አከተመ ።

ፖርቱጊዞች በ1575 የባህሩን ጠረፍ ተከትለው ወደ ደቡብ በመውረድ ሉዋንዳን መሠረቱ ። በ1641 ደቾች ሉዋንዳን ከፖርቱጊዞች አስለቅቀው ያዙ ። ከዚሁ ጋር ባርያ መሸጫ የነበረችውን የወደብ ከተማ ቤንጉዌላንም ተቆጣጠሩ ። በዚህ ጊዜ ፖርቱጊዞች ወደ መሀል አንጎላ ሸሹ ። ከሰባት ዓመት በኋላ ከብራዚል የመጣ የጦር ልኩዐ ደቾችን አሸንፎ ጠረፉን ለፖርቱጊዞች መለሰ ።

ሊዝቦን ይህን የባህር ዳርቻ ለመቆጣጠር በቆራጥነት የተዋጋችበት ምክንያት ለኤኮኖሚ ጥቅም ማለትም ለባርያ ንግድ ስትል ነው ። ለዚህም በተከታዮቹ ሶስት መቶ ዓመታት ሶስት ሚሊዮን አንጎላውያንን በመሸጥ ወደ ብራዚል የተከል ልማት ለጉልበት ሥራ በመርከብ አስተላልፋለች ። ይህም የፖርቱጋል ቅኝ ግዛት ለነበረችው ብራዚል የኤኮኖሚ እድገት መሠረት ሆኗል ። ይህ የባርያ ኢንዱስትሪ የተሳካ ውጤት ያመጣው በመሃል አንጎላ የነበሩ የሁለት ጎሳዎች መሪዎች በንግዱ ስለተባበሩ ነው ። እነዚህም ቾክዌ የተባለው በምሥራቅ አንጎላ የሚገኝ ተዋጊ ጐሣና እንዲሁም አቪምቡንዱ የተሰኘ ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት (ከአንጎላ አርባ በመቶ) ያለውና በማዕከላዊና በደቡብ አንጎላ የሚኖር ጐሳ ነው ።

የፖርቱጋል ወታደሮች በአንጎላ ያልተቋረጠ የተቃውሞ ጦርነት አጋጥሟቸዋል ። እንዲያውም መሐል አገሩን መቆጣጠር የጀመሩት ከ1800 ጀምሮ ነው ። በኋላም የአውሮፓ ኃያላን አፍሪካን ለመቃራ



ሙት በ1884—1885 በበርሊን ሲገናኙ ፖርቱጋል ደካማ ኃይል [illegible] ነበረች አንጎላና ሞዛምቢክን ለመቆጣጠር የተፈቀደላት በእንግሊዝ ድጋፍ ነበር ።

ከዚህ ምዕት ዓመት በፊት በአንጎላ እንዲሠፍሩ ከፖርቱጋል የተላኩት ወንጀል የፈጸሙ እስረኞች ብቻ ነበሩ ። እስከ 1950 ድረስ በአንጎላ ከነበሩት ነጮች ግማሹ ያህል የትምህርት ቤት ደጃፍ ያልረገጡ ማይሞች ነበሩ ። ከቀሪው አርባ በመቶ ያህሉ ደግሞ ከአራተኛ ክፍል በላይ ያልተማሩ ናቸው ። በኬንያ እንደሰፈሩት የተማሩ ነጮች ሳይሆን አንጎላ የአውሮፓ ማይማን ገበሬዎች መጣያ ነበር ። ስለዚህም ብዙዎቹ ከገጠር ጥቁር ሴቶችን እያገቡ የድህነት ኑሮ መግፋት ተገደዱ ።

ፖርቱጋሎችን ከሌሎች ቅኝ ገዢዎች የተለዩ የሚያደርጓቸው ሁለት ጉዳዮች አሉ ። አንዱ የሚያግምሩ ከተሞች ሉዋንዳና ሎሬንሶ ማርከስ (ማፑቶ) የተሰኙትን በጥሩ ሁኔታ መገንባታቸው ሲሆን ፣ ሌላው በብዛት ከጥቁሮች ጋር በመጋባት ብዙ ዲቃላዎችን ማፍራታቸው ነው ። ይህም የሆነው የነጭ ሴቶች ቁጥር ጥቂት ስለነበረ ነው ። እንዲያም ሆኖ ነጮቹ በከተማ በመሰባሰብ ወደ ገጠሩ በእርሻ መሠማራቱን (እንደ ኬንያ እንግሊዞች) አልወደዱትም ።

በአንድ ወቅት በ1950 አካባቢ የፖርቱጋል መንግሥት በገጠሩ አንጎላ በግብርና ለሚሰራ ነጭ ሃምሳ ጋሻ መሬት በነፃ እንደሚሰጥና ከእሱም ጋር ላም ፣ በግ ፣ አሳማ ፣ ስድስት ዶሮዎች ፣ ስድስት ዳክዬዎች ፣ ጥቂት ጥንቸሎች እንደሚሰጥ ቢያውጅም ጥያቄውን ተቀብለው የተሰማሩት በዓመት ከመቶ አይበልጡም ነበር ።

አንጎላና ሞዛምቢክ በመጨረሻ በ1975 ነፃ ሲወጡ ፖርቱጊዞች በብዛት ጥለው የሄዱባቸው ምክንያቶች አንድም በመሬት ባለቤትነትና በእርሻ ያልተሰማሩ በመሆናቸው ነው ። ሌላው ምክንያት ነፃነት የሰጡት እንደ እንግሊዞች በጦር አሸንፈውና በድርድር ተስማምተው ሳይሆን በጦርነት ስለተሸነፉ የበቀል ርምጃ በመፍራት ነው ።

በሌላም በኩል በኬንያ የማኦ ማኦ ንቅናቄ ከተቀጨ በኋላ እስከ ነፃነት ድረስ ሰባት ዓመታት የዝግጅት ጊዜ ስለነበረ አውሮፓውያንና አፍሪካውያን የዘር መድልኦን አስወግደው በጋራ ሠርተው ለመበልፀግ ተስማሙ ። ከዚህም በቀር በኬንያ የብዙኃን አመራር ተመሠረተ እንጅ እንደአንጎላና ሞዛምቢክ ሥር ነቀል የፖለቲካና የርዕዮተ ዓለም ለውጥ አልተደረገም ። ሞዛምቢክና አንጎላ ግን ማርክሲስት የፖለቲካ አቅጣጫን ተከተሉ ። በዚህም ምክንያት ሶቪዬት ኅብረት የመንግሥት ሥልጣን የጨበጡትን ስትደግፍ ምዕራባውያን ደግሞ በፀረ—ኮሚኒዝም አቋም ተቃዋሚ ቡድኖችን ደገፉ ።

በተለይም አሜሪካ ሁልጊዜም የነፃነት ንቅናቄዎችን ሳይሆን የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎችን በመደገፍ የኤኮኖሚ ጥቅሟን ስትጋራ የቆየችውን ያህል ከነፃነት በኋላም ተራማጅ መንግሥታትን በሞቃወም የመቆሟ ነገር የተለመደ ሆነ ። አንጎላና ሞዛምቢክም ወደ ግራ አክርረው በመሄድና ተቀናቃኝ በማፍራት አገሮቻቸውን በጦርነት አዳከሙ ። የኤኮኖሚ ተቋሞችን በመውረስ ፣ የአንድ ፓርቲን አምባገነን መሪነት በመምረጥና ነፃ ጋዜጦችን በማገድ ማዕከላዊነትን አጠበቁ ። አንጎላ በቅኝ ግዛት ዘመን ሰባት ሬዲዮ ጣቢያዎች ፣ አሥራ ስድስት ጋዜጦች ፣ አሥራ አምስት መጽሔቶች የነበሯት ሲሆን ፣ ከነፃነት በኋላ አንድ ሬዲዮ ጣቢያና ሁለት ጋዜጦች (ሁሉም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የዋሉ) አሏት ። ኃያላኑ ለጥቅማቸው ሲሉ ተቃዋሚዎችን በርዕዮተዓለም ለያይተው ያቀራቁሳሉ ፤ አፍሪካውያኑም በፖለቲካ መቻቻል ፣ ሥልጣን መካፈልና የሚበጃቸውን አቅጣጫ መምረጥ አላወቁበትም ።

ማርክሲዝም በአፍሪካ ተሞክሮ ውድቅ ሆኗል ። በአንጎላና በሞዛምቢክም አልሠመረም ። በተሞከረበት አገር ሁሉ ብሔራዊ ኤኮኖሚ ይላሸቃል ፤ ሕዝቡ መብቱን እንዳይጠይቅ ይደረጋል ፤ የሶቪዬት የእጅ አዙር ተጽዕኖ ከገደብ አልፎ ይሄዳል ፤ መንግሥት በመጨቆን መምራት ይሻል ፤ የቢሮክራሲያዊ መረብ መንዛዛት የነበረችውን ጥቂት ቀልጣፋ አሰራር ያጨልማታል ። አፍሪካ ለኮሚኒዝም ተስማሚ የሆነ የማዕከላዊ አመራርና የጋራ ደህንነት ባህልና ታሪክ አልነበራትም ።



ከጋራ ጥቅም ይልቅ አፍሪካውያን የቤተሰብና የጎሳ ጥቅምን ማስበለጥ ይወዳሉ ። ለግል ኑሮ ካልሆነ በቀር ለጋራ እድገት በማሰብ ጠንክረው የመሥራት ባህል የላቸውም ። የማርክሲዝም መሠረታዊ ሃሳቦች ለአፍሪካውያን እንግዳ ናቸው ።

ማርክሲዝም በሶማሊያ ፡ በአልጄሪያ ፡ በጋና ፡ በጊኒ ፡ በሱዳን ፡በኮንጎ በኢትዮጵያ ውጤት እንዳላስገኘ ታይቷል ። በታንዛኒያም ጁሊየስ ኔሬሬ በቃል ሲያወሩት ይሰባል እንጅ በተግባር ፋይዳ አላስገኘም ። ርዕዮተዓለምና ፖለቲካ ከምሥራቅም ተቀዳ ከምዕራብ የተራበ ሆድን አይሞላም ፤ ወና የቀረ ፋብሪካን አይገነባም ። ይልቁንም ለብሔራዊ ልማት የሚጠቅም ጉልበትን በከንቱ የሚያባክን ነው ። ማርክሲዝም የኤኮኖሚ ማበረታቻዎችን በማጥፋት ሕዝቡ በድልነት ፕሬዚዳንቱ የሚወረውሯቸውን መፈክሮች ሲያነበንብ እንዲኖር የሚያደርግ ነው። ስለዚህ ለም መሬት እያላቸው ከእጅ ወደ አፍ ብቻ በሆነ ኑሮ በሕይወት ለመቆየት መታገል ብቻ ይሆናል ። ሥልጠና ፡ ትምህርትና ማበረታቻ የሌለው ሕዝብ ለምርት ዕድገት አይጨነቅም ። ጠንክሮ በመሥራት ለማደግ የሚችልበት በሩ ሲዘጋበት በሕይወት ለመሰንበት ብቻ ያህል ይሠራል ።

ማርክሲዝምን በሚከተሉ እንደ አንጎላ ባሉ አገሮች ምርት ለማሳደግ ይባልና በዕረፍት ቀን ነፃ አገልግሎት ይሰጣሉ ። እድገት ግን የለም ፡ ምክንያቱም በመደበኛ የሥራ ቀናት የሚሠራው ለግብር ይውጣ ስለሆነ ነው ። ይህም የሆነው የኤኮኖሚ ማበረታቻዎች ስለ ማይሰጡ ነው ። በዚህ ላይ የፖለቲካና የፓርቲ ስብሰባዎች የሚያባክኑት የምርት ሰዓት ጥቂት አይደለም ። ጋዜጦች የሚያቀርቡት ዜና ሳይሆን ፕሮፓጋንዳ ነው ፤ መጻሕፍት ቤቶች የሚሸጡት የኮምኒዝም መፃሕፍትን ብቻ ነው ። ሕዝቡ ለመላው ኅብረተሰብ ጥቅም እንዲሠራ ይወተወታል ፤ የእርሻ ልማት ጣቢያዎች ግን በአረም ተሞልተዋል ። ቃልና ተግባር የማይጣጣሙበት ዓለም ።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

# የውጭ ኃይሎች ያጠሉበት ሁኔታ

"ዩናይትድ እስቴትስ ስለምታውቀው ጉዳይ እንክብካቤ ብታደርግ ይሻላታል ። ስለአፍሪካ የምናውቀው ጥቂት ነው ። በአፍሪካ ስለሚገኙ 800 ጎሳዎች ምን እናውቃለን?. . . እኔ የተለየ ዓለም ዓይነት ነው እላለሁ ።"

ሴኔተር ሁበርት ሀምፍሪ
1976

በአንድ ወቅት ስለ አፍሪካ ረስቶ መቀመጥ ቀላል ነበር ሊባል ይቻል ይሆናል ። በ1980 ዓለም አፍሪካን በቅርብ ይጎዳኝ ጀምሯል ፤ አደጋውም እያደገ ሄዷል ። የአፍሪካ ቅምጥ የማዕድን ሀብት በዓለም አያሌ ከሚባሉት ነው ፤ አቀማመጧም እስትራቴጅአዊ በመሆኑ ከዚያ በመወርወር አንድ ወታደራዊ ኃይል የምዕራቡ ዓለም ነዳጅ ማመላለሻ የሆኑትን መስመሮች ቀይባህርን ጨምሮ ሊቆጣጠር ይችላል ። ቀይ ባህር ደግሞ የስዊዝ ቦይና የሜዴትራንያን ባህር መዳረሻ ነው ። በዚህ ላይ አፍሪካ በተባበሩት መንግሥታት ያላት የድምፅ ብዛትም ውሳኔ ዎችን ለማስለወጥ የሚያስችልና በርካታ ነው ። የብዙ ሽቀጥ ግራ ፊያንቷንም ይፈልጉታል ፤ ያልለማ የእርሻ መሬቷን ይሻሉ ፤ በሚሊየን ለሚቆጠሩ የአህጉሪቱና ሌሎችም ሕዝቦች ተስፋ የተጣለባት የዳቦ ቅርጫት ናት ። አፍሪካ ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ያላት ፣ ድንግል ክልል ሆና ለውስጥ ግጭትና ለውጭ ተጽዕኖ የተጋለጠች አህጉር ናት ። ጠመንጃና ገንዘብ ይዞ ለሚመጣ የውጭ ኃይል የምታጓጓ ነበረች ።

ስለዚህም ከሞስኮ እስከዋሽንግተን ፥ ከሪዮ ዲ ጃኔሮና ከሃቫና እስከ ፓሪስና ቶኪዮ መንግሥታት በአፍሪካ የተጽዕኖ ክልል ለመፍጠር ማሽኮርመም ጀመሩ ። ምናልባት ወደፊት ይህ አህጉር ከሃያና ሰላሣ ዓመት በኋላ የኃይል ሚዛንን ወደ አንዱ ወይ ወደሌላው ሊያጋድለው ይችላል በሚል ስጋት ነው ። የመጀመሪያው አፍሪካን የመከፋፈል ሩጫ ከመቶ ዓመት በፊት በበርሊን ተጠነሰሰ ። የአሁኑ አዲሱ የቅርምት ሴራ ረጋ ባለ ሥልት ይሁን እንጅ ዓላማው ተመሳሳይ ነው ። ያው ኢኮኖሚያዊና እስትራቴጂካዊ የበላይነትን ለመጨበጥ ነው ። እስከአሁን አፍሪካ ኢላማቸው ውስጥ ገብታለች ፤ ለመኖር የሚያስፈልጋትን ገንዘብ ከምዕራቡ ትሻለች ፤ የወቅቱ ጠላቶችዋን ለመዋጋት ጦር መሣሪያ ከምሥራቁ ካምፕ ትፈልጋለች ። ዶላሩንና ጠመንጃውን በመቀበል አፍሪካ ለሚሰጧት አገሮች ጥገኛ ሆናለች ። አፍሪካ ለራስዋ ችግሮች ራስዋ መፍትሔ እንድትፈልግ ጣልቃ እንዳይገቡባት ትለፈልፋለች ፤ ወታደራዊ ወይም ኤኮኖሚያዊ ችግር ሲመጣ ግን ሮጣ ወደ ሞስኮ ወይም ዋሽንግተን ወይም ፓሪስና ለንደን ታንኳኳለች ። ገለልተኛ ስለመሆንዋ ትናገራለች ፥ ግን ከናይጀርያ በስተቀር ለማንም ሳታጐበድድ የምታምንበትን አስተያየት ለመሰንዘር ወይም ርምጃ ለመውሰድ የምትችል አገር ማግኘት ያስቸግራል ። በአፍሪካ አዲስ የርዕዮተዓለም ክፍፍል ተፈጥሯል ። ተራማጅ ነን የሚሉት ወደ በላይ ጠባቂ መልአካቸው ወደ ሞስኮ ይመለከታሉ ። ለዘብተኛ ነን የሚሉት ወደምዕራብ ያማትራሉ ። በተለይ በድንበር ግጭት ወቅት የኃያላኑ ፍጥጫ ይጐላል ።

የአፍሪካን መንግሥታት ወዳጅነት ለአንድ ቀን መከራየት እንጅ መግዛት አይቻልም የሚል አባባል ስላለ በአፍሪካ ብዙ ነዋይ ያፈሰሱ አዱጋ እንዳለባቸው ያመለክታል ። የመንግሥታት ታማኝነት መሸቶ እስኪነጋ ይለወጣል ፤ አንዳንድ ጊዜም የበለጠ ለሰጣቸው ይገዛሉ ። መንግሥታት ሳይታሰብ ይገለበጣሉ ፥ የኢኮኖሚ ተቋሞች ይወረሳሉ ወይም ይመለሳሉ ፥ የውጭ ዜጐች ይባረራሉ ወይም ዳግም እንዲመጡ ይጋበዛሉ ።

ይህን ሁኔታ ከራሽያ የበለጠ የሚያውቅ ባይኖርም ራሽያኖች ቶሎ አይማሩም ። በዚህ ላይ የዘረኝነት ባህርያቸው ስለሚጎላ ከአፍ



ሪካውያን አይቀላቀሉም ። የሚኖሩት ለብቻ በተከለለ ግቢ ሆኖ ለዝቅተኛው የኤምባሲ ሥራ እንኳን ከአገሬው ሰው አይቀጥሩም ። ሾፌርና ወጥቤት ሳይቀር ከአገራቸው ያመጣሉ ። በሶማሊያና በአንጐላ መዋኛ ሥፍራ ለብቻቸው አስከልለው ነበር ። ከሥራ ቦታ ቤታቸው ድረስ (ቅርብ ቢሆንም) የሚመላለሱት በተመደበላቸው አውቶብስ ታሽገው ነው ። በየሄዱበት የሰው መውደድ አያጋጥማቸውም ።

የሞስኮ ፖሊሲ የክልል አለመረጋጋትን በማራገብ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ፤ የልማት ርዳታ ሳይሆን የጦር መሣሪያ በማቀበል ያተኮረ ነው ። በሞዛምቢክ ፥ በኢትዮጵያ ፥ በአንጎላ የተከተለችው ይህንኑ ለራስዋ ጥቅም የመስገብገብ ፖሊሲ ነው ። ተራማጅ ነን ብለው ጠላት ለሚያበዙት መሣሪያ በማቀበል ተጠቃሚ ለመሆን መሞከር ነው ። ዛሬ ሞስኮ ደጋፊዎችዋ ሁሉ ጠልተዋት ከየአገሩ እየተባረረች ነው ። ብጥብጥና የኤኮኖሚ ውድቀት ባለበት አገር ሁሉ ሶቪየት አለች ፤ ሰላምና የሰከነ የኤኮኖሚ እድገት አይበጃትም ።

ከሶቪዬት ወዳጅነት ጥቅም ያገኙ እጅግ ጥቂት ናቸው ። በልማት ርዳታ ስጦታዋ የሚጠቀሱት ጥቂት ናቸው ። ምሁራንም ብትልክ ያለ ራሽያ ቋንቋ አይችሉም ። በሶማሊያ የቆርቆሮ ሥጋ ማምረቻ አቋቁማ የነበረ ቢሆንም አብዛኛው በቅናሽ ዋጋ ወደ ሞስኮ የሚላክ ነበር ። ለታንዛንያ የማያስፈልጋትን 30,000,000 ዶላር የፈጀ የአየር መቃወሚያ መሣሪያ በዳሬሰላም ተከሉ ። ለኢትዮጵያ መሣሪያ በማጋዝ ለብድሩ መክፈያ በየዓመቱ ቡናዋን ያግዛሉ ። ጊኒ ቢሳው ከራስዋ የባህር ጠረፍ የተያዘውን የዓሣ ሀብት መልሳ ትገዛለች ። ሌላው አገር ዓሣ ለማጥመድ ባህሩ ዳር ላሉት አገሮች በየዓመቱ በሚሊየን ዶላር ሲከፍል ሶቭየት ግን ጥቅሟን በሚያስጠብቅ መልኩ ትዋዋልና በነፃ ታግበሰብሳለች ። ለዚያውም ዓሣውን አሟጥጣ ስለምታጠምድ የሚተርፍ አይኖርም ።

በአፍሪካ የሶቭዬት ወዳጅነት ታሪካዊም ፥ ሥነልቦናዊም ነው ። ምክንያቱም አሜሪካ እስከ ነፃነት ድረስ ግንኙነትዋ ከቅኝ ገዢ አገሮች ጋር የነበረ ሲሆን ፥ የሶቭዬት ግን ከነፃነት ንቅናቄዎች ጋር ነበር ። በዚህ ላይ አሜሪካ ደቡብ አፍሪካን ትደግፋለች ፤ ስለ ሰብአዊ መብት እያ

ወራች በራሷ ሀገር ያሉ አናሳ ጎሳዎችን ትጨቁናለች ። ይህ አንዳንድ የተማሩ አፍሪካውያን የሚጠቅሱልኝ ነው ። ያም ሆኖ አሜሪካና ሶቭዬት ለአፍሪካ ሕዝብ በነፃ ወደ ሀገራቸው የመግባት ዕድል ቢሰጡ አሜሪካ ሕዝቡን ለማጋዝ እልፍ አእላፍ መርከብ ማቅረብ ይኖርባታል ፤ ሶቭዬት ግን አንድ አውሮፕላን የሚሞላ ሰው አታገኝም ።

ኮሚኒዝም ከአፍሪካውያን ባህርይ ጋር ይጋጫል ። መጀመሪያ ነገር ሕዝቡ ሃይማኖተኛ ነው ፤ (ክርስቲያን ፤ እስላም ፤ ወይም ሌላ እምነት ያለው) ። ሁለተኛ አፍሪካዊ ከብቶቹን ሳይቀር በማራባትና በመቁጠር የሚረካ ካፒታሊስት ባህርይ ያለው ነው ። ሶስተኛ አፍሪካውያን በታሪካቸው ዲሞክራሲያዊና የጎሳ መሪያቸውንና የመንደር ሽማግሌያቸውን ሳይቀር ራሳቸው የሚመርጡ ናቸው ። አራተኛ አፍሪካውያን ግለኞች ስለሆኑ ለራሳቸው ፤ ለቤተሰባቸው ፤ ለጎሳቸው ብቻ መሥራትን ያለዚያም የኤኮኖሚ ጥቅም ለሚያስገኝ ነገር መልፋትን የሚመርጡ ናቸው ።

አሜሪካ ለአፍሪካ የገንዘብ ድጋፍና የድርቅ ርዳታ በማድረግ ረገድ ከሶቭዬት በብዙው የላቀ አስተዋጽኦ ማድረጉዋ እርግጥ ነው ። በሶቭዬት በኩል ጠመንጃና ርዕዮተዓለም እንጅ የልማት እርዳታ ማድረግ አልለመደባትም ። ይሁን እንጅ በአሜሪካም በኩል ቢሆን የፕሬዚዳንት ካርተር አስተዳደር እስከተቋቋመ ድረስ ለጥቁር አፍሪካ ብሶቶች ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው ቆይተዋል ። ዋሽንግተን ለአዲሶቹ ነፃ ሀገሮች የወደፊት ተስፋ ድጋፍ እንደምትሰጥ ብትገልጥም እውነተኛ ስሜትዋ ግን በአፍሪካ ከሚገኙ ፈረንጆች ጋር ነው ። ለፖርቱጊዞች ፤ ለሮዴሽያ ነጮችና ለደቡብ አፍሪካ ዘረኛ መንግሥት የበለጠ ድጋፍ ሰጥታለች ። ለምሳሌ በ1962 አሜሪካ የፖርቱጋልን ቅኝ አገዛዝ በመንቀፍ በተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ ላይ ለይስሙላ ድምፅ ሰጠች ። ነገር ግን ዋሽንግተን በአዞርስ የነበረውን የአውሮፕላን ማረፊያ ቁልፍ የጦር ካምፕ ላለማጣት ስትል በፕሬዚዳንት ኬኔዲና በኒክሰን ዘመን ቅኝ አገዛዝን በተመለከተ በተከታታይ ፖርቱጋሎችን በመደገፍ ድምፅ ስትሰጥ ኖራለች ።

ፕሬዚዳንት ኒክሰን በተከታታይ አሜሪካን የሚጎበኙ የአፍሪካ



መሪዎችን ባለመቀበል አሻፈረኝ ሲሉ ኖረዋል ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሄንሪ ኪሲንጀርም የአፍሪካን አገሮች አምባሳደሮች በቡድን ካልሆነ በስተቀር በግል አያነጋግሩም ነበር ። ይህ ሁሉ አሜሪካ ለጥቁር አፍሪካ ያላት ንቀትና አለማስተዋል መሆኑን የአፍሪካ ዲፕሎማቶች ይገነዘባሉ ። ሄንሪ ኪሲንጀር ስለአፍሪካ እጅ እጅ እንዳላቸው በግል ሲናገሩ ስለአፍሪካ ፖሊሲ መንደፍ የማይቻል ነው ብለዋል ። እህጉሩ ብዙ ልዩነት የሚታይበትና አንድ የፖለቲካ አቅጣጫ ያልያዘ ስለሆነ አርባና ሃምሳ ፖሊሲ ማውጣት ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል ።

ስህተት ነበሩ ። የካርተር አስተዳደር ከሶስተኛው ዓለም ጋር በበለጠ እኩልነት ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ለመፍጠር ቅድሚያ ትኩረት ሰጠ ። በ1978 ካርተር ናይጀሪያን ጐበኙ ። ለዚምባብዌ ነፃ መውጣት ንቁ ተሳትፎ አደረጉ ። ዋሽንግተንም የደቡብ አፍሪካን ነጮች መገሰጽና ማራቅ ጀመረች ። ካርተርና በተባበሩት መንግሥታት የአሜሪካ አምባሳደር የነበሩት አንድሪው ያንግ ለአፍሪካ ልዩ ትኩረት መስጠታቸው ያስገረማቸው የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ጀምስ ካላሀን ሲናገሩ ፤ "አፍሪካ ለዘለዓለም እዚያው ነበረች ፤ ዛሬ ግን አፍሪካን [illegible]ኘት ከአሜሪካ የሚጎዘው ሰው በርክቷል" ብለዋል ፡

[illegible]ግተን ለአንድ ክልል [illegible]ሰጠው ግምት የሚለካው በምትለግሰው የ[illegible]ርዳታ ነው ። [illegible] ካርተርና አንድሪው ያንግ ስለአፍ[illegible]ቱ እንጅ የሰጣት ርዳት ይህን ያክል አይደለም ። በ1979 አሜሪካ ለጥቁር አፍሪካ የሰጠችው ርዳታ 265,000,000 ዶላር ሲሆን ፤ ይህም ከዓመቱ የአሜሪካ ጠቅላላ ርዳታ አሥራ ሰባት ከመቶ ነው ። በሌላ በኩል ለእሥራኤል በዚያው ዓመት አሜሪካ የሰጠቻት ርዳታ 785,000,000 ዶላር ነበር ። ግብፅ ደግሞ በዚያው ዓመት ከአሜሪካ 750,000,000 ዶላር አግኝታለች ።

አሜሪካ በ1979 የመደበችው የርዳታ ገንዘብ አራት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ዶላር የነበረ ሲሆን ፤ በዓለም ከፍተኛው ርዳታ ነበር ። ነገር ግን ከአገሪቱ ሀብት ጋር ሲነፃፀር ከዓመት ገቢዋ ነጥብ ሁለት በመቶ ብቻ ስለሆነ ይህን ያህልም የሚደነቅ ለጋስነት አይደለም ። ለዚያውም ይህ የርዳታ መጠን በየዓመቱ እየቀነሰ የመጣ ነው ። ይህም ከአይዘን

አወር እስከ ኬኔዲ ዘመን ነጥብ አምስት ከመቶ ፤ በ1970 ደግሞ ነጥብ ሶስት ከመቶ ፣ ከካርተር እስከ ሬጋን ዘመን ደግሞ ወደ ነጥብ ሁለት ከመቶ እያቆለቆለ በመሄድ ርዳታው ከፖለቲካ ጋር እየተቆራኘ ሄደ ።

ጥቁር አፍሪካ ለአሜሪካ ንግድም አስፈላጊ ሆና ሳለ የአሜሪካ የመዋዕለ ንዋይ ተሳትፎና የልማት ተቋሞች ድጋፍ በጣም አነስተኛ ነው ። በጥቁር አፍሪካ የአሜሪካ መዋዕለ ንዋይ ሁለት ነጥብ አምስት ቢሊየን ዶላር ሲሆን ፤ አነስተኛ ሕዝብና ዝቅተኛ የተፈጥሮ ሀብት ባላት ደቡብ አሜሪካ ግን በስድስት እጅ ከዚህ ይበልጣል ። በብራዚል ብቻ ስምንት ቢሊየን ዶላር የሚገመት ሀብት በልማት ሥራ ላይ አውላለች ። ሌላው ቀርቶ በደቡብ አፍሪካ ብቻ አንድ ነጥብ አምስት ቢሊየን ዶላር የሚደርስ ኢንቬስትመንት ነበራት ። አሜሪካ በዓመቱ ለጥቁር አፍሪካ የሸጠችው ምርት ሶስት ነጥብ አራት ቢሊየን ዶላር ሲደርስ ፤ ከጥቁር አፍሪካ የገዛችው ምርት ግን አሥራ ሶስት ነጥብ ስድስት ቢሊየን ዶላር ነበር ። ይህም ለደቡብ አፍሪካ የሸጠችውን አንድ ነጥብ ሶስት ቢሊየን ዶላር የሚገመት ምርትና ከደቡብ አፍሪካ የገዛችውን አንድ ቢሊየን ዶላር የሚሆን ሸቀጥ ሳይጨምር ነው ። አሜሪካ ኢኮኖሚዋን ከአፍሪካ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ልማቶች ጋር ካላቆራኘች ከአህጉሯ ጋር ያላት የወጭና ገቢ ንግድ ሳይስተካከል እንደተዛባ ይቀጥላል ።

ሰላምና እድገት የሰፈነባት አፍሪካ ለሁሉም የምትጠቅም ትሆናለች ። ነገር ግን በጦርነት ፣ መሣሪያ በማጋበስ ፤ ጥቁር ከነጭ በሙጋጨት ፣ እርስበርስ በርዕዮተዓለም ተከፋፍሎ በመዋጋት ፤ ከመገንጠል ንቅናቄ እስከ ነፃነት ጦርነት መተራመስ ከቀጠለች ለራሷም ለሌላውም ጥቅም የለውም ።

"ኃያላን መንግሥታት አህጉራችንን የጦርነት አውድማ አድርገው ሕዝባችንን የመድፍ ቀለብ አደረጉት" አሉ ፕሬዚዳንት ኒሜሪ። "አህጉራችን ከአሁን ቀደም እስያ ለሃያ ዓመት የተጓዘችበትን የጦርነትና የጥፋት ጎዳና እንዳትከተል እፈራለሁ" ብለዋል ። ጥቁር አፍሪካ ከደቡብ አፍሪካ በስተቀር የጦር መሣሪያ አታመርትም ። ስለዚህ



የምትዋጋው ከውጭ በሚገዛ መሣሪያ ነው ። አፍሪካ ከራስዋ ጋር መታረቅ እቅቷት ኃያላኑን መንግሥታት መንቀፍ ቀሏታል ።

አፍሪካን ለግጭት የሚዳርጋት አንዱ ቅኝ ገዢዎች ያሰመሩት ልክ ያልሆነና ሕዝቦችን የሚከፋፍል ሰው ሰራሽ ድንበር መሆኑ እርግጥ ነው ። ነገር ግን ያም ባይሆንና ኃያላኑም መሣሪያ ባይሸጡላት አፍሪካ በጦርና በቀስት ከመዋጋት የምትድን አትመስልም ። ለምዕት ዓመታት የቆየ ልማድ በአሥርና ሃያ ዓመታት አይለቅም ። በአፍሪካ ሰዎች ሥልጣን በመያዝ ጄኔራልና ፕሬዚዳንት የሚሆኑት በመስማማት ሳይሆን በአብዛኛው በኃይል ነው ። መግደልና ማሰር እየቻሉ ከተቃዋሚዎቻቸው ጋር መወያየትና በድርድርና በመቻቻል ተስማምተው ሥልጣን መካፈልን ወይም ለሕዝብ ፍላጐትና ውሳኔ መገዛትን አይቀበሉም ። ለጊዜውና ለማስመሰል ካልሆነ በቀር የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶች ፣ የተለያዩ ጎሳዎችና ሃይማኖቶች ተግባብተው አንድ ላይ ለመሥራት አልቻሉም ። ይህን የሚያደርጉት አመራር የያዙ ጋጠወጦች በጠመንጃ ስለሚያምኑና በፖለቲካ ክርክር ስለማያምኑ ነው ።

በአፍሪካ ስለሚካሄዱት ጦርነቶች ትክክለኛ የዜና ዘገባ ለማቅረብ ያስቸግራል ። ብዙውን ጊዜ መንግሥታት ስለሁኔታው ትክክለኛ መግለጫ አይሰጡም ። ጦርነቱን ሸፋፍነው በምሥጢር ማካሄድ ይመርጣሉ ። ጋዜጠኞች ወደ ጦር ግንባር ሄደው እውነቱን ማወቅና መግለጥ የሚችሉበት ዕድል አይሰጣቸውም ። ማን እንዳጠቃ ፣ ማን እንደገደለ፣ ማን ጥፋት እንዳደረሰ ማወቅ አይቻልም ። ስለዚህ የምዕራብ ጋዜጠኞች ብዙ ጊዜ ዜናውን ከውጊያው ክልል ተሰደው ከሚመጡና ከመንግሥቱ ሬዲዮ ሥርጭት ወይም ከዲፕሎማቶች የወሬ ወሬ ለማስተላለፍ ይገደዳሉ ። አንዳንድ ጊዜም ለጋዜጠኞች ሕይወት አደገኛ የሚሆንበት ጊዜ አለ ። በኡጋንዳና ታንዛንያ ውጊያ ጊዜ አትሂዱ እያልናቸው በጀልባ ከኬንያ ወደ ኢንቴቤ የተሻገሩ አራት የምዕራብ ጋዜጠኞች መጀመሪያ የኡጋንዳ ጦር አባላት በፈገግታ ከተቀበሏቸው በኋላ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዷቸውና ገደሏቸው ።

የአፍሪካ ቀንድ እየተባለ የሚጠቀሰው፣ የምሥራቅ አፍሪካ ክፍል

ሶስት አገሮችን ያቀፈ ነው ። እነዚህም ኢትዮጵያ ፣ ሶማሊያና ጅቡቲ ናቸው ። በዚህ ክልል አስከፊ ጦርነት ተካሂዷል ። አሜሪካና ሶቭዬት ኅብረት በዚህ አካባቢ ካለው የአፍሪካ ቀንድ እስትራቴጂካዊ የባህር ጠረፍ የሚቆጣጠሩት ክልል ለማግኘት ሲፋጠጡ ቆይተዋል ። ክርስትናና እስልምና ፣ ማርክሲዝምና አፍቃሪ ምዕራብ አቋም በዚህ ክልል ሲያፋትጉ ቆይተዋል ። ድህነትና ጭቆናም በአካባቢው ተንሰራፍተው ኖረዋል ። ስደተኞች የበዙበት አካባቢ ነው ። ጦርነትና ድርቅ ተፈራርቀውበታል ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ከፍተኛ የስደተኞች ችግር የተከሰተበት አካባቢ መሆኑን የተባበሩት መንግሥታት መረጃዎች ይዘግባሉ ።

የአፍሪካ ስደተኞች ብዛት በመላው ዓለም ካሉት ስደተኞች ቁጥር ከግማሽ በላይ ነው ። በዓለም ዘጠኝ ሚሊዮን ስደተኞች ሲኖሩ አምስት ሚሊዮን አፍሪካውያን ናቸው ። ከአፍሪካ ሕዝብ ቁጥር ሲነፃፀር ከመቶ ሰዎች አንዱ ስደተኛ ነው ማለት ነው ። የአፍሪካ ስደተኞች ብዛት ከቤኒን ፣ ከብሩንዲ ፣ ከቻድ ፣ ከቦትስዋና ፣ ከማዕከላዊ አፍሪካ ሪፑብሊክ ፣ ከጅቡቲ ፣ ከጋቦን ፣ ከጋምቢያ ፣ ከላይቤርያና ከስዋዚላንድ ሕዝብ ድምር ይበልጣል ።

በ1965 የአፍሪካ ስደተኞች ቁጥር 535,000 ብቻ በነበረ ጊዜ የአፍሪካ ቤተክርስቲያናት ጉባዔ ለችግሩ ምክንያት ያለውን የደቡብ አፍሪካ የዘር መድልዎ ኮንኗ ። በ1979 ግን ጉባዔው ባወጣው ሪፖርት አምስት ሚሊዮን ለደረሰው የስደተኞች ቁጥር ብዛት ምክንያት የጥቁር አምባገነን መሪዎች ጭቆና መሆኑን አመልክቷል ። በዚሁ ሪፖርት ውስጥ "በሥልጣን ላይ ያሉ ብዙ አፍሪካውያን (ተማርን የሚሉት ባለሥልጣኖች) ለሕዝቦቻቸው በሕብረተሰብ ውስጥ መኖር የሚገባ ቸውን ሰብዓዊ መብቶች ለማሳወቅ ልባዊ ፍላጎት የላቸውም ። አሁን በአህጉሪቱ ያለውን የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ ስንመረምር በአፍሪካ ያለ ማንም ሰው ስደተኛ ሊሆን ይችላል" የሚል ሠፍሯል ።

በብዙ አጋጣሚዎች የስደተኞች ፍልሰት የአፍሪካን ድንበሮች ሰው ሰራሽነት የሚያንፀባርቅ ቅጥ ያጣ ነው ። ለምሳሌ 400,000 አንጎላውያን ወደ ዛየር ሲሰደዱ ፤ 200,000 ዛየራውያን ደግሞ ወደ አንጎላ



ሸሽተው ይገኛሉ ። በሺህ የሚቆጠሩ ብሩንዲዎች ወደ ሩዋንዳ ኮብልለዋል ፤ ይህንኑ የሚያክሉ ሩዋንዳውያን ደግሞ ወደ ብሩንዲ ተሰደዋል። በጠቅላላው ከአፍሪካ ሃምሳ አንድ ነፃ ሀገሮች ውስጥ ሃያ አምስቱ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ስደተኞች ያስተናግዳሉ ። ከስደተኞች ውስጥ ፕሬዚዳንቶች ፣ የቀድሞ ሚኒስትሮች ፣ የደፈጣ ውጊያ መሪዎች ፣ ነጋዴዎች ፣ የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰሮች ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ገበሬዎችና ዘላኖች ይገኙባቸዋል ። የእነዚህ ሰዎች ወንጀል ፣ ባልሆነ ወቅት ያልሆነ ቦታ መገኘታቸው ብቻ ነው ።

የሚያሳዝነው የአፍሪካ ስደተኞች ችግር ከራሷ ከአፍሪካ ይልቅ ለዓለም ኅብረተሰብ የበለጠ አሳሳቢ የመሆኑ ጉዳይ ነው ። የምግብ እጥረት ፣ የሕዝብ ብዛት ፣ ድርቅና ሌላም የተፈጥሮ አደጋም እንዲሁ ከአፍሪካ ይልቅ ዓለምን ያሳስበዋል ። ለአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች ግን ይህ ጉዳይ እንዲያውም ለገንዘብ ማግኛ ፣ በሀገር ሕልውና ስም ጭቆናቸውን ማመካኛና የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ማውጫ ሰበብ ሆኗቸዋል ። አንድ ጊዜ ኬንያ 80,000 ቶን ስንዴ ለዛምቢያ ሸጠችና ድርቅ መትቶኛል ብላ በመጮህ ያገኘችውን ርዳታ ማግኘያ በማድረግ የሸያጩን ገንዘብ ባንክ አስገባች ። ርዳታ ሰጭዎችም ይህን ያህል ሕይወት አዳንን የሚለውን እስታትስቲካቸውን ሞልተው ወደ ሀገራቸው ይመለሳሉ ።

የታንዛኒያው ፕሬዚዳንት ጁሊየስ ኔሬሬ በአንድ ወቅት ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር ፖል ሀርትሊንግ ጋር ሲነጋገሩ ችግርን መጠቀሚያ የማድረግ እስተሳሰብን በጥሩ ሁኔታ ሰብስብ አድርገው ገልጠውታል ። "ስደተኞችን እወዳቸዋለሁ ። ሀገሬን ያለሙልኛል ። ግን ገንዘብ የለኝም ። እናንተ ገንዘቡን ታመጣላችሁ" በማለት በምግብ ለሥራ ስም የሚከናወነውን ገልጠውታል ።

በአፍሪካ ከጎበኘኋቸው አገሮች ሁሉ እንደ ኢትዮጵያ በእአምሮዬ ተቀርጾ የቀረ ሀገር የለም ። በታሪክ የከበረችውና የዓለም አቀፍ ሽኩቻ የሚፈራረቅባት ኢትዮጵያ ዛሬ በአፍሪካ ቀንድ የኃይል ሚዛን የሚለካባት ሚዛን መጨበጫ ሆናለች ። የፖለቲካ ወገን የመለየት ሁኔታ እንዴት ተለዋዋጭ እንደሆነ መማር የሚቻልበት ቦታ ይህ ነው።

ኢትዮጵያ የሚለው ስም ከግሪክ ቃል የተወሰደ ሲሆን ፤ ፀሐይ የመታው ፊት ያለው ሕዝብ ማለት ነው ። ከግብጽ በስተቀር ኢትዮጵያ ከሁሉም አገሮች የቆየ ታሪክ ያላት ነፃ ሀገር ናት ። በመሀል አገር ያለው ደጋማ ለም መሬት በወጣ ገባ ተራራዎች የታጀበ ነው ። እነዚህ ተራሮች ኢትዮጵያውያን ከቆየ ጀግንነታቸው ጋር ራሳቸውን ከውጭ ወራሪ ጠብቀው ለመዝለቅ የተፈጥሮ ምሽግና ከለላ ሆነውላቸው ኖረዋል ። በዚህም ምክንያት ለብቻቸው ተገልለው የራሳቸውን ባህል በማዳበር ከሁለት ሺህ ዓመታት በላይ ቆይተዋል ። በጥቁር አፍሪካ ከላይቤርያ ሌላ በአውሮፓ አገር ቅኝ ሳትገዛ በነፃነት የቆየች ሀገር ኢትዮጵያ ናት ። የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት በአውሮፓ ሚሲዮኖች ያልመጣና እዚያው በቀል የሆነባት ብቸኛ የአፍሪካ አገርም ኢትዮጵያ ናት ።

በአፈ ታሪክ እንደሚነገረው የጥንቱ የኢትዮጵያ ንጉሥ ቀዳማዊ ምኒልክ የንጉሥ ሰለሞንና የንግሥት ሳባ ልጅ ነበረ ይባላል ። ብዙ ኢትዮጵያውያን የአውሮፓዊ መልክ ቅርጽ አላቸው ። የበላይ ሆኖ የኖረው የአማራው ብሔረሰብ ሌላውን ጥቁር አፍሪካዊ እንደዝቅተኛ ፍጡር ናቅ አድርጎ ይመለከተዋል ። የቀረው የምሥራቅ አፍሪካ ሕዝብ መሽከርከሪት መጠቀም ከመጀመሩ በፊት ኢትዮጵያውያን ታሪካቸውን በሚፃፍ ቋንቋ ይዘግቡ ነበር ። ይህም ቋንቋ አማርኛ ይባላል ። አምሀራ ማለት በሂብሩ ቋንቋ በተራራ ላይ የሚኖር ሕዝብ ማለት ነው ።

ኢትዮጵያ በጣም የተገለለችና ለብቻዋ የምትኖር ስለነበረች በባለቅኔው ሆሜር ዘመን የሀገር መጨረሻ ሩቅ ፣ የፀሐይ መጥለቂያ ሥፍራ ሆና ትመሰል ነበር ። በ1895 ኢጣልያ የሰነዘረችውን ወረራ አድዋ ላይ በማንኮታኮትም ኢትዮጵያ የአውሮፓን ኃያል አገር ጦር በማሸነፍ የመጀመሪያዋ የጥቁር ሀገር ሆናለች ።

በ1935 የኢጣልያ ፋሺስት አምባገነን ቢኒቶ ሙሶሎኒ ጦር ኢትዮጵያን ሲወር አፄ ኃይለ ሥላሴ ተሰደው በእንግሊዝ ሀገር ሳሉ ለዓለም መንግሥታት ማህበር (ሊግ ኦፍ ኔሽንስ) ስለሀገራቸው አቤቱታ አቀረቡ ። በ1936 በዚሁ ወቅት ባደረጉት ንግግር "ከአምላክ ግዛት



ውጭ አንዱ ከሌላው የሚበልጥ ሀገር የለም ። እግዚአብሔርና ታሪክ ፍርዳችሁን ያስታውሳሉ" በማለት አስመሩበት ።

አፄ ኃይለሥላሴ ፈላጭ ቆራጭ ሙሉ ሥልጣን የነበራቸው መሪ ነበሩ ። የሀገሪቱ ሀብትና ገንዘብ ሁሉ በእጃቸው ነበር ። የመሪዎች በምርጫ ሥልጣን መያዝ የሚባል ነገር አስበውት አያውቁም ። ሞ አንበሳ እየተባሉ የሚጠቀሱት እኒህ ንጉሥ ከዘመናዊ አፍሪካ አምባገነን መሪዎች በተለየ መልኩ ለኢትዮጵያ አንዳንድ ጠቃሚ የማሻሻያ ለውጦች አምጥተዋል ። አንድ ሶስተኛውን የሀገሪቱን በጀት ለትምህርት ማስፋፊያ አውለዋል ። የሚያማምሩ ሆስፒታሎችና ትምህርት ቤቶች አስገንብተዋል ። በአፍሪካ መሪዎች ደረጃ ሲታዩ አረመኔ ጭቆና ያካሄዱ አይደሉም ። በ1950ዎቹ አካባቢ የፖለቲካ እስረኞቻቸው ቁጥር አንድ መቶ አይሞላም ነበር ። አጭር ሆነው ግርማ ሞገስ ያላቸው ነበሩ ።


ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

ኃይለሥላሴና ንጉሣውያን ቤተሰቦች በምቾት ሲንደላቀቁ በ1970ዎቹ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በድህነት ይማቅቅ ነበር ። በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ በዓመት ዘጠና ዶላር ብቻ ነበር ። ከማይምነት የተላቀቀውም ሰባት በመቶ ብቻ ነበር ። ሕዝቡ ልክ እንደባርያ እየማሰነ በልዑላንና በመሳፍንቶች በተያዘው መሬት ላይ በጭሰኝነት ገባርና የበይ ተመልካች ሆኖ ኖሯል ።

አጼ ኃይለ ሥላሴ አስተዳደሩን ዲሞክራሲያዊ ለማድረግ ችላ በማለታቸው በሕዝቡና በጦር ኃይሉ አመፅ ከሥልጣን ተወገዱ ። ከየትኛውም የአፍሪካ አገር ይበልጥ አብዮት የሚያስፈልጋት ሀገር ኢትዮጵያ ስለነበረች ለውጡ መምጣቱ ተገቢ ነበር ። ባለመታደል ግን ሥልጣን የነጠቀው ቡድን ገዳይና በቀል የጠማቸው ማርክሲ



ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

ሴቶች ስብስብ ሆኖ አረፈ ። በመንግሥቱ ኃይለማርያም የተመራው ወታደራዊ ጁንታ በሙቶ የሚቆጠሩ ከፍተኛ ባለሥልጣኖችንና ከንጉሣውያን ቤተሰብ ጋር ግንኙነት የነበራቸውን ሁሉ ገደለ ። ሌሎችም ንክኪ ነበራቸው የተባሉ ሁሉ በየእስር ቤቱ ታጎሩ ። ከባድ ወንጀለኛ ያላቸውን በታላቁ ቤተ መንግሥት ምድር ቤት በሚገኘው የግብር ማግቢያ አዳራሽ በሰንሰለት እያስቀፈደደ ከግድግዳ ጋር አበታቸው ። ፀረ—አብዮተኛ ተብለው የተጠረጠሩ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በየመንገዱ ተረሸኑ ። ሰላሳ ሺህ የሚሆኑ ታሰሩ ። አንድ ቀን አንድ የደርግ አባል በስብሰባ ላይ ስለ ቀይ ሽብር ነቅፎ ጥያቄ በማቅረቡ መንግሥቱ ኃይለማርያም ኮልት ሽጉጡን መዞ እዚያው ስለገደለው ከዚያ በኋላ የሚናገር ጠፋ ይባላል ።

አፄ ኃይለሥላሴ በታላቁ ቤተ መንግሥት ከታሰሩ በኋላ ዓመት ያህል እንደቆዩ መሞታቸው ተሰማ ። ስለአሟሟታቸው ብዙ ዓይነት ወሬ ይናፈሳል ፤ የረሃብ አድማ አድርገው ሞቱ የሚሉ አሉ ፤ በመርዝ ተገደሉ የሚሉም አሉ ። የዘመናችን አፍሪካ ያፈራቻቸው ጠንካራና ተሰሚነት የነበራቸው መሪ ኃይለሥላሴ የተቀበሩበትን ቦታ የሚያውቁት አገራቱን የመሩ ወታደሮች ብቻ ናቸው ።


መንግሥቱ ኃይለማርያም

የሰላሣ ስምንት ዓመት ዕድሜ የነበራቸው መንግሥቱ ኃይለማርያም ሲአዩአቸው የዋህ ሰው ቢመስሉም የለየላቸው ጨካኝ አምባገነን ናቸው ። ለማንም ርኅራኄ የላቸውም ፤ ለቤተሰቦቻቸው ሳይቀር ሃዘኔታ አያሳዩም ። ሥልጣናቸውን እንዳረጋገጡ ንጉሡ እንዳረጉት በያለበት ፎቶግራፋቸውን አስለጠፉ ። የንጉሡ ዓይነት ፈላጭ ቆራጭ በመሆን የተንደላቀቀ የአኗኗር ዘይቤ ተከተሉ ። የግል ገናና ስም ለመገንባት በመኩራራት ሕዝቡን ረሱት ።

በኢትዮጵያ በተደረገው መፈንቅለ መንግሥት የተጠቀመችው ሶቪዬት ኅብረት ብቻ ናት ። ወዳጅነቷንም ከሶማሊያ ወደ ኢትዮጵያ



አዞረች ። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ትልቅና ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ያላት ፤ የግብጽ ሕይወት የሆነው የአባይ ወንዝ መፍለቂያና በቀይ ባህር ትልልቅ ወደቦች (አሰብና ምፅዋ) ያሏት ቁልፍ ቦታ ስለሆነች ነው ።

ሶማሊያ በ1974 ከሶቭዬት ኅብረት ጋር የትብብርና የወዳጅነት ስምምነት የተፈራረመች ሲሆን ፤ 6,000 ራሽያኖች በሶማሊያ አድራጊ ፈጣሪ ሆነው ቆይተዋል ። የሀገሪቱን መከላከያ ፣ የስለላ ተቋምና ማስታወቂያ ሚኒስቴርን እንደፈለጉ በማዘዝና የበርበራን ወደብ ለጦር ኃይል ማከማቻ በመጠቀም ሶማሌያንም እስከአፍንጫዋ አስታጥቃት ነበር ። ሶማሊያም አሜሪካንን በማግለል በሶቭየት በተቀነባበረ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በማጥላላት አጥብቃ ስትነቅፍ ቆየች ። አሜሪካዊ የተባለ ሁሉ ሶማሊያ ውስጥ መሥራት በማይችልበት ሁኔታ በያለበት ስድብና ዱላ ከሕዝቡ ይወርድበት ነበር ። በኤምባሲ ሠራተኞቻቸው ላይ ሕዝቡ ይተፋባቸው ነበር ። ወዲያውም የኤምባሲው ሠራተኞች ቁጥር እንዲቀነስ ሶማሊያ በማዘዝ ሶስት ብቻ ቀሩ ። ይህ ሁሉ የሆነው አሜሪካ ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅ ስለነበረች ነው ። ማንም የሶማሊያ ዜጋ ከውጭ ዜጋ ጋር እንዳይነጋገር ፕሬዚዳንቱ ድንጋጌ አወጡ ። የአሜሪካን ኤምባሲ ስልኮች ተጠልፈው የሚነጋገሩትን ሁሉ የስለላው ድርጅት በቴፕ እየቀረፀ ይመረምር ነበር ። አሜሪካ ኤምባሲ ውስጥ ሲገባ የታየ የሶማሊያ ዜጋ በሰላይነት ይመዘገብና ፍዳ ያገኘው ነበር ።

በ1977 ሶማሊያ ኦጋዴንን ለመውረርና ከራስዋ ግዛት ለመቀላቀል የሚያስችላትን ጦርነት ለመጀመር በከፍተኛ ዝግጅት ላይ ነበረች ። ወዲያውም ጦርነቱ ተጀመረና ሁለቱ ኃያላን ወዳጆቻቸውን ተለዋወጡ ። የሶማሊያ ጥያቄ ሶማሌዎች የሚኖሩበት በአፍሪካ ቀንድ ያለ መሬት ሁሉ ለእኔ ይገባል ነው ። በ1897 እና በ1908 አፄ ምኒልክ ከእንግሊዝና ከኢጣልያ ጋር ስምምነት በመፈራረም ያን ጊዜ ሰሜንና ደቡብ ሶማሊያን በቅኝ ያስተዳድሩ ከነበሩት እነዚህ ኃይሎች ጋር በመስማማት ኦጋዴን የኢትዮጵያ አካል ሆኖ እንዲዘልቅ ስምምነት አድርገዋል ። ሆኖም ኢጣልያ በ1934 ኢትዮጵያን ስትወር ኦጋዴንን በመቆጣጠር እስከ 1941 ድረስ ከራስዋ ቅኝ ግዛት ጋር



መንግሥቱ ኃይለማርያም

ቀላቅላ ስታስተዳድረው ቆየች ። በ1941 እንግሊዞች ኢጣልያን በማሸነፍ ኢትዮጵያ ነፃ ስትወጣ አጋዴንን ግን ራሳቸው እንግሊዞች በወታደራዊ አስተዳደር ሲቆጣጠሩት ቆዩ ። በ1950 እንግሊዞች "ታላቋ ሶማሊያ" በሚል ፈሊጥ ጅቡቲ ፡ አጋዴንና የኬንያ ሰሜናዊ ምሥራቅ ክፍል ለሶማሊያ እንዲሰጥ ለተባበሩት መንግሥታት ሃሳብ አቀረቡ ። የእንግሊዞች ሀሳብ ውድቅ ሆነና በኃይለሥላሴ ውትወታ በ1955 እንግሊዝ አጋዴንን ለኢትዮጵያ መለሰች ። ከአምስት ዓመት በኋላ ደግሞ የእንግሊዝ ሶማሊያና የኢጣልያ ሶማሊያ ነፃ ወጥተው አንድ ላይ በመሆን ሶማሊያን መሠረቱ ።

ሶማሊያ አጋዴንን ለመጠቅለል የነበራትን ምኞት ለማሳካት በከፈተችው ጦርነት መጀመሪያ ተሳካላት ። ፕሬዚዳንት ሲያድ ባሬ በምዕራብ ሶማሊያ ሕዝብ ነፃ አውጭ ስም እያሳበቡ እስከ አፍንጫው የታጠቀ ጦራቸውን ለወረራ አስገቡ ። በጥቂት ቀናት ውስጥ የአጋዴንን ግዛት ዘጠና በመቶ ተቆጣጠሩ ። እኔም ከምዕራብ ጋዜጠኞች ጋር ወደ ሞቃዲሾ ሄድሁና ፕሬዚዳንቱ ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጡ ተገኘሁ ። ጦርነቱ በጠቅላላ የሚካሔደው አጋዴን በሚኖሩ ሶማሌዎች ነው ፣ በማለት ሲያድ ባሬ ገለጡልን ። እነዚህ የአጋዴን ዘላኖች ታንኮችንና መድፎችን ከየት እንዳገኙ ሲጠየቁ ፡ ቀድሞ ፖሊስ የነበሩትና አጋዴን የተወለዱት ሲያድ ባሬ "እርግጠኛ አይደለሁም ፤ ከሶማሊያ ጦር ሠራዊት ተውሰው ሊሆን ይችላል" በማለት መለሱ ።



ሲያድ ባሬ

ከምዕራባውያን ጋዜጠኞች ጋር ሆነን ከጥቂት ቀናት በፊት የያዙትን ጅጅጋን ለማየት ጉዞ ጀመርን ። በሶስት ላንድሮበር መኪናዎች ሆነን የኢትዮጵያ የጦርአውሮፕላኖች እንዳይመቱን በሌሊት ጉዞ ቀጠልን ። ጅጅጋ ስንደርስ ከተማው ወና ሆኖአገኘነው ። ከተማው



አጠገብ ያለ የኢትዮጵያ ጦር ለቆት የሄደ የተራራ ምሽግ ላይ ወጣን ። ለክብራችን የታረደ ፍየል ተጠበሰልንና በላን ። ወዲያው የጋዜጠኞች መምጣት ተወርቶ ኖሮ ከዚያም ከዚያም የተሰባሰበ ሕዝብ በጅጅጋ ከተማ የድል ስልፍ ሲያደርግ ተመለከትን ። ገነት ሆቴል ፊት ለፊት ለተሰበሰበው ሠልፈኛ አስጐብኝአችን አብደላ አብዲ መኪና ላይ ወጣና "አሁን ይበቃል ፤ ወደ ቤታችሁ ሂዱ ፤ መንገዶች ላይ ብዙ ሰው አያስፈልግም ፡ አውሮፕላኖች ሊመጡ ይችላሉ" ሲል አስጠነቀቀ ።

ማስጠንቀቂያው ግን በጣም የዘገየ ነበር ። የኢትዮጵያ የጦር አውሮፕላኖች ከሰሜን በኩል ድንገት ብቅ አሉ ። የአጋዴንን ሰማይ ተንተርሰው ፡ ድምፃቸውን አጥፍተውና ግርማ ሞገስ ተላብሰው ከተፍ አሉ ። በመንገድ ዳር ማስታወሻ ደብተራችንን እንደገለጥንና ካሜራችንን እንደደገን ሱማሌዎች ሰልፈኞችም ሳያስቡት ጅጅጋ ከተማ ላይ ዳግም የሞት ጥላ አንዣበበ ።

በቅጽበት አውሮፕላኖቹ ወደ ሆቴሉ ዝቅ ብለው ተወረወሩ ። ቦምብና መትረየሱን አንጣጥተው እንደብራቅ ጮሁብን ። ሕዝቡ እየተጩዋጯኸ ተተራመሰ ። አንዱ ወደ መሬት ሲወረወር ፡ ሌላው በሌላው ላይ ሲወድቅ በድንጋጤ በእንብርክክ እየሄዱ ከለላ ፍለጋ ተጣደፉ ። እኔም መኪና ሥር ተደፋሁ ። ካሜራዬ ፡ ሲጃራዬና የፀሐይ መነጽሬ በየአቅጣጫው ተበተኑ ። ማስታወሻ ደብተሬን በሁለት እጆቼ እንደጨመደድሁ በሆዴ መሬቱ ላይ ተለጠፍሁ ። በዙሪያዬ ያሉት ለቅሶና ጩኸት ያሰማሉ ። ደብድቦን የሄደው ፓይለት ፈገግ ሲል በሃሳቤ ታየኝ ። ግራ ገባኝ ና ቆም ብዬ ፓይለቱን" ስለእግዚአብሄር አትግደለኝ! ፡ አሜሪካዊ ነኝ!" ለማለት አማረኝ ።

አውሮፕላኖቹ አራት ጊዜ በላያችን እየተመላለሱ በከፍተኛ ድምፅ አናወጡት ፤ በመትረየስ አረሱት ፡ መሬቱን አንቀጠቀጡት ፣ በሶስተኛው ቀጥ ብለው ወደ ሰማይ መጠቁና ዞረው በመገልበጥ ልክ ጭልፊት ጫጩት እንደምታድነው ወደ እኛ ተወረወሩ ። በአራተኛው ወደ መጡበት ተመለሱ ። ይህ ሁሉ የጥቂት ሴኮንዶች ድራማ የዓመት ያህል ጨነቀን ።

የአውሮፕላኖቹ ጩኸትና የተኮሱት ጥይት ብዙ ሰው ገደለ ፤



ሲያድ ባሬ

ብዙ አቆሰለ ። ከሆስፒታሉ ውጭ የነበረችው የሶማሊያ ነርስ ሳራ በመጀመሪያው በረራ ከጥቅም ውጭ ሆነች ፤ የሆስፒታሉ ብቸኛ ዶክተር አልጋ ላይ ሲወድቅ ሹል ነገር ቀዶት በጽኑ ቆሰለ ። አንድ ሲቢል ታካሚ ሆዱና ጭንቅላቱ ተነድሎ ቃሬዛ ላይ አስተኝተውታል ። ወደ አላህ የመጨረሻ ፀሎቱን አደረሰና ሰውነቱ ተንቀጥቅጦ ዝርግትግት አለ ። አጠገቡ የነበረው አስታማሚ የግሉኮስ ላስቲኩን ከክንዱ ላይ አወለቀና በችግር ጊዜ እንደ ሬሳ ማቆያ ወደ ሚጠቀሙበት የዕቃ ማስቀመጫ ጥላ አመራ ።

በጠቅላላው ሰባት ሶማሌዎች ሞቱ ፡ ሰላሳ የሚደርሱ ቆሰሉ ። ጥቃቱ ጅጅጋን ለመደምሰስ ሳይሆን የሕዝቡን ሞራል ለመጣል እንደነበር ግልጽ ነው ። ሰባት ብቻ ሊሞቱ የቻሉትም ለዚህ ነው ። ከጥቂት ቀናት በፊት በኢትዮጵያ የአየር ጥቃት ሶስት ሰዎች ሞተዋል፤ ከዚያም በፊት በተደረገ ሌላ ጥቃት ዘጠኝ ተገድለዋል ።

ሶቭዬት ኅብረት ወዲያውኑ ምርጫዋን ወሰነች ። ወደ ኢትዮጵያ በብዛት መሣሪያ ማጋዝ ጀመረች ። የአሜሪካ የስለላ ሳትላይቶች የሶቭዬት አውሮፕላኖች ባልተጠበቀ ሁኔታ በብዛት ወደኢትዮጵያ ሰማይ ሲጎርፉ ማየታቸውን ጠቆሙ ። የኢትዮጵያ ጦር ዓመት ባልሞላ ጊዜ የሶማሌን ጦር አሸንፎ ከግዛት አስወጣ ። ሶማሌዎችም ለአያሌ ተውልዶች ሲያካሂዱት ወደኖሩት የደፈጣ ውጊያ ተመለሱ ።

የመሣሪያ ማቀበሉ ሂደት በምሥራቅ አፍሪካ የኃይል ሚዛን ለውጥ አስከተለ ። በዓለም አቀፍ ፖለቲካ የካምፖች ልውውጥና የርዕዮተ ዓለም ቅያሬ አመጣ ። ፕሬዚዳንት ሲያድ ባሬ ራሺያኖችን አባረሩና ስለማርክሲዝም ቀና ማውራታቸውን አቆሙ ። የተባረሩት ራሽያኖች ብዙዎቹ ወደ ኢትዮጵያ ገቡ ። በተጨማሪም ሲያድ ባሬ በሞቃዲሾ የነበሩ ፀረ—አሜሪካ መፈክሮችን በማስነሳት ፡ በአሜሪካ ዲፕሎማቶች ላይ የሚያካሂዱትን ስለላ በማቆም ፤ ከዋሽንግተን የመሣሪያ ድጋፍ ጠየቁ ። ቀደም ሲል ሲያድ ባሬ በአሜሪካዊው የጥርስ ሐኪማቸው አማካይነት ከዋሽንግተን ጋር የምሥጢር ውይይት አካሂደው ለመከላከያ የሚሆኑ የጦር መሣሪያዎች ርዳታ እንደሚሰጣቸው ቃል ተገብቶላቸው ነበር ። ስለዚህም አሜሪካ ከብዙ ዓመት በኋላ



የዲፕሎማቲክ ተልእኮ ያላቸውን ስድሳ ዘጠኝ ዜጎቿንና ለሶማሊያ የሰጠችውን 86,000,000 ዶላር ርዳታ ይዛ ወደ ሶማሊያ ተመለሰች። ወዲያውም ራሺያኖች ለቀውት የሄዱት ቢሮና መኖሪያ ቤት ውስጥ ገቡ ። ከዚያም ሶቭየቶች የነበሩበትን የበርበራ ወደብ ለጦር ማከማቻ ለመጠቀም መደራደር ጀመረች ። በዚያው ሰሞን ኢትዮጵያ ደግሞ አሜሪካንን በማስወጣትና ከሶቭዬት ጋር የወዳጅነትና የትብብር ስምምነት በመፈራረም በጥቁር አፍሪካ የመጀመሪያዋ እውነተኛ ኮሚኒስት ሀገር ለመሆን መወሰኗን አወጀች ። በዚህም የአቋም ለውጥ የዋሽንግተን የቅርብ አጋር የነበረችው የሶቭየት ጭራ ሆነች ። የሞስኮ የእንጀራ ልጅ የነበረችው ደግሞ በአሜሪካ ሞግዚትነት ሥር ተወሸቀች። ኢትዮጵያና ሶማሊያ ራሳቸውን ለግልጽ የገበያ ጨረታ አቅርበው የተሻለ ዋጋ ላቀረበላቸው ታማኝነታቸውን ሸጡ ። አንድ ቀን ይህ የአጋርነት አሰላለፍ ይፈርስና የታማኝነት ለውጥ እንደሚደረግ ጥርጥር የለውም ።

በአፍሪካ ቀንድ የታየው ወደኋላ መገለባበጥ የሚያሳየው የአፍሪካ የወደፊት ዕድል በምሥራቅና በምዕራቡ እጅ መሆኑንና ሁለቱም ካምፖች አፍሪካን ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ ሀብት ሊያፈሱባት የምትገባ ጠቃሚ አህጉር አድርገው የወሰዱት መሆኑን ነው ። ራሽያኖች እስከ መጨረሻው የኩባ ደም ጠብታ ለመዋጋት ዝግጁ ሲሆኑ ፤ አሜሪካም የሶቭዬትን የመስፋፋት ጥረት በወታደሮቿም ባይሆን በጠመንጃዎቿ ለመገደብ ቆርጣለች ። በእርግጥም የአፍሪካ የተፈጥሮ ሀብትና እስትራቴጅያዊ አቀማመጥ ፤ ብሉም ራሷን ለመከላከል ያለመቻልዋ የውጭ ኃይሎች ፍጥጫን ሊያካትት በሚችል ለሌሎች ጣልቃ ገብነት የተጋለጠች አድርጓታል ።

እንደሚመስለኝ እያንዳንዱ የአፍሪካ አገር የራሱን የመንግሥት ዓይነት መምረጥ አለበት ። ማርክሲዝም በሞዛምቢክ ሲንኮታኮት ፤ ካፒታሊዝምም በጋና ከዚሁ ባላነሰ ሁኔታ ርባና ቢስ ሆኗል ። ነገር ግን ማርክሲዝም በባህርይው አፍሪካውያንን የኤኮኖሚ እድገት ነፃ ነፃ ሕዝብ ለመሆን የሚያስፈልጋቸውን የግል ክብር ነጥቋቸዋል ። ይህንን ለመቋቋም ምዕራቡ ዓለም አፍሪካ ለእድገት የሚያስፈልጋ

ትን የፋይናንስ ርዳታ መቀጠል አለበት ። ምንም እንኳን በአንዳንድ መዝባሪ ፕሬዚዳንቶችና በትክክል ባልተተለሙ ፕሮጀክቶች የርዳታው ገንዘብ አብዛኛው እጅ የሚሟጠጥ ቢሆንም የልማት ርዳታው መቀጠል አለበት ። አሳዛኝ ቢሆንም ምናልባትም አፍሪካ ድንበሮቿን ለመጠበቅ የሚያስፈልጓት ጠመንጃዎችንም መስጠት ይኖርባት ይሆናል ። ምንም እንኳን ይህን ጠመንጃ አምባገነን ፕሬዚዳንቶች የራሳቸውን አገዛዝ ለማቆየት የሚጠቀሙበት ቢሆንም ። ያለዚያ ሌላው አማራጭ ሞስኮ አፍሪካን አንድ በአንድ በመቆጣጠር ፣ የአገሮችን የርስበርስ ሽኩቻ በመጠቀም በፍላጎታቸው ያልተቀበሉትን ኮሚኒዝም ለሀገሮች በመምረጥ እንደአሻት እንድታደርጋቸው መፍቀድ ይሆናል ።



ምዕራፍ አሥር

# በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም አቅጣጫዎች

“ስለአፍሪካ አንድነት ማህበር የሚናገሩትን ሰዎች የምጠይቃቸው ፣ ምናችንን ለመካፈል ነው? የየእንዳንዳችንን ድህነት?

—ፕሬዚዳንት ሁፌት ቡዋኚ
(አይቮሪኮስት)

“በጊኒ በመጀመሪያዎቹ ሃያ ዓመታት ያተኮርነው የሕዝባችንን አስተሳሰብ በማዳበር ነው ። አሁን ወደሌላው ጉዳይ ለመሸጋገር ዝግጁ ነን ።

—ፕሬዚዳንት አህመድ ሴኩ ፣ ቱሬ(ጊኒ)

አይቮሪ ፣ ኮስትና ጊኒ በምዕራብ አፍሪካ ከሚጋሯቸው ነገሮች
ዱ የጋራ ድንበር ነው ። ሁለቱም የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት የነበሩ
ው ። ሁለቱም የእርሻ ልማትን የላቀ ግምት ሰጥተውታል ። የፖ
ካ መረጋጋትም ነበራቸው ። ሁለቱም የኢኮኖሚ እድገት ፣ የግለ
ብ ክብርና በራስ መተማመንን ብሔራዊ ግብ ለመጨበጥ ይታገላሉ።
ነታቸውን የተቀዳጁትም በሁለት ዓመት ልዩነት ነው ። ጊኒ
958 ፣ አይቮሪ ኮስት ደግሞ በ1960 ።

በቅኝ አገዛዝ ማክተሚያ ግድም ጊኒ ሀብታም አገር ነበረች ።
ቁር አፍሪካ ከሁሉም የበለፀገች ሀገር ትሆናለች ብለው ብዙዎች
ገሩ ነበር ። በከርሰ ምድርዋ በዓለም ካለው የቦክሳይት ክምችት
ድ ሶስተኛውን አቅፋ ነበር ። በአፍሪካ ግንባር ቀደም ሙዝ አም
ና ላኪም ነበረች ። ከለም መሬቷ የሚመረተው አብዛኛዎቹን